የሂዩማኒስት ፣ የዎች ጥናት ፣ ጋዜጠኝነትና ፣ ኮምኒዩኬሽን ኮሌጃ

የአማርኛ ቋንቋ ስነ-ፅሁፍ ፎክለር  ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርህ ግብር

# የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን አቀናጅቶ ማስተማር ክሂሎችን ለማሻሻል ያለው ሚና ትንተና

## ( በጉራጌ ዞን በገደባኖ ጉታዘር ወለኔ ወረዳ 9ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኩሪነት )

በ

ለምለም ከበደ

ነሐሴ 2016 ዓ.ም

አዲስ አበባ

የሂዩማኒስት ፣ የቋንቋዎች ጥናት ፣ ጋዜጠኝነትና ፣ ኮምኒዩኬሽን
ኮሌጃ የአማር ኛ ቋንቋ ስነ-ፅሁፍ ፎክለር  ትምህርት ክፍል

# የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን አቀናጅቶ ማስተማር ክሂሎችን ለማሻሻል ያለው ሚና ትንተና (በጉራጌ ዞን በገደባኖ ጉታዘር ወለኔ ወረዳ 9ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተከሪነት)

የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር
ለአማርኛ ቋንቋና ስነ-ፅሁፍ ትምህርት ክፍል አማርኛን ለማስተማር
(TeAM) ለኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናት

የጥናቱ አማካሪ
ዳዊት ፍሬህይወት (ዶ/ ር )

ነሐሴ 2016
አዲስ አበባ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ ፣ ቋንቋዎች ጥናት፣ ጋዜጠኝነትና ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ ስነ-ፅሑፍ እና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት


# የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን አቀናጅቶ ማስተማር ክሂሎችን ለማሻሻል ያለው ሚና ትንተና

በ

ለምለም ከበደ

የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ

የፈተና ቦርድ አባላት

| | |
|---|---|
| የአማካሪ ስም | ፊርማ |
| ____________________________ | ______________ |
| ____________________________ | ______________ |
| የፈታኝስም | ፊርማ |
| ____________________________ | ______________ |
| ____________________________ | ______________ |

# ምስጋና

ይህ ጥናት በተሳካ ሁኔታ እንዲጠናቀቅ ሰፊ ጊዜያቸውን ሰውተው አቅጣጫ በማስያዝና በማስተካከል ለተባበሩኝ አማካሪዬ ዶክተር ዳዊት ፍሬህውት ጥልቅ ምስጋናዬን አቀርባለኡሁ ። እንዲሁም ይህን የመማር እድል ለሰጠኝ አዲስ አበባ ተዩኒቨርሲቲን እና ያስተማሩኝን መምህራኖቼን አመሰግናለሁ ። ውድ ጊዜያቸውን ሰውተው መረጃ በመስጠት ለተባበሩኝ የገደባኖ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የዘጠንኛ ክፍል የአማርና ቋንቋ መምህራንና ተማሪዎች ከልቤ አመሰግናለሁ።በመጨረሻም ትምህርቴን ጀምሬ እስክ ምጨርስ በገንዘብና በቁሳቁስ ለተባበሩኝ የስራ ባልደቦቼ እ፣ለባለቤቱ እንዲሁም ለቤተሰቦቼ ምስጋናዬ የላቀ ነው።

# ማውጫ

**ይዘት** **ገጽ**

ምስጋና....................................................................................................... i

አጠቃሎ ....................................................................................................vii

ምዕራፍ አንድ

መግቢያ...................................................................................................... 1

1.1 ጥናቱ ዳራ.............................................................................................. 1

1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት............................................................................ 3

1.3 የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄዎች....................................................................... 4

1.4 የጥናቱ ዓላማ.......................................................................................... 4

1.5 የጥናቱ ጠቀሜታ ...................................................................................... 4

1.6 የጥናቱ ወሰን........................................................................................... 5

1.7 የጥናቱ ውስንነት ...................................................................................... 5

1.8 የፅንስ ሀሳቦች አጠቃቀም ብያኔ.................................................................. 6

ምዕራፍ ሁለት

ክለሳ ድርሳናት…………………………………………………………………….7

2.1 የቋንቋ ክሂሎትና የይዘት ምንነት ................................................................ 7

2.1 የቋንቋ ክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ ምንነት ................................................ 7

2.2.2 የቋንቋ ክሂሎችን አቀናጅቶ የማቅረብ ጠቀሜታ............................................ 8

2.2.3 የቋንቋ ክሂሎችን አቀናጅቶ የማቅረቢያ ዘዴዎች........................................... 9

2.3. የአንብቦ መረዳት ምንነት ........................................................................ 10

2.3.1 የንባብ ትምህርት አስፈላጊነት ................................................................ 11

2.3.2 አንብቦ የመረዳት ትምህርት አቀራረብ ....................................................... 12

2.3.3 አንብቦ የመረዳት ጥያቄዎች ሲዘጋጁ ትኩረት የሚደረግባቸው ነጥቦች ............... 14

2.4 የጽህፈት ክሂል ምንነት ............... 16

2.5 የጽህፈት ክሂል ትምህርት አስፈላጊነት ............... 17

2.6 የማንበብና የመጻፍ ክሂሎች ትስስር ............... 17

2.6.1 አንብቦ መረዳትንና የመጻፍ ክሂልን በቅንጅት የማቅረብ አስፈላጊት ............... 18

2.6.2 አንብቦ መረዳትንና የመጻፍ ክሂልን ለማዳበር የሚረዱ ብልሃቶች............... 19

2.7 የቀደምት ስራዎች ቅኝት ............... 22

ምዕራፍ ሶስት

የአጠናን ዘዴ ............... 25

3.1 የጥናቱ ዘዴ............... 25

3.2 የመረጃ ምንጮች ............... 25

3.3 የጥናቱ ናሙና አመራረጥ ............... 26

3.3.1 የክልልና የዞን አመራረጥ ............... 26

3.3.2 የትምህርት ቤት አመራረጥ ............... 26

3.3.3 የመምህራን አመራረጥ ............... 26

3.3.4 የምድብና የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ ............... 27

3.4 የጥናቱ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ............... 27

3.4.1 ፈተና............... 27

3.4.1.1.ቅድመ ትምህርት ፈተና ............... 28

3.4.1.2. ድህረ ትምህርት ፈተና ............... 29

3.4.2 ምልከታ ............... 30

3.4.3 የተማሪዎች ቃለ መጠይቅ............... 30

3.4.4 የመምህራን ቃለ መጠይቅ ............... 31

3.5 አጠነቃቀር አቀራረብና አተናተን ዘዴዎች............... 31

ምዕራፍ አራት

የመረጃ ትንተናና የጥናቱ ውጤት ........ 33
4.1 መፃፉ አንብቦ የመረዳትና የመፃፍ ክሂልን ለማቀናጀት ያለው እገዛ ........ 33
4.2 ከምልከታ የተገኘ መረጃ ትንተና ........ 33
4.3 ከመምህራን ቃለ መጠይቅ የተገኘ ምላሽ ........ 35
4.4 ከተማሪዎች ቃል መጠይቅ የተገኘ የመረጃ ትነተና ........ 41
4.5 ከሙከራ ቡድኑ የተወሰደ የድህረ ትምህርት ቃለ መጠይቅ ትንተና ........ 43
4.5.1. ከመምህራን ቃለ መጠይቅ የተገኘ ምላሽ ........ 45
4.5.2. ከተማሪዎች የቅድመና ድህረ ፈተና የተገኘ ውጤት ትንተና ........ 47
4.6 ከምልከታ የተገኘ መረጃ ትንተና ........ 50
4.7 ከመምህራን ቃል መጠይቅ የተገኘ ምላሽ ........ 52
4.8 መምህራን የማንበብና የመፃፍ ክሂልን ለማቀናጀት የሚያደርጉት ጥረት ........ 53
4.8.1 ከመምህራን ቃለ መጠይቅ የተገኘ ምላሽ ........ 56
4.8.2 መምህራን ለማንበብና ለመፃፍ ክሂል ቅንጅታዊ አቀራረብ ያላቸው ግንዛቤ ........ 57
4.8.3 ከመምህራን ቃል መጠይቅ የተገኘ ምላሽ ........ 58

ምዕራፍ አምስት

ማጠቃለያና የመፍትሔ ሀሳብ ........ 59
5.1 ማጠቃለያ ........ 59
5.2. የመፍሀሔ ሀሳብ ........ 61
ዋቢ ጽሑፎች ........ 62
አባሪዎች ........ 65

## አባሪዎች


አባሪ አንድ በሙከራ ቡድኑ ለተካተቱ የ9ኛ “ለ” ክፍል ተማሪዎች የተዘጋጀ ቅድመ ትምህርት ፈተና፡፡ ........ 65

አባሪ ሁለት በሙከራ ቡድን ለተካተቱ የ9ኛ ክፍል ተመሪዎች የቀረበ ቅድመ ትምህርት ቃለ መጠይቅ ........ 68

አባሪ ሶስት የመምህራን ቃለ መጠይቅ ........ 69

አባሪ አራት የምልከታ ቅጽ ........ 70

አባሪ አምስት በሙከራ ቡድኑ ለተካተቱ ተማሪዎች የተዘጋጅ የድህረ ትምህርት ፈተና ........ 73

አባሪ ስድስት ለሙከራ ቡድኑ የቀረበ የድሀረ ትምህርት ቃለ መጠይቅ ........ 76

አባሪ ሰባት ለሙከራ ቡድኑ አባላት ማስተማሪያነት የተዘጋጀ ዕቅድ ........ 77

አባሪ ስምንት፡ የቅድመ እና ድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት ዝርዝር ........ 86

አባሪ ዘጠኝ ለቡድኑ አባላት ማስተማሪያነት የተዘጋጀ እቅድ ........ 87

አባሪ አስር፡ተማሪዎች ትምህርት ሲማሩ የሚያሳይ መረጃ በፎቶ ........ 88

## የሠንጠረዠ ማውጫ

ሠንጠረዥ 1፡- መፀሀፉ  አንብቦ የመዳትና የመፃፍ ክሂልን ለማቀናጅት ያለው እገዛ፡፡..........34

ሠንጠረዥ 2 ፡- ከመምህራ ቃለ መጠይቅ የትግኙ መረጃዎች ..........................................39

ሠንጠረዥ 3 ፡- የእለቱ ትምህርት  ይዘት የማበብና የመፃፍ ክሂል ደረጃዎችን ለማከናወን ናየተማሪዎችን ፍላጎት ለማነሳሳት ያለው ሚና ምን እንደሚመስል ለመፈተሽ በተደረገው ምልከታ የተገኘው ምላሽ..........................................................................................44

ሠንጠረዥ 4 ፡- የእልቱ ትምህርት የማንበብና የመፃፍ ክሂልን ለማቀናጀትና ለማዳበር ያላቸው ሚና ምን እንደሚመስል ለማወቅ በተደረገው ምልከታ የተገኝ ምላሽ..................................46

ሠንጠረዥ 5 ፡ - የቅድመ እና ድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት ዝርዝር..............................48

ሠንጠረዥ 6፡ - በሁለት ዙር የተገኘው ውጤት ንጽጽራዊ ትንተና......................................49

ሠንጠረዥ 7 ፡-መምህራን የማንበብና የመፃፍ ክሂልን አቀናጅቶ ለማስተማር የሚጠቀሙባቸው ስልቶችን ምን እንደሚመስሉ ለማወቅ በተደረገው ምልከታ የተገኝ ምላሽ፡፡ ..........................51

ሠንጠረዥ 8፡-መምህራን የማንበብና የመፃፍ ክሂልን ለማቀናጀት የሚያደረጉትን ጥረት ለመፈተሽ በተደረገው ምለከታ የተገኝ ምላሽ፡፡ ....................................................................53

# አጠቃሎ

*የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በጉራጌ ዞን በገደባኖ ሁለተኛ ደረጃ ትምህረት ቤት የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን አቀናጅቶ ማስተማር ክሂሎችን ለማሻሻል ያለው ሚና መተነን ነው። የጥናቱ የአጠናን ዘዴ ቅይጥ የምርምር ዘዴ ሲሆን በዋናነት አይነታዊ ምርምርና በደጋፊነት ደግሞ መጠናዊ ምርምር ዘዴን አካቷል። የጥናቱ ሂደትም ተግባራዊ ይሆን ዘንድ አስፈላጊ መረጃዎችን ለመሰብሰብ የክፍል ውስጥ ምልከታ፣ ለተማሪዎች የቅድመና የድህረ ትምህርት ፈተና እና ቃል መጠይቅ ፤ ለመምህራን ደግሞ በቃለ-መጠይቅ  መረጃ ተሰብስባል። የተገኙት መረጃዎችም በሰንጠረዥ ተደራጅተው በቁጥርና በመቶኛ ተተንትነው ቀርበዋል። እንዲደዚሁም በቃል መጠይቅ የተገኙ መረጃዎችም  በምልከታ ለተገኙ መረጃዎች አጋዥ ሆነው ተተንትነዋል። የመከራ ቡድኖቹም ቅድመ ትምህርት ፈተና ተፈትነዋል። ለእንድ ወር በእቅድ የተደገፍ ትምህርት ተምረው ድህረ ህርት ፈተና ተፈትናዋል። በቡድኖቹ መካከል ያለውን ልዩነት ለማረጋገጥ የፈተናእ ውጤት በአማካይ ተስልቶ ተነፃፅሯል ። ከተማሪው የተገኘው ቃለ መጠይቅምላሽና ክንውን ምልከታው ተመሳሳይነት አረጋግጧል ።ስለዚህ የማንበብና ይመፃፍ ክሂሎች ካላቸው ትስስርና ዝምንድና አንፃር በተናጥል ከመቅረብ ይልቅ በቅንጅት ቢቀርብ ለክሂሌችን መጐልበት የላቀ እንደሆነ ጥናቱ አሳይቷል።በመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች አመካይነት በተገኘ የውጤት ትንተና መሰረትም መምህራን የማንበብና የመፃፍ ክሂልን በቅንጅት ለማስተማር እየተገበሩት ያለው አካሄድ ክሂሎቹን ለማቀናጀትና ለማዳበር ያላቸው ሚና ዝቅተኛ እንደሆነ መምህራን ከተማሪዎች ችሎታ፣ ዳራና ፍላጎት ጋር የተጣጣሙ ይዘቶችን፤ን እንደማያቀርቡ፣ ከመማሪያ መጽሀፍ  በተጨማሪ ለዓላማው ተስማሚ የሆኑ አጋዥ መሳሪያዎችን እንደማይሰጡ ተረጋግጧል።  የመማሪያ መጽሐፍ የማንበብና የመፃፍ ክሂልን በቅንጅት ለማቅረብ አመቺ እንደልሆነና ለ፳፱መምህራን ስለኪሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ አጫጭር ስልጠናዎችንና ዋረክሽፖችን አለሰመስጠት ተፅእኖ እንዳሳደረባቸው ለማወቅ ተችሏል። የተገኘው የትንተና ውጤት እንደሚያሳየው የማንበብና የመፃፍ ክሂልን በቅንጅት ማስተማር ዘዴ  በዝቅተኛ ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ተመላክቷል።*

# ምዕራፍ አንድ
# መግቢያ

## 1.1 ጥናቱ ዳራ

የቋንቋ ትምህርት በዋናነት ዓላማው ተማሪዎች የዳበረ የተግባቦት ብቃት እንዲኖራቸው ማስቻል ነው። የትምህርቱ አጠቃላይ አላማዎች የማዳመጥ ፣ የመናገር፣ የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን ለማጎልበት እንዲሁም ተጓዳኝ የቋንቋ ክሂሎች የሆኑትን የሰዋሰውና የስነጽሑፍ መሰረታዊ። ዕውቀቶችን ለማዳበር ነው።እነዚህም ክሂሎች በክፍል ውስጥ እንዴት መተግበር እንዳለባቸው መርሀ ትምህርት ተዘጋጅቶላቸው በተናጥል ይሰጣሉ።

ውስብስብ የሆነውን የማስተማር ስራ ቀላል ለማድረግ ከ2000 አመታት በላይ እድሜ ካስቆጠረው ከሰዋስው ዘዴ ጀምሮ በርካታ ሙከራዎች ተካሄደዋል።በመሆኑም Squire (1984) ባደረገው ጥናታዊ አሳብ ቋንቋን ለማስተማር ሲታሰብ በዋናነት የሚነሳው ጉዳይ ምን እና እንዴት እናስተምር የሚለው ጉዳይ ነው። ይህ የይዘት መረጣእና የማስተማሪያ ስልት መወሰንን ይመለከታል። በተለይም ከይዘት መረጣ በኋላ የማስተማሪያ ዘዴውን መወሰን በጣም ወሳኝ እና ትኩረት የሚሻ ጉዳይ ነው። ተማሪዎች በየአንዳዱ የቋንቋ ክሂል ላይ ብቃት አግኝተው የሚገለገሉበትን ቋንቋ እንዲያጎለብቱ ለማድረግ በጥንቃቄ የታቀዱ የቋንቋ ትምህርት ያስፈልጋል። ይህም የቋንቋ ክሂሎችን አደራጅቶ በአግባቡ ማስተማር የሚያስችል የአቀራረብ ስልት መርጦ ተግባራዊ ማድረግ ይጠይቃል። ማንበብና መፃፍ በክፍል ውስጥ ማስተማር የቃላትን አነባብ ፣ የተዋጣለት የንግግርና የሐሳብ አገላለፅን፣ ጥርት ያለ የአነባበብ ድምፀትን ፣ ሐሳብን ከጽሑፍ እንዲረዱ የማድረግ ሁኔታዎችን ሁሉ ሊያጠቃልል እንደሚችል Nuttall (1982 ) ይገልፃሉ።

ሞገስ(1999) ባደረገው ጥናት Baeydgew(2003)ዋቢ በመጥቀስ እንደገለፀው በ1950ዎቹ እና በ1960ዎቹ አመታት ማንበብና መፃፍ በሙያ ተግባር ሥረአት ትምህርት አቀራረብ እንደ ተለያዩ አላባውያን ተደርገው ይወሰዱ ነበር። በማንበብና በመፃፍ ትስስር ላይ ጥናትና ምርምር ማካሄድ የተለመደ አልነበረም ።በተጨማሪም በ1970ዎቹና በ1980ዎቹ አመታት ላይ ግን በሁለቱ ክሂሎች መካከል ያለውን ዝምድና ለማጥናት ጥረት ተደርጓዋል።ምርምሮቹ አንብቦ የመረዳትና የመፃህፍ ክሂሎች በውህደት ከቀረቡና በልምምድ ከተተገበሩ ለክህሎቹ መጎልበት ጥሩ ሊሆን እንደሚችል ሞገስ(1999) ይገልፃል።

ተማሪዎች በማንበብ ወይም በመፀሀፍ ተግባር በተገቢው መንገድ በቋንቋ የመገልገል ችሎታ ካለ በሌላኛው ተግባርም በብቃት መጠቀም ይችላሉGary(1995 )፡፡ በመሆኑም ማንበብና መፃፍ እርስ በእርሳቸው ተሳስረውና ተደጋግፈው ሊከወኑ እንደሚችሉ ይታሰባል፡፡ አንደኛው ተግባር መፃፍ ካለ ሌላኛው ተግባር ማንበብ ሊኖር ይችላል፡፡ ሁለቱም በአንድ አይነት ተግባር የሚከወኑ መሆናቸው በአንድና በተመሳሳይ ጊዜ ተግባራዊ ሊሆኑይችላሉ፡፡በሌሎች አገሮች በዘርፉ ጥናት ያደረጉ ተመራማሪዎች በማንበብና በመፃፍ ክሂሎች መካከል ጥብቅ ትስስር መኖሩንና በቅንጅት ቢቀርቡ የተሻለ እንደሆነ ያሥረዳሉHary(1996) ፡፡ በመሆኑም ሁለቱን ክሂሎች ከትስስራቸው አንፃር በቅንጅት ማስተማር ክሂሎችን በማጎልበት ረገድ ጉልህ ሚና ሊኖረው ይችላል ቢባል ምክንያታዊ ሊሆን እንደሚችልም ያስገነዝባሉ፡፡ Byrn (1981) በክፍል ውስጥ የቋንቋ ክሂሎችን ትኩረት በመስጠት አቀናጅቶ ማቅረብ ያለው ጠቀሜታ እንደሚከተለው ጠቅሰዋል፡፡

ቋንቋውን ተፈጥሯዊ በሆነ መቼት ለመማር አጋጣሚን ይፈጥራል፡፡

- ✓ ተማሪዎች በጥንድና በቡድን ሆነው የተለያዩ ተግባራትን እንዲሰሩ ያበረታታል፡፡
- ✓ ከክፍል ውስጥምሆነ ከክፍል ውጭተማሪዎች ትርጉም ያለው ስራና እንቅስቃሴ እንዲያደርጉ ያበረታታል፡፡
- ✓ ነባራዊነት ያለው ቋንቋ እንዲጠቀሙ ያግዛል፡፡
- ✓ ትምህርቱን ያፋጥናል፡፡
- ✓ በመማር ማስተማር ሂደቱ ላይ የተማሪዎቹን ተነሳሽነትና ተሳትፎ ይጨምራል፡፡

ነገር ግን በ9ኛለ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የክሂሎቹ አቀራረብ ከዚህ የተለየ ይመስላል፡፡ ለዚህም ከመርሀ ትምህርቱ አወቃቀር ጀምሮ እስከ ክፍል ውስጥ ትግበራው ድረስ ክሂሎቹን በማስተማር ረገድ ተግባራዊ እየተደረገ ያለውን ለማወቅ ጥረት ይጠይቃል፡፡ አሁን እየተሰራበት ባለው የ9ኛ ክፍል ስረዓተ ትምህርት እና የመማሪያ መፀሀፍ ላይ ክሂሎችን በተናጠል ለማስተማር በሚያስችል መልኩ የተዘጋጀና እየተሰራባቸውም እንዳለ ይታወቃል፡፡

አትክሊቲ( 1998) ለሁለተኛ ድግሪ መመረቂያ ጽሁፍ ባደረገው ጥናት የቋንቋ ክሂሎች አቀናጅቶ አማርኛ የማስተማሩን ዘዴ አተገባበር ፍተሻ  እድርጋል፡፡ በመሆኑም የማንበብና የመፀሀፍ ክሂሎች አቀራረብ  በመማሪያ መፀሀፍ አዘገጃጀትና አተገባበር በተናጥል እንደሆነ ገልፀዋል፡፡ እንዲሁም አበበች (2002) አና ሞገስ (1999) ባደረጉት ጥናት በአገራችን ሁለተኛ ደረጃ የትምህርት እርከን የማንበብ እና የመፃፍ ክሂሎች በቅንጅት የሚቀርቡበት አግባብ

ትኩረት የገኘ አይመስልም፡፡ ከዚህም ሌላ አጥኝዋ ለ10 አመት የአማርኛ ቋንቋ ስታስተምር ክሂሎቹን ታስቦበትና ታቅዶ በቅንጅት የሚቀርብበት ሁኔታ እንዳልነበረ ታዝባለች፡፡ ከዚህ በመነሳት የችግሩን መንስኤ ለመረዳት የገደባኖ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ9ኛለ ክፍል የቋንቋ ትምህርት ዋና አላማ አራቱን የቋንቋ ክሂሎች ማዳበር እንደሆነ ይታሰባል፡፡ከዚህም የተነሳ የማንበብና የመፀሀፍ ክሂል ትኩረት ተሰጥቷቸው በቅንጅት መቅረብ አለመቅረባቸውን ፤ ከቀረበ ደግሞ የአተገባበር ስልታቸውን መፈተሽ የዚህ ጥናት ትኩረት ነው፡፡

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

የቋንቋ ትምህርት ዋና አላማ አራቱን የቋንቋ ክሂሎች ማዳበር እንደሆነ ይታሰባል፡፡ነገር ግን በቁጥር አራት ይባሉ እንጂ በመማር ማስተማሩ ተግባር ስንገባ አንዱ ከሌላው ጋር የጠበቀ ቁርኝት ያላቸው ናቸው፡፡ ስለዚህ በስለመፃፍ ስናስተምር ስለማንበብ አብረን እናነሳለን፡፡

አጥኝዋ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለአስር አመት በአማርኛ ቋንቋ መምህርነት አገልግላለች በዚህ ጊዜያት የማንበብና በመፃሀፍ ክሂል ለተማሪዎች በትናጥል እየቀረበ እንዳለ ታዝባለች፡፡ በሌላ በኩል በማንበብና በመፃሀፍ ክሂል የተደረጉ ጥንቶች ሞገስ (1999) እና እሸቱ (2003) ክለሳ እንደሚያሳየው የሁለቱ ክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ ችግር እንዳለበት አመልክተዋል፡፡ ከችግሮቹ መካከል ለአብነት ያህል የማንበብና የመፀፍ ክሂልን ለማስተማር በመማሪያ መፃሀፍቱ ውስጥ የቀረቡት ይዘቶችና ክንውኖች ፤ የማስተማሪያ ትግበራ ተማሪውን የሚያበረታታ ሆኖ አለመቅረቡ ፤ በመማሪያ መፃሀፍት ውስጥ የተካተቱት መልመጃዎች አላማውን ለማሳካት የሚያስችሉ አለመሆናቸውን በጥናታቸው ውጤት ገልፀዋል፡፡

ከላይ የቀረቡት መረጃዎች ሲቃኙ የማንበብና የመፃሀፍ ክሂሎችን በቅንጅት ለማስተማር የተዘጋጁ አይመስልም፡፡ ስለዚህ በ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት የክሂሎችን ትስስርና መደጋገፍ መሰረት በማድረግ በተናጥል ወይስ በቅንጅት ማስተማር የሚለውን መለየት ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ በመነሳት የማንበብና የመፃፈፍ ክሂሎችን አቀናጅቶ በማስተማር ክሂሎችን በማጎልበት ረገድ ያለውን ሚና የሚጠይቅ በመሆኑ የዚህ ጥናት መነሻ ሆኗል፡፡

## 1.3 የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄዎች

ሀ/ የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን በማቀናጀት የማስተማር ልምምድ አንብቦ የመረዳትና የመፃፍ ችሎታን ለማሻሻል ይረዳ ይሆን?

ለ/ አንብቦ ይመረዳና መፃፍ ክሂሎችን በማቀናጀት ማስተማር ይቻላል?

ሐ/ የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን ትስስርና መድጋግፍ ምን ያህል ነው?

## 1.4 የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በጉራጌ ዞን በገደባኖ ጉታዘር ወለኔ ወረዳ በገደባኖ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን አቀናጅቶ ማስተመር ክህሂሎችን ለማሻሻል ያለውን ሚና መተንተን ሲሆን ጥናቱ የሚከተሉት ዝርዝር አላማዎች ይኖሩታ ፡-

ሀ/የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን በቅንጅት የማስተማር ልምምድ አንብቦ የመረዳትና የመፃፍ ችሎታን ለማሻሻል ያለውን ሚና መተንተን፡፡

ለ/ የማንበብና የመፃፍ ክሂሎች ትስስርና መደጋገፍ ለይቶ መፍትሸ፡፡

ሐ/ አንብቦ የምረዳትና የመፃፍ ክሂሎችን በቅንጅት ማስተማር እንደሚቻል ለይቶ ማሳየት፡፡

## 1.5 የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በክፍል ውስጥ የማንበብና የመፃህፍ ክሂልን አቀናጅተው ያስተምራሉ ካስተማሩስ አቀራረባቸው ምን ይመስላል የሚለውን በመፈተሸ ለመረዳት ተችሏል፡፡ስለሆነም ይህ ጥናት  የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል የሚል እምነት አለ፡፡

- መምህራንና ተማሪዎች የማንበብና የመፃህፍ ክሂሎች በቅንጅት መቅረባቸው ያለውን ጠቀሜታ ተገንዝበው የመማር ማስተማር ዘዴን በመቃኘት ለማስተካከል የሚያስችሉ አማራጮችን ያገኙበታል፡፡
- የአማርኛ ቋንቋ የመማሪያ ማስተማሪያ የመምህሩን መምሪያ እና የመርሀ ትምህርቱን መፃህፍት የሚያዘጋጁ የትምህርትባለሙያዎች በተማሪው የመማሪያ መፀህፍት ውስጥ

መካተት ስለሚገባቸው የማንበብና የመፃፍ ክሂልን የሚያዳብሩ መልመጃዎች ቅንጅታዊ አቀራረብ  የማስተማሪያ ዘዴ ለመጠቀም ፍንጭ ይሰጣሉ፡፡

- ከዚህ ጥናት ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ርዕሶች ወደፊት ለሚሰሩ ጥናታዊ ጽሁፎች እንደ መረጃ ምንጭነት ሊያገለግል ይችላል፡፡
- መህምህራን የሚያስለጥኑ ኮሌጆችና ዩኒቨርሲዎች ለማንበብና ለመፃፍ ክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ ትኩረት ሰጥተው ትምህርት እንዲስጡ ያመለክታል፡፡

## 1.6 የጥናቱ ወሰን

ከቦታ አንፃር በጉራጌ ዞን በገደባኖ ጉታዘር ወለኔ ወረዳ ነው፡፡ በዚህ ወረዳ ውስጥ 6ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ይገኛሉ፡፡ ከነዚህም ትምህርትቤቶች ውስጥ ጥናቱ ትኩረት ያደረገው በገደባኖ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ9ኛ‹‹ለ›› ክፍል ተማሪዎችን በመምረጥ ነው፡፡ የጥናቱ ትኩረት የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን አቀናጅቶ  ረገድ ባለው  ጠቀሜታ  ላይ ነው፡፡ ስለዚህ የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን አቀናጅቶ ማስተማር ከሚመለከቱ ጉዳዮች በስተቀር ሌላ ዝርዝር የክፍል ትምህርት አሰጣጥ ላይ አያተኩርም፡፡ እንዲሁም ከተጠቀሰው የክፍል ደረጃም ሆነ ትምህርት ቤት  ውጪ የጥናቱ ትኩረት አይደለም፡፡

ጥናቱ የክሂሎችን ትስስር እስከ ምን ድረስ እንደሆነ ፈትሾ ክሂሎችን በቅንጅት ወይስ በተናጥል ማስተማር የተሻለውን መለየት ከጥናቱ ይጠበቃል፡፡ በመሆኑም መመሪያዎችን በመከተል ለአንድ ወር ተግባራዊ ሙከራ በማድረግ ክሂሎችን በቅንጅት በማስተማርና በማለማመድ የሚኖረውን ጠቀሜታ ማሳየት ነው፡፡

## 1.7 የጥናቱ ውስንነት

ይህ ጥናት ትኩረት የሚያድርገው የማንበብና የመፃፍ ክህሎችን አቅናጅቶ ማስተማር ክህሎችን ለማሻሻል ያልው ሚናትንትና ሲሆን ልጥናቱ የሚያስፍልትን መረጃዎች ለመሰብስብ የተወሰኑ ተግዳሮቶች አጋጥመዋል፡፡ለዚህ ጥናት መሳካት የተሰበሰቡት መረጃዎች አብዛኛዎቹ የተወሰዱት ከተማሪዎችና ከመምህራን እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ይሁን እንጅ ተማሪዎች መረጃውን ለመስጠት ፍቃስኛ አለመሆንና በትምህርት ስዓት አለመገኘት ፡፡ በተጨማሪምብ መረጃ ሰጭ መምህራን ለቃለ መጠይቁ ፍቃድኛ ቢሆኑም ቀጠሮ ማብዛትና በተባለበት ስአት አለመገኘት ነበር፡፡ይሁን እንጅ አጥኝዋ እነዚህን ችግሮች ለመፍታት መምህራን የሚመቻቸውን ሰአት በመጠበቅ ፣

ለተማሪዎች የጥናቱን አላማ በማስገንዘብ ማሳመንና ያልተገኙትን ተማሪዎች ለይቴ በማስተማር ችግሮቹን በመፍታት መረጃዎችን መሰብሰብ ተችሏል፡፡

## 1.8 የፅንሰ ሀሳቦች አጠቃቀ ምብያኔ

1. <u>የአንብቦ መረዳት ችሎታ፡-</u> (Reading comprehension ability) ተማሪዎች በራሳቸው ምርምርም ሆነ ለትምህርት የቀረበላቸውን ምንባብ መልዕክት መርምረው፣ገምግመው እና አመዛዝነው ለመረዳት ያላቸውን ችሎታ ለመለካትየገባ ስያሜ ነው፡፡ ከራሳቸው ማህበራዊ ህይወትም ጋር በማነፃፀር የሚስማሙባቸውንና የማይስማሙባቸውን ያንፀባርቃሉ

2. <u>የመፀሀፍ ክሂል</u>፡-(writing skill) ጅምር ሀሳብን በመጨረስ የሰዋሰው ሥርዓቱን የጠበቀና ትርጉም ያለው የመፀሀፍ ሂደት ያከናውናሉ ፡፡ተማሪዎች የቀረበላቸውን መፀሀፍት ዋናዋና ሃሳቦችን በመንቀስ አሳጥረው ይፅፋሉ፡፡ ከመፅሀፍ ለወጡ አዳዲስ ቃላትና ፍቻቸውን ከመጻሀፍ ይፈልጋሉ፡፡

3. <u>አንብቦ መረዳትና የመፀሀፍ ክሂሎች ቅንጅት</u>፡- (Reading and writing connections) ሁለቱን ክሂሎች የለምንም ክፍተት በትስስራቸውና በዝምድናቸው ተመስርቶና አቀናጅቶ የማቅረብ ሂደት ነው፡፡ ስለዚህ ሂደታዊ በሆነ መልኩ እያነበቡ የሚፅፉበት እየፃፍ የሚያነቡበት ሂደት ነው፡፡

# ምዕራፍ ሁለት
# ክለሳ ድርሳናት

## 2.1 የቋንቋ ክሂሎትና የይዘት ምንነት

በማንኛውም ደረጃ የሚሰጥ የቋንቋ ትምህርት ዋና አላማ አራቱንም የቋንቋ ክሂሎች በሚገባ ተክነው በትክክል መገልገል እንዲችሉ ማድረግ ነው፡፡ እንዲሁም ተማሪዎቹ የስነ-ጽሁፍና የስነልሳን እውቀት እንዲኖራቸው ማድረግ ሌላው የቋንቋ ትምህርት አላማ ነው፡፡ ከቋንቋ ትምህርት አላማዎች መካከል ቀዳሚው የቋንቋ ክሂሎችን ብቃት ማሳደግ መሆኑ ቀደም ሲል ለመግለፅ ተሞክሯል፡፡ ቋንቋን የመማር ማስተማር ሲታሰብ የተለያዩ የማስተማሪያ ዘዴዎችና ስልቶች አብረው ይነሳሉ፡፡ የቋንቋ ትምህርት አላማ ግቡን ሊመታ የሚችለውም አራቱ ክሂሎች በተገቢ ሁኔታ ተቀናጅተው መቅረብ ሲችሉ ነው፡፡ በመሆኑም ይህ ጥናት ትኩረት የሚያደርገው በቋንቋ ትምህርት ቅንጅታዊ አቀራረብ ላይ በመሆኑ የቅንጅታዊ አቀራረብን ምንነት ፤ ክሂሎችን በቅንጅት የማስተማር ጠቀሜታ ፤የማስተማሪያ ስልቶችን ከዚህ በመቀጠል በዝርዝር እንደሚከተለው ለመቃኘት ተሞክሯል፡፡

### 2.1 የቋንቋ ክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ ምንነት

ቋንቋን የመማር ማስተማር ሂደት ሲታሰብ የተለያዩ የማስተማሪያ ዘዴዎችና ስልቶች አብረው ይነሳሉ፡፡ለምሳሌ የቋንቋ ትምህርት በሚፈለገው ደረጃ ግቡን እንዲመታ ያግዛሉ ተብለው ከሚጠቀሱት አቀራረቦች ውስጥ አንዱ የቋንቋ ክሂሎችን አቀናጅቶ ማቅረብ ነው Little Wood (1981) ይገልፃሉ፡፡ በቋንቋ ትምህርት ከሚቀረፁት ዓበይት ዓላማዎች ውስጥ አንዱ አራቱን የቋንቋ ክሂሎች ማዳበርና ማጎልበት እንደመሆኑ መጠን ከቅርብ አመታት ወዲህ በቋንቋ ክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ ላይ ከፍተኛ ትኩረት እየተደረገ መምጣቱን Byrne (1981) ገልፀዋል፡፡ የቋንቋ ክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ ምንነትን አስመልክተው ምሁራን እንደሚከተለው ገልጸዋል፡፡

እውናዊውን የቋንቋ አጠቃቀም ስንመለከት ንግግር በማዳመጥ ጽህፈት በንባብ ወዘተ የሚታገዝ ነው፡፡ በክፍል ውስጥ የሚሰጠው የቋንቋ ትምህርት አላማም ተማሪዎች የታላሚውን ቋንቋ አጠቃቀም በትክክለኛው መንገድ እንዲጠቀሙ ማስቻል በመሆኑ የቋንቋ ክሂሎችን አቀናጅቶ ማቅረቡ ተግባቦታዊ ብቃትን የማጎልበት አስተዋጽኦ ከፍ ያለ ነው (Gilbert: 1982) በማለት ገልፀዋል፡፡

የቋንቋ ክሂሎችን አቀራረብ ስናስብ በአንድ መማሪያ ክፍል አንድን የቋንቋ ክሂል ነጥሎ ማቅረብ አስቸጋሪ ነው፡፡ የንባብ ክሂልን ለማስተማር ሲታለም የመፃፍ ክሂል አብሮ መምጣቱ አይቀርም፡ ፡እንደዚህ ዓይነቱን ትስስር የቋንቋ ባህሪ የሚፈጥረው ቢሆንም በቋንቋ ትምህርት ብቻውን በቂ አይደለም፡፡ይህን ሀሳብ በተመለከተ Byren (1981) እንደሚከተለው ያብራሩታል፡፡የቋንቋ ክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ ድንገት የሚፈጠረውን ቅንጅት ሳይሆን ሆን ተብሎና ታቅዶበት ተማሪዎቹን በልምምድ ብቁና የቋንቋው ተጠቃሚ እንዲሆኑ የሚያግዝ ሂደት ነው፡፡የክሂሎች ቅንጅታዊ አተገባበር ከክፍለ ጊዜው የትምህርት ዕቅድ ጋር በሚስማማ መልኩ ትኩረት ሊደረግበት የሚገባውን ክሂል በዋናነት ትኩረት እንዲቸረው ለማድረግ ያስችላል፡፡አክለውም የቋንቋ ክሂሎች እርስ በእርስ ተሳስረው አንዱ ሲነሳ አንዱ ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ሌሎች ክሂሎችን በማስከተል ተዋህደው የሚቀርቡበት የቋንቋ ክሂሎችን የማስተማሪያ ሂደት ነው በማለት አብራርተዋል፡፡እንዲሁም Rivers(1981) በበኩላቸው ተማሪዎች የመጻፍ ክሂልን በሚማሩበት ጊዜ ሌሎችንም ክሂሎች አብረው እንዲያዳብሩ ለምሳሌ ተማሪዎች በሳል ድርሰት እንዲጽፉ ከተፈለገ በሌሎች የቋንቋ ክሂሎች ያላቸውን ችሎታ መዳበር እንዳለበት ያስረዳሉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በጣም ጥሩ የሆነ አንብቦ የመረዳት ክህሎት የመናገርና የማዳመጥ ብቃት ካላቸው ጥሩ ጽሁፍ እንደሚጽፉ የታመነ ነው፡፡በመሆኑም ጽህፈትን ስናስተምር ሌሎችም አብረው እንዲመጡ ማድረግ አስፈላጊ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡ከምሁሩ ሃሳብ እንደምንረዳው የቋንቋ ክሂሎችን አቀናጅቶ ማስተማር ማለት በአንድ ክፍለ ጊዜ ውስጥ ከአንድ በላይ የሆኑ ክሂሎችን በማጣመር አንዱ ሲነሳ ሌሎቹ አብረው እንዲነሱ ወይም እንዲተገበሩ የሚደረግበት ዘዴ መሆኑን ነው፡፡

### 2.2.2 የቋንቋ ክሂሎችን አቀናጅቶ የማቅረብ ጠቀሜታ

Oxford (2001) የቋንቋ ክሂሎች ተናጥላዊ አቀራረብ በጥንታዊው የቋንቋ ትምህርት የተማሪዎችን የተግባቦት ብቃት ከመገደብ ባለፈ በሌሎችም ትምህርታቸው ውጤታማ እንዳይሆኑ ያደርግ እንደነበር በመግለጽ ለዚህም እንደምክንያት የገለጹት ስርዓተ ትምህርትና መርሀ ትምህርት የሚቀርጹ ባለሙያዎች የቋንቋ ትምህርቱን በቋንቋ ቅርጽ ላይ እንዲያተኩር በማድረግ የተነጣጠሉ የቋንቋ ክሂሎችን ማቅረባቸው ነው፡፡በዚህ ሁኔታ የተማሩ ተማሪዎች ሊኖራቸውየ ሚችለው የቋንቋ እውቀት ደግሞ ስለ ቋንቋው ከማወቅ ባለፈ በታላሚው ቋንቋ የመጠቀም ችሎታቸውን እንዳያጎለብቱና ተግባቦታዊ ብቃታቸው በተገቢው መጠን እና ዳይጨምር ትልቅ እንቅፋት ሆኗል በማለት ያብራራሉ፡፡እንዲሁምMcDonough and Shaw

(1992) በበኩላቸው የቋንቋ ክሂሎችን በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ አቀናጅቶ ማቅረብ በርካታ ጠቀሜታዎች አሉት፡፡ዋና ዋናዎቹ የተማሪውን ፍላጎት ማነሳሳት፣የተማሪውን ግንዛቤ ማሳደግና የመማር ማስተማሩን ሂደት ማፋጠን መሆናቸውን አስረድተዋል፡፡

ከምሁራን ሀሳብ እንደምንረዳው የቋንቋ ክሂሎችን ነጣጥሎ ከማቅረብ ይልቅ አቀናጅቶ ማቅረቡ ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታዎች እንዳሉት ነው፡፡በየትኛውም ደረጃ የሚሰጥ የቋንቋ ትምህርት ዋና አላማ ተማሪዎቹ አራቱን የቋንቋ ክሂሎች በሚገባ ተክነው መገልገል እንዲችሉ ማድረግ ነው፡፡ ይሁን እንጅ የዚህ ጥናት ዋና ትኩረት ከቋንቋ ክሂሎች ውስጥ በአንብቦ መረዳትና በመጻፍ ክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ ላይ ብቻ ይሆናል፡፡የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ከሚሰጥባቸው ዓላማዎች ውስጥ "የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ክሂልን ማዳበር" የሚል ይጠቀሳል፡፡ይህ አላማ ከግብ ሊደርስ የሚችለው የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት እና የመጻፍ ችሎታን ያዳብራሉ ተብለው የሚካተቱ ይዘቶች በተገቢው መንገድ በመፃሀፉ ውስጥ ተቀናጅተው ሲቀርቡ ነው፡፡ተማሪዎች በታቀደው ይዘት ተጠቅመው በተደጋጋሚ መለማመድ ሲችሉ የታሰበው ግብ ሊገኝ ይችላል፡፡በመሆኑም ከዚህ በላይ ከቀረቡት ቅኝቶች በመነሳት አጥኝዋ ክሂሎች በውህደት ቢቀርቡ የተሻለ እንደሆነ ታምናለች፡፡ስለሆነም በመጀመሪያ ስለ ክሂሎቹ ምንነትና አስፈላጊነት መመልከቱ አስፈላጊ ይሆናል፡፡በዚህም መሰረት ስለአንብቦ መረዳት ምንነት፣የንባብ ትምህርት አስፈላጊነት፣ስለ መጻፍ ክሂል ምንነትና የመጽሀፍ ክሂል ትምህርት አስፈላጊነትን በተመለከተ እንደሚከተለው ለመቃኘት ተሞክሯል፡

### 2.2.3 የቋንቋ ክሂሎችን አቀናጅቶ የማቅረቢያ ዘዴዎች

በመማር ማስተማር ሂደት የቋንቋ ክሂሎችን አዋህዶ ለማቅረብ የሚያስችሉ የተለያ ዩዘዴዎች እንዳሉ ምሁራን ይገልጻሉ፡፡ከዚህ በመቀጠል ጥቂቶችን ለማየት ተሞክሯል፡፡ Celece-Muricia (1991) እና Oxford (2001) የቋንቋ ክሂሎችን አቀናጅቶ ለማቅረብ ስርዓተ ትምህርትና መርሀ ትምህርት ቀራጮች መጽሀፍ አዘጋጆችና መምህራን የተለያዩ ዘዴዎችን መጠቀም እንዳለባቸው ገልጸው በተለይም ይዘትን መሰረት ያደረገ ተግባር ተኮር የሆነ ወይም ሁሉንም ዘዴዎች ያዋሀደ ዘዴን ተጠቅመው ክሂሎችን በተቀናጀ መልኩ ማቅረብ እንደሚችሉ አስረድተዋል፡፡ከዚህ በመቀጠል ስለ ይዘት ተኮር እና ስለተግባር ተኮር ቅንጅታዊ የክሂሎች አቀራረብ እንመለከታለን፡
፡

**ይዘት ተኮር ቅንጅታዊ የክሂሎች አቀራረብ**፦በዋናነት ይዘት ላይ ትኩረት ያደረገ የቋንቋ ትምህርት ማቅረቢያ ዘዴ ነው፡፡በዚህም አማካኝነት ተማሪዎቹ የትምህርቱን ይዘት እየተማሩ የቋንቋ ችሎታቸውን ያዳብራሉ፡፡Celce-muricia (1991) ይዘት ተኮር ዘዴ ትኩረት የሚያደርገው በቋንቋ ቅርጽ ላይ ሳይሆን ተማሪዎች ርዕሰ ጉዳዩን መሰረት በማድረግ እንዲረዱት የሚያደርግ አቀራረብ ነው ሲሉ Atkins etal (1996) በበኩላቸው የቋንቋ ትምህርት ዋና ዓላማ ተማሩዎች ክሂሎችን አዋህደው እንዲጠቀሙና ተግባቦታዊ ብቃታቸውን እንዲያጎለብቱ ከማድረግም በተጨማሪ የሌሎች የትምህርት ዓይነቶችን ይዘቶች በጥልቀት እንዲገነዘቡ ማስቻልም ነው ይላሉ፡፡ከዚህ ሀሳብ እንደምንረዳው ይዘት ተኮር የክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ ዘዴ ዋና ዓላማ ቋንቋን በይዘት ማስተማር በመሆኑ የተማሪዎችን የቋንቋ ችሎታ ከማዳበር ባሻገር የተለያዩ ይዘቶችን በጥልቀት እንዲያውቁ የሚያደርግ ዘዴ መሆኑን ነው፡፡

**ተግባር ተኮር ቅንጅታዊ የክሂሎች አቀራርብ** የሚያተኩረው ደግሞ ተማሪዎች ተግባቦታዊ በሆነ ተግባር ላይ እየተሳተፉ ቋንቋውን ለመማር የሚያስችላቸው ዘዴ ነው፡፡ይህን ዘዴ በተመለከተ ምሁራን እንደሚከተለው ያብራራሉ፡፡ተግባር ተኮር የክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ ተማሪዎች ተግባቦታዊ በሆኑ የቋንቋ ተግባራት የሚሳተፉበትና ተግባቦታዊ የቋንቋ አጠቃቀምን የሚያዳብሩበትን ተግባር የሚያከናውኑበት ዘዴ መሆኑን (Oxford፡2001) ያስረዳሉ፡፡

ከምሁራን ሀሳብ መረዳት እንደሚቻለው ተግባር ተኮር ዘዴ ተማሪዎች በጥንድና በቡድን በተለያዩ ተግባራትና ክንውኖች እየተሳተፉ የቋንቋ ክሂሎችን አቀናጅተው እንዲጠቀሙባቸው የሚያደርግ ዘዴ መሆኑን ነው፡፡ይህን ዘዴ ተግባራዊ ማድረግ ተማሪዎች የቋንቋ አጠቃቀምን እየተገነዘቡ ተግባቦትን የሚያዳብሩበትና መረዳታቸውን የሚያጎለብቱበት ዘዴ መሆኑን ነው፡፡ ቀጥሎ የቋንቋ ክሂሎችን አቀናጅቶ ማቅረብ ያለውን ዘዴ እናያለን፡፡

## 2.3. የአንብቦ መረዳት ምንነት

አብዛኞቻችን አንብቦ መረዳት ማለት አንድን ምንባብን ካነበብን በኋላ ጥያቄዎችን መመለስ መቻል ነው ብለን ልናስብ እንችላለን፡፡ይሁን እንጅ እንደዚህ ከተረዳን ትክክለኛ የሆነ ግንዛቤ አለመሆኑን ማወቅ ይኖርብናል፡፡የአንብቦ መረዳትን ምንነት በተመለከተ ምሁራን የየራሳቸውን ብያኔ ሰጥተዋል፡፡ጥቂቶችን እንደሚከተለው ለማየት ተሞክሯል፡፡

አንብቦ መረዳት ማለት ከአንድ ጽሁፍ ውስጥ የሚፈለገውን መረጃ ለይቶ በማውጣት ጽሁፍን የመገንዘብ ሂደት ነው፡፡አንባቢው በተገቢው ፍጥነት የሚፈለገውን መረጃ የሚለይበት ተራ ያልሆነ ጥልቅ ግንዛቤን የሚመለከት ነው Williams (1990)፡፡ Grellet (1981) በበኩላቸው አንብቦመ ረዳት ማለት ከሚነበበው ጽሁፍ ውስጥ አንባቢው ወይም ተማሪው እስከሚቻለው ድረስ በብቃት የሚፈለገውን መረጃ ማውጣት መቻል ነው በማለት ገልጸዋል፡፡

ከምሁራኑ ሃሳብ እንደምንረዳው አንድተማሪ ወይም አንባቢ የሚያነብበትን አላማ አውቆ ዓላማውን ለማሳካት የሚያስችለውን መረጃ ካገኘና ለይቶ ካወጣ አንብቦ ተረድቷል ማለት ነው፡፡ በመሆኑም አንብቦ መረዳት ማለት የሚፈለገውን መረጃ ከአንድ ጽሁፍ ውስጥ ለይቶ ማውጣት ሲሆን አጠቃላይ የጽሁፉን መልዕክት የመገንዘብ ሂደት ነው፡፡ስለ አንብቦመረዳት ምንነት ሲነሳ የተለያዩ ክሂሎች ጥምረት መሆኑን ምሁራን ይገልጻሉ፡፡Durkin (1977) እና Grellet (1991) እንደሚያስረዱት አንብቦ መረዳት የምንባብን ሃሳብ የመገንዘብ፣የማብራራት፣ የመከለስዕንሰ ሃሳቦችን የማዛመድ፣አንድነትና ልዩነቶችን የመመርመር፣የመከራከርና የመወያየት ችሎታዎች ማንጸባረቂያም በመሆኑ ከመጻፍ፣ከማዳመጥና ከመናገር ክሂሎች ጋር ተነጣጥሎ ሊታይ አይችልም፡፡ይህም ሲባል ስለንባብ የቀረበ ጽሁፍን በሚገባ ካነበቡ በኋላ በጽሁፉ ሀሳብ ዙሪያ መከራከርና መወያየት ከንግግር፣የጽሁፉን ሀሳብ መከለስና ማስታወሻ መያዝ ከጽሁፍ እንዲሁም ጽሁፉን ከማደመጥ ነገር ጋር ከዜናና ከሌሎች ዘገባዎች መለየት ከማዳመጥ ክሂል ጋር የተሳሰረ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡ጠቅለል ባለ መንገድ አንብቦ መረዳት አንባቢ የፀሀፊውን ሃሳብና አመለካከት ለመረዳት ሲል ከጽሁፍ ያገኘውን ሃሳብ ከቀደመ እውቀቱ ጋር እያገናዘበ የራሱን አዲስ አመለካከት የሚንጸባረቅበት ሂደት ነው ማለት ይቻላል፡፡

### 2.3.1 የንባብ ትምህርት አስፈላጊነት

አሁን ባለንበትም ሆነ በቀደምት ጊዜያት ንባብ ቋሚ ከሆነው መረጃ ማለትም ከጽህፈት እውቀት የምንቀስምበት ብቸኛ ክሂል እንደሆነ ይታመናል፡፡የንባብ ትምህርትን አስፈላጊነት አስመልክተው Williams (1990)ሲያስረዱ አንድን ጽሁፍ አንብቦ መልዕክቱን የመረዳት ችሎታን ለማዳበር፣በማንበብ እውቀትን ለመገብየት እንዲሁም ከተለያዩ የንባብ ባህሪያት ጋር ለማስተዋወቅና የንባብ ችሎታን ለማጎልበት የንባብ ትምህርት አስፈላጊ መሆኑን ይገልጻሉ፡፡Mc Donough and Shaw (1993) ሲገልጹንባብመረጃለማግኘት፣አንድ ነገር መቼና የት እንደተከናወነ ለማወቅ እንዲሁም በጋዜጦች፣በመጽሄቶች የሚቀርቡትን ሀሳቦች ለመረዳትና ለመዝናናት ወይም ለመደሰት አስፈላጊ ነው በማለት አስረድተዋል፡፡

ከምሁራኑ ሀሳብ እንደምንረዳው ንባብ ለትምህርት ብቻ ሳይሆን ለምናከናውናቸው ተግባራት መረጃ በመስጠት፣ለመዝናናትና ታሪክን ለማወቅ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳለው እንረዳለን፡፡ በመሆኑም ይህ ክሂል እንዲዳብር የተለያዩ ተግባራትን ማከናወን አስፈላጊ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ Lindsay and Knight (2006) ሲያስረዱ የንባብን ክሂል ለማዳበር የምናዘጋጃቸው ጽሁፎች የሚከተሉትን ሶስት ነጥቦች ከግምት ውስጥ ያስገቡ መሆን አለባቸው፡እነሱም፡-

**ርዕስ ጉዳይ፡-**የምንመርጠው ጽሁፍ የተማሪዎቻችንን ፍላጐት ያማከለ መሆን ይኖርበታል፡፡

**ደረጃ፡-**ጽሁፉ የተማሪዎችን የእውቀትና የክፍል ደረጃ ያማከለ ሊሆን ይገባል፡፡በውስጡ የሚካተቱ ቃላት፣አረፍተነገሮች ወዘተ. ውስብስብነት ከተማሪዎች የእውቀት ደረጃ ጋር የተመጣጠነ መሆን አለበት፡፡

**የጽሁፉ ርዝመት** (መጠን)፡-የምንመርጠውን ጽሁፍ ስፋት ወይም መጠን ክፍል ውስጥ ካለን ጊዜ አንፃር የተጣጣመ መሆን አለበት፡፡ምክንያቱም ጽሁፍን ለማንበብ የሚወስድብን ጊዜ እና ከንባብ በኋላ ለሚሰሩ ተግባራት የምንሰጠው ጊዜ ከአለን አጠቃላይ ጊዜ ጋር ካልተጣጣመ ልናዳብረው የፈለግነውን የንባብ ክሂል ውጤታማ ልናደርገው አንችልም በማለት ገልፀዋል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ ከቀረበው ፅሁፍ እንደምንረዳው የንባብ ክሂልን ለማዳበር የማስተማሪያ ፅሁፎችን ትኩረት ሰጥቶ መምረጥና የተማሪዎችን የቀደመ ችሎታ ማወቅ ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለው ነው፡፡

### 2.3.2 አንብቦ የመረዳት ትምህርት አቀራረብ

የንባብ ትምህርት ሲቀርብ ተማሪዎችን ውጤታማ ለማድረግ የተለያዩ ክንዋኔዎችን ያካተተ መሆን ይኖርበታል፡፡የንባብ ትምህርት አቀራረብ ቅድመ ንባብ፣የንባብ ጊዜና ድህረ ንባብ ክንዋኔዎችን ያካተተ የትምህርት አቀራረብ እንዲሆን የመስኩ ምሁራን የሚገልጹ ሲሆን በእነዚህ አቀራረብ ማስተማር ደግሞ የተሻለ ውጤታማ መሆኑን Lindsay and Knight (2006) ገልጸዋል፡፡ቅድመ ንባብ ተግባራት፡- የምንለው ተማሪዎች ለምንባቡ የሚኖራቸውን እውቀት ከወዲሁ ለመጠቀም የሚያገለግለን ነው፡፡

የቅድመ ንባብ ተግባራት አስፈላጊነትም፡-

- ተማሪዎችን ለንባብ ለማዘጋጀት
- ተማሪዎችን በርዕሰ ጉዳዩ ዙሪያ ያላቸውን የቀደመ እውቀት ለማረጋገጥ
- የንባብ ፍላጐት እንዲኖራቸው ለማድረግ እና ሌሎችም ጠቀሜታዎች አላቸው፡፡

ቅድመ ንባብ ተግባራት በሁለት መንገድ ይካሄዳል፡፡እነሱም፡-

1. በጥያቄና መልስ መልኩ ይካሄዳል፡፡
2. ድርጊቶችን በማከናወን /ለምሳሌ፡- ዕሎች መሳል እና ችግር ፈቺ በሆኑ ጥያቄዎች ዙሪያ እንዲወያዩ በማድረግ ይካሄዳል በማለት Lindsay and Knight (2006) ገልፀዋል፡፡ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች የሚነበበውን ጽሁፍ አስመልክቶ ከንባብ በፊት የሚሰሩ በመሆናቸው የሚከተሉት ጠቀሜታዎች አሏቸው፡፡እነሱም፡-

- ✓ ተማሪዎቹ ቀድመው ስለሚዘጋጁ ወደ ዋናው ምንባብ በሚገቡበት ጊዜ ምን መስራት እንደሚጠበቅባቸው ያውቃሉ፡፡ይህም መማርን ቀላል፣ተፈጥሯዊና ትርጉማዊ ያደርገዋል፡፡
- ✓ ቅድመ ንባብ ተግባራት ተማሪዎች የጋራ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ያግዛሉ፣ልምዳቸውን፣ ሃሳባቸውንና ጽሁፉን አስመልክቶ የገመቱትን ከማንበባቸው በፊት ስለሚለዋወጡ የተሻለ ግንዛቤ ይዘው ያነባሉ፡፡
- ✓ ሰቅድመ ንባብ የመማር ክሂልን መማሪያም ነው፤ተግባራቱ ተማሪዎቹ ጽሁፍን እንዴት እንደሚያነቡ ወይም እንዴት እንደሚያቀርቡት የሚያመላክቱ በመሆናቸው ለራሳቸው የንባብ ስራ ሃላፊነት እንዳለባቸው ግንዛቤያቸውን ያጐለብትላቸዋል፡፡ተማሪዎች ስለሚያነቡት ጽሁፍ አስቀድመው በጋራ እንዲሰሩና የጋራ ግንዛቤያቸውን ይዘው እንዲያነቡ ያደርጋሉ፡፡

የመገመት ተግባራቱ በጣም ጠቃሚና አስፈላጊ ሲሆኑ ከሚነበበው ጽሁፍ ምን እንደሚጠበቅ በማመላከት ጽሁፉን የማንበብ ፍላጐትን ይጨምራል፡፡ተማሪዎች ቀድመው የገመቱትን ወይም የሚጠብቁትን ከሚያነቡት ጋር እያነፃፀሩ እንዲያነቡ ያግዛል፡፡

ሰዎች አዲስና ያልታወቀ ነገር ይፈትናቸዋል፡፡ለዚህም ቅድመ ንባብ ተግባራት በሚነበብ ጽሁፍ ውስጥ እንግዳ ነገር ወይም ችግር ሲያጋጥም እንዴት መፍታት እንደሚቻል መንገድ

ያመላክታል፡፡ቅድመ ንባብ ተግባራት የተማሪዎችን ቋንቋውን በጥልቀት የመማር ፍላጐት ይጨምራሉ፡፡ነገሮችን በጥልቀትና በስፋት የማየትና የመረዳት ችሎታን ያሳድጋሉ፡፡የንባብ ጊዜ ተግባራት፡-በዚህ የንባብ ጊዜ ተግባር ወቅት መምህራን ተማሪዎቻቸውን በንቃት ላይ የተመሰረተ ንባብ እያካሄዱ መሆናቸውን የሚቆጣጠሩበትና ተማሪዎቹ የበለጠ ለንባብ እንዲነሳሱ የሚያግዙ ተግባራትን የሚያከናውኑበት ጊዜ ነው፡፡በዚህ የንባብ ጊዜ እያነበቡ ያሉ ተማሪዎችን በርካታ ተግባራትን ማሰራት ይቻላል፡፡ነገር ግን እነዚህ ተግባራት እንደየምንባቡ ይዘትና አላማ ይለያያሉ፡፡ይህንን በተመለከተ Lindsay and Knight (2006) የንባብ ጊዜ ተግባራትን በሶስት መንገድ ገልፀዋል፡፡እነሱም፡-

- ✓ የተማሪና የመምህር ጥምረት ተግባራት
- ✓ የተማሪ ከተማሪ ጥምረት ተግባራት
- ✓ የጽሁፍ ተግባራት ናቸው በማለት ገልፀዋል፡፡

**ድህረ ንባብ ተግባራት**፡-ድህረ ንባብ ከንባብ ሂደት በኋላ የሚሰጡ ጥያቄዎች የሚሰሩበት ሂደት ነው፡፡እንዲሁም በንባብ ማጠናቀቂያ ጊዜ የሚታዩ ሲሆን የንባብ ሂደት የሚከለስበት ነው፡፡ድህረ ንባብ ተግባራት ተማሪዎች ምንባቡን ሙሉ በሙሉ መረዳታቸውን ለማረጋገጥ የምንባቡን ተዓማኒነት እንዲገመግሙ ለማበረታታት እና ከራሳቸው ገጠመኝ ጋር እንዲያያዙ ለማድረግ የሚጠቅም ነው፡፡በዚህ ደረጃ ተማሪዎቹ ከተነሱባቸው የቅድመ ንባብና በመቀጠል ምንባብ ጊዜ ከተሳተፉባቸው ጥያቄዎች በተረዷቸው ሃሳቦች መሰረት የሚመልሷቸውን ጥያቄዎች የሚያካትት ተግባራዊ ክንውንን ይይዛል፡፡በአብዛኛው የግምገማ ስራዎችን የሚይዝ ሲሆን ምንባቡን መነሻ በማድረግ ከክፍል ውጭ ካለው አለም ጋር በማዛመድ ሃሳብ እንዲሚያቀርቡባቸው የሚችሏቸው ጥያቄዎች የሚካተቱበት ነው፡፡በተጨማሪም ተማሪዎቹ ከራሳቸው የህይወት ልምድና እውቀት አኳያ የአስተሳሰብ አድማሳቸውን ተጠቅመው ሃሳብ የሚሰነዝሩበት ነው፡፡የሚዘጋጁት ጥያቄዎች ለአሳታፊነታቸው እንጂ ለውጤት ተብለው መዘጋጀት የለባቸውም፡፡

### 2.3.3 አንብቦ የመረዳት ጥያቄዎች ሲዘጋጁ ትኩረት የሚደረግባቸው ነጥቦች

አንብቦ የመረዳት ጥያቄዎች ከምንባብ ቀጥሎ የሚመጡ በተነበበው ጽሁፍ ላይ መሰረት ያደረጉ እንደሆኑ Nuttal (1988) ገልጸዋል፡፡እንደ Shin (1992) ቋንቋን ለማስተማር ዓላማ ባደረገ የንባብ ክፍለ ጊዜ ተማሪዎች የሚቀርቡላቸውን የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች መመለስ

እንዲያስችላቸው መምህራን በቅድመ ንባብ ተግባራት ዳራዊ እውቀታቸውን እንዲፈትሹ ያደርጋሉ፡፡የሚዘጋጁት የቋንቋ መማሪያ መጻህፍትም ይህን የተከተሉ ናቸው፡፡

የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችም በቅድመ ንባብ ተግባር የተፈተሹ የተማሪዎችን ዳራዊ እውቀት፣ በንባብ ጊዜ የሚያዙ አጫጭር ማስታወሻዎችን ከንባብ በኋላ የሚካሄዱ ውይይቶችን የጽሁፍ ተግባራትና ሌሎች ክሂሎችን አጠቃለው የሚይዙ ናቸው፡፡ይህም ተማሪዎች መሰረታዊ የሆኑ በይዘት ላይ ያተኮሩ መልመጃዎችን እንዴት እንደሚሰሩ በመጠቆም ልምድን ያዳብርላቸዋል፡፡ በአጠቃላይ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች አንባቢ የአንድን ጽሁፍ አጠቃላይ መልዕክት ከተለያዩ አተያዮች አንጻር መገንዘብን ለመመርመር የሚዘጋጁና ክሂልን ለማዳበር የሚረዳ መንገድን የሚያሳዩ ጥያቄዎች ናቸው፡፡እነዚህ ጥያቄዎች በሚዘጋጁበት ወቅት ትኩረት ሊደረግባቸው የሚገቡ በርካታ ነጥቦች እንዳሉ የተለያዩ ምሁራን ያስረዳሉ፡፡የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች የአንባቢያንን ችሎታ በመመዘን ላይ ብቻ ያተኮሩ ሳይሆኑ አንባቢያኑ አንድን ጽሁፍ ለመረዳት በራሳቸው የሚፈጥሩትን አዳዲስ ስልት እንዲቀይሱ የሚገፋፉ መሆን እንደሚኖርባቸው የተለያዩ ምሁራን አብራርተዋል፡፡ Johnson (1982) እንደገለጹት ምንባብን መሰረት ያደረጉ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ተከታታይነት ያላቸው የመረዳትን ሁኔታ ማረጋገጫ መልመጃዎች ናቸው፡፡እነዚህ መልመጃዎች ደግሞ እንደ ጽሁፉ ባህሪ ተለዋዋጭነት ያላቸው ይሆናሉ፡፡ ከምሁራኑ ሀሳብ እንደምንረዳው የእያንዳንዱም ንባብ ባህሪ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ የራሱ የሆነ አስተዋጽኦ አለው፡፡በመሆኑም በመልመጃዎቹ ስር የሚካተቱ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ጽሁፉን ደጋግመው እንዲያነቡ የሚገፋፉ ሆነው ቢዘጋጁ ተመራጭነት ያለው መሆኑን ነው፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎች የራሳቸውን የአነባበብ ስልት ተጠቅመው ምንባቡን የመረዳት፣ የመተርጎም፣የማብራራት፣የማጠቃለል እና ሌሎች ችሎታቸውን የሚያዳብሩበት መንገድ የሚያሳይ በመሆኑ ነው፡፡የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ሲዘጋጁ ትኩረት ሊደረግባቸው ከሚገቡ በርካታ ነጥቦች መካከል በዋናነት የሚጠቀሱትን Grellet (1991) ገልጸዋል፡፡እነሱም፡- ከአጠቃላይ ጭብጥ መጀመር፣የጥያቄዎችን ስብጥር መጠበቅ፣ከልዩ ልዩ ክሂሎች ጋር ማቀናጀትና በመልመጃ ጥያቄዎችና በፈተና ጥያቄዎች መካከል ያለውን ልዩነት መገንዘብ ናቸው፡፡የዚህ ጥናት ትኩረት አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ክሂሎች የይዘት ቅንጅታዊ አቀራረብ ላይ ትኩረት ያደርጋል፡፡በመሆኑም ከዚህ በመቀጠል ስለ ጽህፈት ክሂል ምንነትና ስለ ክሂሎቹ ትስስር እንመለከታለን፡፡

## 2.4 የጽህፈት ክሂል ምንነት

ከቋንቋ ክሂሎች መካከል መፃፍ አንዱ ሲሆን የንግግር ድምጾችን በሚወክሉ ምልክቶች አማካኝነት ሀሳብን በወረቀት ላይ በማስፈር የመግባባት ተግባር ነው፡፡የክሂሉን ምንነት አስመልክተው ምሁራን የየራሳቸውን ብያኔ የሰጡ ሲሆን ከዚህ ቀጥሎ እንመለከታለን፡፡Byrne (1988) ሲገልጹ በአንድ ቋንቋ ውስጥ ያሉ የንግግር ድምጾች የየራሳቸው የሆነ ትዕምርታዊ ውክልና ይሰጣቸዋል፤ትዕምርቶቹ የቋንቋውን ሥርዓት ተከትለው ይዋሀዳሉ፡፡እነዚህ ድምፆች ትርጉም ሊሰጡ በሚችሉበት መንገድ ተቀናጅተው ይቀርባሉ ይህም ጽህፈት ይባላል በማለት አብራርተዋል፡፡አክለውም ጽህፈት ድምፅን አቀናጅቶ ቃላት መመስረት ብቻ ሳይሆን እነዚያን ቃላትም በማቀናጀት ትርጉም ያለው ዓ.ነገርን ማዋቀርን፣ዓረፊተ ነገሮችም አንቀጽንም መመሰረትን ወዘተ የሚያካትት ነው ሲሉ ገልጸውታል፡፡ ይህንኑ ሀሳብ ብዙዎቹ የመስኩ ባለሙያዎች ይጋሩታል (Harmer 1991)እና(Nunan 1988)፡፡ እንዱሁም Byrne (1991) ጽሁፍ በምንጽፍ ጊዜ ምልክቶችን እንጠቀማለን፡፡ እነዚህ ምልክቶች የሚፈጥሯቸው ፊደሎችና የፊደሎች ግንኙነት ሲሆን ከድምጹ ጋር ይገናኛሉ፡፡ ይሁን እንጂ ንግግር ከድምጽ በላይ እንደሆነ ሁሉ ጽህፈትም በግልጽ የሚታዩ ምልክቶችን ከማፍለቅ በላይ ነው ብለው በይነውታል፡፡ከላይ ከቀረቡት ብያኔዎች እንደምንረዳው ጽህፈት የንግግር ድምፆችን የሚወክሉ ትዕምርቶችን በመጠቀም ሀሳብን፣ስሜትን፣መረጃን እንዲሁም መልዕክትን ማስተላለፊያና ቀርፆ ማስቀመጫ ክሂል ነው፡፡በሚፃፍበት ወቅትም የቋንቋውን ተናጋሪዎች የቋንቋ አጠቃቀምና ሥርዓት ግንዛቤ ውስጥ ማስገባት አስፈላጊ ነው፡፡በተጨማሪም ጽህፈት እንደ ቃላዊ ክሂሎች በመልመድ ሳይሆን በመማር የሚገኝ ከመሆኑም ባሻገር ከፍተኛ ትጋትንና ጥረትን የሚጠይቅ የቋንቋ መሠረታዊ ክሂል ነው፡፡

መጻፍ የሀሳብ አቀነባበርን፣የሀሳብፍሰትን፣የቃላት አመራረጥን እና የአገላለጽ ስልትን የሚጠይቅ የቋንቋ ክሂል ነው፡፡ስለዚህ ብዙዎች እንደሚስማሙበት መጻፍ የነቃ አዕምሮ ውጤት ነው ማለት ይቻላል፡፡ሆኖም ግን የመጻፍ ክሂል በብዙዎች ዘንድ አስቸጋሪ መሆኑ ይገለጻል፡፡መጻፍ ለብዙዎች አስቸጋሪ የሚሆንበትን ምክንያት Byrne (1988) ሲያስረዱ ሶስት ምክንያቶችን ይጠቅሳሉ፡፡እነሱም;-ስነልቦናዊ ችግር፣ሰዋሰዋዊ ችግርና ግንዛቤዊ ችግር ናቸው፡፡በመቀጠል ስለ ጽህፈት ክሂል አስፈላጊነት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

## 2.5 የጽህፈት ክሂል ትምህርት አስፈላጊነት

ጽህፈት ሲዘጋጅ ከአንባቢ ጋር ተግባቦትን የሚፈጥር በመሆኑ በጥሩ ሁኔታ መዘጋጀት ይኖርበታል፡፡አስፈላጊነቱን አስመልክተው Raimes(1983) ሰዎች በጊዜና በቦታ ሳይ ገደቡ በሚታዩ ትዕምርቶች አማካኝነት ከማግባባቱም በላይ ለትምህርት መማሪያ፣ለሀሳብ መለዋወጫና ለመሳሰሉት ነገሮች እንደሚያገለግል ይገልፃሉ፡፡ይህ ዘርፈ ብዙ አገልግሎቱ ደግሞ በትምህርትነት እንዲሰጥና እንዲያድግ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክቶለታል፡፡እንዲሁም celce Murcia (1991) በበኩላቸው ተማሪው በተሻለ ሁኔታ በቋንቋው እንዲጠቀምና የተግባቦቱን ሂደትም በጥልቀት እንዲመረምር ያደርገዋል ይላሉ፡፡ከምሁራን ሀሳብ እንደምንረዳው በጥሩ ሁኔታ እንዲጠቀም ያስችለዋል ሲባል በጽህፈት ክሂል አማካኝነት ሌሎችን የቋንቋ ክሂሎችን ለማዳበር ማስቻሉ ነው፡፡በሌላ በኩል Ur (1996) የጽህፈትን ትምህርት ከግለሰብዓዊና ከማህበራዊ ፋይዳ አንፃር ይመለከቱታል፡፡ግለሰባዊ ፋይዳው አመለካከትን ከመግለፅ፣የተፃፉ ሰነዶችን ከመመርመርና አዕምሯዊ ተግባራትን ከመመርመር አንፃር ሲመለከቱት ማህበራዊ ፋይዳውን ደግሞ የማህበረሰቡ የሆኑ የተለያዩ ታሪኮችን፣ባህላዊ መገለጫዎችን፣ሥነ ጽሁፋዊ ስራዎችንና የመሳሰሉትን ለመሰነድ ካለው ፋይዳ አንፃርቃኝ ተውታል፡፡በመሆኑም ጽሁፍ ለግለሰብም ይሁን ለማህበረሰቡ ያለው ፋይዳ ጉልህ አስተዋጽኦ ያለው መሆኑን እንረዳለን፡፡ከዚህ በመቀጠል በማንብበና በመጻፍ ክሂሎች መካከል ያለውን ትስስር ለመቃኘት ተሞክሯል፡፡

## 2.6 የማንበብና የመጻፍ ክሂሎች ትስስር

በማንበብና በመጻፍ ክሂሎች መካከል የጠበቀ ትስስር ያላቸው በመሆኑ በቅንጅት ቢቀርቡ የተሻለ እንደሆነ ጥናት ያደረጉ ተመራማሪዎች ያስረዳሉ፡፡መጻፍ አንብቦ የመረዳት ክሂልን ሊያሳድግ ይችላል፤ማንበብ ደግሞ የመጻፍ ክሂልን ሊያዳብር ይችላል፡፡ምክንያቱም ተማሪዎች አንድን ጽሁፍ በሚያነቡበት ጊዜ የአጻጻፍ ስልቱን፣የታሪክ አወቃቀሩንና የጽሁፉን መልዕክት በመገንዘብ ራሳቸው ለሚጽፉት ጽሁፍ ይጠቀሙበታል፡፡ይህም ሂደት በሁለቱ ክሂሎች መካከል ያለውን ትስስር የሚያመለክት መሆኑን Harp, etal (1996) ገልጸዋል፡፡እንዲሁም Ruddel (1997) ሲገልጹ ማንበብና መጻፍ ጥብቅ ትስስር ስላላቸው በውህደት ቢቀርቡ የተማሪዎችን በውህደት የማንበብና የመጻፍ ችሎታ ሊያሳድጉ ይችላሉ፡የሁለቱ በውህደት መቅረብ የትምህርቱንም ይዘት በተገቢው መንገድ እንዲረዱት ሊያግዛቸው ይችላል፡፡ክሂሎቹ የቀደመ

እውቀትንና ነባር ልምድን የሚጠይቁ ተመሳሳይ ባህሪያላቸው በመሆናቸውም እንደሆነ አስረድተዋል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ May (1990) በተመሳሳይ ተማሪዎቹ ውስብስብ ዐረፈተ ነገሮችን በሚጽፉበት ጊዜ አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው ሊዳብር ይችላል፡፡ይህም የሚያሳየው በክሂሎቹ መካከል ጥብቅ ትስስር መኖሩን ያመለክታል፡፡አንባቢዎችና ፀሀፊዎች የሚያከናውኗቸው ተግባራት በመስታዎት ውስጥ እንደሚታይ የአንድ ቁስ አካል ምስልና ራሱን የቁስ አካሉን ያህል ትስስር አላቸው፡፡አንባቢዎችና ፀሀፊዎች ለማንበብና ለመጻፍ በሚዘጋጁበት ጊዜ ሁለቱም ምቹ ሁኔታ ይፈጥራሉ፡፡ይኸውም ለማንበብ ወይም ለመጻፍ የራሳቸውን ዓላማ ይነድፋሉ፤ ፍላጎትም ይኖራቸዋል፤የቀደመ እውቀታቸውን ይጠቀማሉ፤አእምሯዊም ስል ይፈጥራሉ፡፡ የፀሀፊዎች ፍላጎት ሀሳባቸውን ለሌሎች በማካፈል መረጃ መስጠት ወይም ሰዎችን ማዝናናት ሊሆን ይችላል፡፡በመሆኑም የሁለቱ የመግባቢያ መንገዳቸው የተዘጋጀው በጽሁፍ ነው፡፡ የአንባቢዎች ፍላጎት ደግሞ መረጃ ለማግኘት፣ሃሳብ ለመጋራት ወይም ለመዝናናት ጽሁፍ ማግኘት ነው፡፡በመሆኑም ሁለቱም ባለጉዳዮች ማለትም ፀሀፊውና አንባቢው በተዘጋጀው ጽሁፍ ይገናኛሉ በማለት አስረድተዋል፡፡የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን ትስስር ቀደም ሲል ለማየት ተሞክሯል፡፡የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን ትስስር መሰረት በማድረግ የክሂሎቹ በቅንጅት መቅረብ ለቋንቋ ትምህርት ያለውን ጠቀሜታ በሚመለከት ተመራማሪዎች የተለያዩ ጽንሰ ሀሳቦችን ገልጸዋል፡፡ለአብነት ያህል የሚከተሉትን እንመለከታለን፡፡

### 2.6.1 አንብቦ መረዳትንና የመጻፍ ክሂልን በቅንጅት የማቅረብ አስፈላጊት

አንብቦ መረዳት የተለያዩ ክሂሎች የተዋሀዱበት ሂደት እንደሆነ Ellis and Brain (1980 )ይገልጻሉ፡፡እንደ Grellet (1991፡4-5)ክሂልን ሊያዳብሩ የሚችሉ መንገዶችን በማመቻቸት የተለያዩ አይነት ጥያቄዎችን ማውጣት ይቻላል፡፡ጥያቄዎችም ከምንባቡ አጠቃላይ አደረጃጀት ጀምሮ እስከ ዝርዝርና ግልጽ የተቀመጡ ይዘቶች ላይ ያተኮሩ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡የጥያቄዎቹ አይነትና ተግባርም የተወሰነ ክሂል ከማዳበር ጋር የተቆራኘ መሆን ይኖርበታል፡፡ይህም አንብቦ መረዳትን ለማስተማር ለተማሪዎች በሚወጡ ጥያቄዎች አማካኝነት ሊረጋገጥ ይችላል፡፡ ጥያቄዎቹ የተማሪዎችን የንባብ ክሂል ብቻ ሳይሆን ሌሎችን የቋንቋ ክሂሎችንም ማዳበር ይጠበቅባቸዋል፡፡ንባብና ፅሁፍ፡-በንባብ ትምህርት ወቅት ተማሪዎች አብረው ሊያዳብሩት ከሚጠበቅባቸው ክሂሎች ውስጥ አንዱ ጽሁፍ ነው፡፡የመጻፍ ክሂል በአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች አማካኝነት እንዲዳብር ተማሪዎች ሊያከናውኗቸው የሚችሉ ተግባራትን መስጠት ያስፈልጋል፡፡

ለምሳሌ ማስታወሻ እንዲይዙ ማድረግ፣ሀሳባቸውን ባጭርባጭሩ በጽሁፍ የመግለጽ ችሎታቸው በተወሰነ መልኩ እንዲያቀርቡ እና አጫጭር ሃሳቦችን አብራርተው በዝርዝር እንዲጽፉ የሚያደርጉ መልመጃዎች የመጻፍ ክሂልን ከንባብ ጋር በተቀናጀ መልኩ እንዲዳብር የሚያግዙ መሆናቸውን አስረድተዋል፡፡

ከምሁራኑ ሃሳብ እንደምንረዳው አንብቦ መረዳት ከሌሎች ክሂሎች ተነጥሎ ሊታይ የማይችል መሆኑን ነው፡፡በመሆኑም በአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች አማካኝነት ሌሎች ክሂሎች ተዋህደው እንዲዳብሩ ማድረግ እንደሚቻል እንረዳለን፡፡Conley (1997)የማንበብና የመጻፍ ክንዋኔዎችን በውህደት ማስተማር የተማሪዎችን የማንበብና የመጻፍ ችሎታ ለማሳደግ ጠቃሚ ዘዴ እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡በተጨማሪም ማንበብና መጻፍ በእለት ተእለት የመማር ክንዋኔዎች ላይ ትርጉምን መገንባት የሚያስችሉ የቋንቋ ሂደቶች እንደሆኑም አስገንዝበዋል፡፡በመሆኑም አንዱ ክሂል ሌላውን ለማዳበር መሰረታዊ ጠቀሜታ ያለውና እርስ በርሳቸውም የሚደጋገፉ በመሆናቸውም ነው፡፡የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን ትስስር መሰረት በማድረግ የክሂሎቹ በቅንጅት መቅረብ ያለውን ጠቀሜታ በሚመለከት ቀደም ሲል ለማየት ተሞክሯል፡፡ከዚህ በመቀጠል ደግሞ ክሂሎቹን በቅንጅት ለማዳበር የሚጠቅሙ ብልሃቶችን ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

### 2.6.2 አንብቦ መረዳትንና የመጻፍ ክሂልን ለማዳበር የሚረዱ ብልሃቶች

አንብቦ የመረዳትንና የመጻፍ ክሂልን በውህደት ለማስተማርና ለማለማመድ የተለያዩ ዘዴዎች እንዳሉ የመስኩ ተመራማሪዎች ይገልጻሉ፡፡ለአብነት ያህል ጥቂቶችን ለማየት እንሞክራለን፡፡ Block (1997)ሲገልጹ የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን አዋህዶ ማስተማር ክሂሎችን ለማጎልበት ከፍተኛ ድርሻ ያለው በመሆኑ የወቅቱ የቋንቋ ትምህርት አቀራረብ አብይ ጉዳይ እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡አክለውም በቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት አንብቦ መረዳትና ጽሁፍ ማቀናበርን ሊያጎለብቱ የሚችሉ በርካታ ብልሃቶች እንዳሉም ገልጸዋል፡፡በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ሁሉንም ዓይነት ጽሁፍ አንብቦ ለመረዳት ማንኛውንም ታሪክ ያለምንም ብዥታ አቀናብሮ ለመጻፍ ከሚያስችሉ ብልሃቶች ውስጥ ጥያቄ መጠየቅ፣ማብራራትና መተርጎም፣ማጠቃለል፣መተንበይና መገመት በጥልቀት ማሰብ የሚሉት ዋናዋናዎቹ ናቸው፡፡ከዚህ በመቀጠል እያንዳንዳቸውን በተናጠል እንመለከታለን፡፡

ጥያቄ መጠየቅ፡-በቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት ጥያቄ መጠየቅ የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን ለማሳደግ ጠቀሜታ እንዳለው የተለያዩ ተመራማሪዎች ያስረዳሉ፡፡ Block (1997) ሲገልጹ

ጥያቄ መጠየቅ ተማሪዎች አዳዲስ ሀሳቦችን ቀደም ብለው ከሚያውቁት ጋር አጣምረው እንዲያደራጁ ይረዳቸዋል፡፡ጥያቄ የመጠየቅ ተግባር በራሱ እውቀትን የማዳበር ክንውን ነው ሲሉ Airasian(1997) በበኩላቸው በቋንቋ መማር ማስተማር ወቅት ተማሪዎች ጥያቄ የሚያቀርቡ ከሆነ ሀሳባቸውን በቃላት ጽፈው እንዲገልጹ፣በጥልቀት እንዲያነቡና ትምህርቱን በትኩረት እንዲከታተሉ ስለሚያደርግ ጠቀሜታው ከፍተኛ እንደሆነ አስረድተዋል፡፡ከዚህም በተጨማሪ Gary(1995) ተማሪዎች እያነበቡ ወይም እየጻፉ እያሉ ምን አውቃለሁ? ለማወቅ የምፈልገው ምንድነው? ያወቅኩት ምንድነው? የሚሉ ጥያቄዎችን ሲያነሱ ግንዛቤያቸውን ያሳድግላቸዋል በማለት አስረድተዋል፡፡

ከዚህም በመነሳት አጥኝዋ ተማሪዎች ሲያነቡና ሲጽፉ በርካታ ጥያቄዎችን በጠየቁ ቁጥር ትምህርቱን የመረዳት ችሎታቸው እየጎለበተ ሊሄድ እንደሚችል ታምናለች፡፡በመሆኑም ተማሪዎች ጥሩ ጥያቄ አቅራቢዎች እንዲሆኑ ሊለማመዱ እንደሚገባም ታስገነዝባለች፡፡

**መተንበይና መገመት** (Inferring and predicting)፡-ይህን የማስተማሪያ ብልሃት በተመለከተ Block (1997) መገመት የሚባለው አንባቢው እያነበበ እያለቀጥሎ የሚመጣውን ሁኔታ ድርጊት ወይም ሀሳብ የሚጠቀምበት ልዩ የመገመቻ ስልት ነው፡፡መተንበይ ግን ከጽሁፍ አንብቦ የሚገኝን መረጃ ከቀደመ እውቀቱና ገጠመኙ ጋር አዛምዶ የተለየ ትርጉም የሚሰጥበት ወይም ስለሚነበበው ሀሳብ ምክንያታዊ ግምገማ ወይም ዳኝነት የሚሰጥበት አማራጮችን የሚጠቀምበት ልዩ ስልት ነው:: እንዲሁም Barrs (2000) መተንበይን በሚመለከት የሰጡት ማብራሪያ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ አንድን ጽሁፍ በማንበብ ላይ እያሉ የገጸባህሪያትን ማንነት፣ድርጊት፣ሴራ በመረዳት ንባባቸውን ሳይጨርሱ ወደ ፊት ሊከሰት የሚችለውን በመተንበይ መደምደሚያ ላይ ይደርሳሉ፡፡ይህም የሚያመለክተው ተማሪዎቹ ጽሁፉን በአግባቡ መረዳታቸውን በመጻፍ የሚገልጹበት እንደሆነ ገልጸዋል፡፡እንዲሁም አንብቦ መረዳትንና የመጻፍ ክሂልን በቅንጅት ለማስተማር ከሚያገለግሉት ብልሃቶች መካከል ማብራራትና መተርጎም ተጠቃሾች እንደሆኑ Block (1997) ያስረዳሉ፡፡በእነዚህ ብልሃቶች አማካኝነት ተማሪዎች ያነበቡትን ነገር በመጻፍ እንዲያብራሩና ማስረጃ እንዲያቀርቡ በማድረግ የመረዳት ችሎታቸውን ለመገንዘብ ጥረት የሚደረግባቸው ዘዴዎች ናቸው፡፡ተማሪዎች እነዚህን ብልሃቶች ተግባራዊ በሚያደርጉበት ጊዜ ስለአነበቡት ጽሁፍ ዝርዝር ማብራሪያ፣ትርጉምና ትንተና በጽሁፍ መስጠት የሚያችሉበት እድል ይፈጥርላቸዋል፡፡

ከዚህም ሌላ Gary (1995) እንደገለጹት ተማሪዎች ከመጀመሪያው ንባብ በኋላ በሚዘጋጁት የውይይት ክንዋኔዎች ሃሳባቸውን እንዲለዋወጡ የሚገፋፉ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ከእነዚህ ክንዋኔዎች በኋላ ተማሪዎቹ ስለ ጽሁፉ ያላቸውን ግንዛቤ ይተነብያሉ፣ትርጉም ይሰጣሉ፣ሌሎች አማራጭ ትርጉሞችን ይመረምራሉ፡፡እንዲሁም ተማሪዎች ስላነበቡት ወይም ስለጻፉት ነገር ማጠቃለያ መስጠት ከቻሉ ላነበቡት ወይም ለጻፉት ይዘት በቂ መረጃ ያላቸው መሆኑን ያመለክታል፡፡ይህ ዘዴ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ችሎታን ለማጎልበት ጠቃሚ ብልሃት ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡

**ማጠቃለል፡- (Summarizing)፡-**ማጠቃለልን በሚመለከት Block and Mangeri (1995) እንደገለጹት ተማሪዎች ከሚያነቡት ጽሁፍ በአእምሯቸው የታሰባቸውን በጽሁፍ የሚያጠቃልሉ ከሆነ የማስታወስ ወይም እውቀትን ይዞ የመቆየት ችሎታቸው 16% ያህል እንደሚጨምር ገልጸዋል፡፡በተጨማሪም ማጠቃለል ንባብን በዕለት ተዕለት ህይወት ተግባራዊ ለማድረግ ያስችላል፡፡በመሆኑም ተማሪዎች በሚያነቡበት ወቅት በየደረጃው በጽሁፍ ማጠቃለያ እየሰጡ መሄድ የሚያስችላቸውን ብልሃቶች መማር ይኖርባቸዋል፡፡

**ምሰል (Imaging)፡-**አንባቢው በሚያነበው ጽሁፍ ውስጥ ባሉት ገጸባህሪያት፣ድርጊትና ሁነቶች በአእምሮ ምስል የሚቀረጽበት ስልትም ሰላ ይባላል፡፡ይህንን ምለል አንባቢዎችና ለጸሀፊዎች ማስተማር አስፈላጊ የሚሆንበት ምክንያት እያነበቡ ወይም እየጻፉ እያሉ በንቃት እንዲያነቡ ስለሚያስችላቸው ነው፡፡ይህም ብልሃት በህይወት ውስጥ ስሜታዊ ገጠመኞችን ከአመለካከትና ከተጠየቃዊ ገጠመኞች ጋር ለማቀናጀትም ይጠቅማል፡፡በቋንቋው ሂደት ውስጥ በራሱ ሳይሆን የቋንቋው ሂደት በሚፈጥረው ገጠመኝ ውስጥ ጠልቆ ለመግባት ያስችላል፡፡ምስል ከሳች ጽሁፎችን እንዲያነቡ በማድረግ እያነበቡ እያሉ በአእምሯቸው የመጣውን ምስል እንዲናገሩ በማድረግ እያነበቡ እያሉም ምስላቸው እንዴት እየተለወጠ እንደሄደ በመጠየቅም ማለማመድ እንደሚቻል Block (1997) አስረድተዋል፡፡

የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን አዋህዶ ለማስተማር ከንባብ በፊት፣በንባብ ጊዜና ከንባብ በኋላ የመጻፍ ክንዋኔዎችን በማዘጋጀት ተማሪዎቹ ሃሳባቸውን እንዲያደራጁ በማድረግ የሚገፋፉ ሊሆኑ ይገባቸዋል፡፡ክንዋኔውም ቀላልና የተወሰነ ማስታወሻ መያዝ ሊሆን ይችላል፡፡ለምሳሌ ፡- ተማሪዎቹ በሚያነቡበት ጊዜ የቃላትን ትርጉም ከአገባባቸው መረዳት ሊሆን ይችላል፡፡ በመጨረሻም መምህራኑ የተማሪዎችን ስራ ለመገምገም ዝርዝር መልሶች የሚያስፈልጋቸው

ይዘት ተኮር ጥያቄዎችን ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡ጥያቄዎችም ከንባብ በፊት፣በንባብ ጊዜና ከንባብ በኋላ የሚቀርቡ ሊሆኑ ይገባል፡፡ሁሉም ክንዋኔዎች ከንባብ ጋር የተቆራኙ የመጻፍ ተግባሮች በመጻፍ ለማንበብ ምላሽ መስጠት የሚያስችሉና ማንበብና መጻፍን በቅንጅት የሚያለማምዱ ሊሆኑ ይገባቸዋል Gary (1995)::በአጠቃላይ በክለሳ ድርሳናቱ የቀረቡት ጥናታዊ ግኝቶች አንብቦ የመረዳትና የመጻፍን ክሂሎች በቅንጅት ማስተማር የተማሪዎችን የቋንቋ ችሎታ የሚያዳብር እንደሆነ ገልጸዋል፡፡እንዲሁም የማንበብና የመጻፍ ክሂሎች የማይነጣጠሉ፣የሚደጋገፉና ትስስር ያላቸው መሆኑንም አመልክተዋል፡፡በመሆኑም ክሂሎቹን በቅንጅት ተከታታይ በሆነ መልኩ ማቅረብ ከተቻለ የተማሪዎችን በራስ የመተማመንን ሁኔታ እንደሚፈጥርላቸው፣የተማሪዎችን ግንዛቤ እንደሚያሳድግላቸውና ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ እንደሚያግዛቸውም ገልጸዋል፡፡ከዚህ በመነሳት አጥኝዋ የመስኩ ተመራማሪዎች ክሂሎቹን በቅንጅት ለማስተማር ያቀረቧቸውን ብልሃቶች በመማሪያ መጽሀፉ መካተት አለመካተታቸውንና ከተካተቱ የክፍል ውስጥ አተገባበሩ ምን እንደሚመስል ለመመርመር ይህንን ጥናት ለማካሄድ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ከዚህ በመቀጠል ከዚህ ጥናት ጋር ተቀራራቢነት ያላቸውን ቀደምት ስራዎችን ቅኝት እንመለከታለን፡፡

## 2.7 የቀደምት ስራዎች ቅኝት

የዚህ ጥናት አቅራቢ በመረጠችው ርዕስ ላይ ጥናት ለማካሄድ ከመጀመሯ በፊት ከርዕሰ ጉዳዩ ጋር ተመሳሳይነት ያላቸውን የቀደምት ጥናቶች ዳሰሳ አካሂዳለች፡፡ይሁን እንጅ የዚህ ጥናት ትኩረት ከዚህ በፊት በተዘጋጀው የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ በተካተቱ አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ክሂል ቅንጅታዊ አቀራረብ ትንተና ላይ በመሆኑ ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸውን ጥናቶች ማግኘት አልተቻለም፡፡ነገር ግን ተቀራራቢነት ካላቸው ቀደምት ስራዎች ውስጥ ጥቂቶቹን ከዚህ ጥናት ጋር ያላቸውን ተመሳሳይነትና ልዩነት እንደሚከተለው ለመግለጽ ተሞክሯል፡፡

√**ትዝታ ደሳለኝ** (2003) "የቋንቋ ክሂሎችን አቀናጅቶ አማርኛ ቋንቋን የማስተማር አተገባበርና የተማሪዎች አቀባበል ፍተሻ" በሚል ርዕስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ያቀረበችው ጥናት ነበር፡፡የጥናቱ ዋና ዓላማ የነበረውም የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የቋንቋ ክሂሎችን ቅንጅታዊ አቀራረብና የተማሪዎችን አቀባበል መፈተሽ ነው፡፡ ይህንን ፍተሻ ለማካሄድም አጥኝዋ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስር ከሚገኙ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ሶስቱን በናሙናነት መርጣለች፡፡

በመሆኑም የተመራማሪዋ ጥናት በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የቋንቋ ክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብና የተማሪዎችን አቀባበል መፈተሽ ላይ የሚያተኩር ሲሆን ይህ ጥናት የማንበብና የመጻፍ ክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብን የክፍል ውስጥ አተገባበር ላይ ስለሆነ፤ እንዲሁም በክፍል ደረጃና ቢመሳሰልም በጊዜ በቦታ በአጠናን ስልቱ ስለማይገናኝ ከዚህ ጥናት ጋርየ ሚያገናኘው ነገር የለም።

√**አታክልቲ መኮነን** (1998) "የቋንቋ ክሂሎችን አቀናጅቶ አማርኛን የማስተማር ስነ-ዘዴ አተገባበር ፍተሻ" በሚል ርዕስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ያቀረበው ጥናት ነበር። የጥናቱ ዓላማም የቋንቋ ክሂሎችን እንዴት እንዳቀረቧቸው የሚቃኝ ነው።የጥናቱ ወሰንም አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በሚገኙ ሶስት ትምህርት ቤቶች ላይ ሲሆን ከሶስቱ ትምህርት ቤቶች ሁለት ሁለት መምህራንን በመውሰድ ምልከታ በማድረግ፣ ቃለ መጠይቅ በማቅረብ መረጃውን ሰብስቧል። ያገኘው ውጤትም መምህራኑ የቋንቋ ክሂሎችን አቀናጅተው እንደማያቀርቧቸው የሚያሳይ ነው። በመሆኑም የአታክልቲ ጥናት የሚያተኩረው የቋንቋ ክሂሎችን አቀናጅቶ አማርኛን የማስተማር ስነ-ዘዴ አተገባበር ላይ ሲሆን ይህ ጥናት ግን የማንበብና የመጻፍ ክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብና የክፍል ውስጥ አተገባበር ትንተና ስለሆነ እንዲሁም በክፍል ደረጃና በጊዜ ስለማይገናኝ ከዚህ ጥናት ጋር የሚያገናኘው ነገር የለም።

√**ሞገስአመራ** (1999) "የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን አዋህዶ ማስተማር ክሂሎችን በማጎልበት ረገድ የሚኖረውን ሚና" ለማረጋገጥ ጥናት አድርገዋል።በጥናታቸው ውጤትም በሀገራችን ሁለተኛ ደረጃ የትምህርት እርከን የማንበብና የመጻፍ ክሂሎች በውህደት የሚቀርቡበት ሁኔታ ትኩረት ያላገኘ እንደሆነ ገልጸዋል።ይህ ጥናት በአንጻሩ ክሂሎች በተናጠል ከሚቀርቡ ይልቅ በቅንጅት ቢቀርቡ የተሻለ እንደሆነ አመላክቷል።የሞገስ ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው በማንበብና በመጻፍ ክሂሎች ውህደት ላይ በማተኮሩ ነው።ነገር ግን ይህን ጥናት ከተመራማሪው ጥናት የሚለየው የተማራማሪው ጥናት የማንበብና የር
√. **እሸቴመብራት** (2003) "የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን አዋህዶ ማስተማር ክሂሎቹን በማጎልበት ረገድ የሚኖረው ሚና"በሚል ርዕስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ያቀረበው ጥናት ነበር።የጥናቱ ዋና አላማ የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን አዋህዶ በማስተማር ክሂሎቹን በማጎልበት ረገድ የሚኖረውን ሚና ለማረጋገጥ በወረታ በአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ሙከራዊ ጥናት አድርገዋል። የእሸቴ ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው በማንበብና በመጻፍ ክሂሎች ውህደት ላይ በማተኮሩ ነው።ነገር ግን ይህን ጥናት ከተመራማሪው ጥናት

የሚለየው የተማራማሪው ጥናት በአስረኛ ክፍል የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን አዋህዶ ማስተማር ክሂሎችን በማጎልበት ረገድ የሚኖረውን ሚና ለማረጋገጥ ሙከራዊ ጥናት ላይ ስለሚያተኩርና የዚህ ጥናት ትኩረት ደግሞ በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ ማንብብና የመጻፍ ክሂል ቅንጅታዊ አቀራረብ ትንተና እና የክፍል ውስጥ አቀራረብ ላይ ስለሆነ እንዲሁም በክፍል ደረጃ፣በጊዜና በቦታ ልዩነት ስላለው ከዚህ ጥናት ጋር የሚያገናኘው ነገር የለም፡፡

በአጠቃላይ ከላይ የቀረቡት ጥናቶች ቀደም ብዬ በዝርዝር ከእያንዳንዱ ጥናት ጋር በጠቀስኩት መልኩ የአታክልቲ (1998) እና የትዝታ (2003) ጥናቶች በስያሜም ይሁን በይዘት ከዚህ ጥናት ጋር ምንም ግንኙነት የላቸውም፡፡ ነገርግን የእሸቴ (2003) እና የሞገስ (1999) ጥናት በስያሜ የሚመሳሰል ሲሆን በአጠናን ዘዴውና በጥናቱ ትኩረት ከዚህ ጥናት ይለያል፡፡በመሆኑ ምይህ ጥናት ከላይ ከቀረቡት ጥናቶች በርዕስ፣ በተጠኝዎች የትምህርት ደረጃ፣ የጊዜ ርዝመትና የርዕስ አመራረጥ ከተጠቀሱት ጥናቶች በብዙ መልኩ እንዲለይ ያደርገዋል፡

# ምዕራፍ ሶስት

# የአጠናን ዘዴ

## 3.1 የጥናቱ ዘዴ

ይህ ጥናት የሚካሄደው በ9ኛለ ክፍል ተማሪዎች የተዘጋጀውን የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍት የአንብቦ መረዳትና የመፃፍ ክሂሎች ቅናጅታዊ አቀራረብ መተንተንና የክፍል ውስጥ አተገባበርን መፈተሽ ሲሆን ተግባራዊ የተደረገው የአጠናን ዘዴ ቅይጥ የምርምር ዘዴ ሲሆን በዋናነት አይነታዊ ምርምር /በደጋፊነት መጠናዊ ምርምር አገልግሎት ላይ ይውላል፡፡ የቅይጥ ምርምር ዘዴ የተመረጠበት ምክንያት ምርምሩ የሚተነተነው በገለፃእና በቁጥር መረጃ ትንተና ስለሆነ ነው፡፡ በተጨማሪም አይነታዊ ምርምር ዘዴን መጠቀም ያስፈለገበት ምክንያት ገለፃ ስልትን የተከተለ በመሆኑ ነው፡፡ መጠናዊ ምርምር በቁጥር ለሚተነተኑ መረጃዎች ላይ የተመሰረተ በመሆኑ አጥኝዋ በቁጥር ለምትገልፀው አመቺ ይሆናል ብላ መርጣዋለች ፡፡በዚህ መሰረት በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የተካተቱ ዋናዋና ነጥቦች የመረጃ ምንጭ አመራረጥ ፣የመረጃ መሰቢሰቢያ መሳሪያዎች አይነትንና አደረጃጀት፣ የመረጃ አሰባሰብ ሂደቱና አጠናን ስልት እንዲሁም የመረጃ አተናተንነጥቦችን ያካትታል፡፡

የዚህ አጠናን ፅንስ ሀሳብ ተጠኝ ቡድኖች ምንም ሳይምሩ የሚወስዱት ፍትና እና በትለያየ ሁኔታከትማሩ በሓላ የሚወስዱት ፈትና የሚያስዩት የችሎታ የልዩነት በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ የሚያሳይ ነው ( koul 1996 )

ጥናቱ የዘርፉ ተማራማሪዎች ያቀረቧችውን ትውረቶች መስረት በማድረግ ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችንና እሙኖችን በፈትና፣ ክፍል ውስጥ ምልከታና ቃለ መጠይቅ በማድረግ ተሰብስቧል፡፡

## 3.2 የመረጃ ምንጮች

ይህ ጥናት በተሳካ ሁሄታ አላማውን ያሳካ ዘንድ የመረጃ ምንጭ አድርጋ የትጠቀመችው ተማሪዎችንና መምህራንን ነው፡፡ብ፡፡ በ2015 ዓ .ም 9ኛ ክፍል ከሚማሩት ተማሪዎች ውስጥ 50 ተማሪዎችንና 9ኛ ክፍል ከሚያስትምሩ መምህራን መካከል 3ቱን በመረጃ ምንጭነት ተጠቅማለች፡፡

## 3.3 የጥናቱ ናሙና አመራረጥ

በዚህ ጥናት ውስጥ የክልል ፣ዞን፣የትምህርት ቤት ፣የመምህራንና የተማሪዎች ናሙና መርጣ ተካሂዷል ።ከዚህ ቀጥሎ እንደሚከተለው ይሆናል።

### 3.3.1 የክልልና የዞን አመራረጥ

በዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ በደቡብ ብሔር በሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል በአላማ ተኮር የናሙና አመራረጥ ዘዴ ሊመረጥ ችሏል።ምክናያቱም አጥኚዋ በዚህ ክልል ውስጥ አላማዋን በተሻለ መልኩ ለማሳካትና መረጃዎችን ማግኘት እንደምትችል ስለገመተች ነው። በደቡብ ብሔር በሔረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት በስሩ15 ዞኖችአካቶ ይዟል።ከነዚህም ዞኖች ጥናት ለማካሔድ ከገንዘብ፣ ከግዜና ከቁሳቁስ አቅርቦት አንጻር አስቸጋሪ ስለሆነ አጥኚዋ አመቺ የናሙና ዘዴን በመጠቀም የጉራጌ ዞንን በናሙናነት መረጣለች ።ይህ ዞን የተመረጠበት ምክንያት አጥኚዋ በዚህ ዞን ዉስጥ የምትሰራና የምትኖር በመሆኑ ነው ።እንዲሁም ለጥናቱ በአጭር ጊዜ ውስጥ በቂ መረጃዎች በማግኘት ስላሰበች ነው።

### 3.3.2 የትምህርት ቤት አመራረጥ

ይህ ጥናት በጉራጌ ዞን በገደባኖ ጉታዘር ወለኔ ወረዳ ውስጥ ከሚገኙ ስድስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ አንዱን ትምህርት ቤት በላማ ተኮር ናሙና ዘዴ መሰረት ተመርጧል ። በወረዳዉ ውስጥ ያሉት ስድስተ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሲሆኑ እነሱም፡- ገደባኖ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ኢንጌ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ተበተባን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ወለጋ ደሴ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ጉታዘር ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ከተዋት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ናቸው። ከነዚህም ውስጥ አጥኚዋ አንዱን ትምህርት ቤት በዓላማ ተኮር ናሞና አመራረጥ መሰረት የገደባኖ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መርጣለች። ይህ ትምህርት ቤቱ የተመረጠበት ምክንያት ካሉት ትምህርት ቤቶች አንጋፋ በመሆኑ እና ለመማር ማስተማር ምቹ ከመሆኑም በላይ የተሟላ ግብዓትና ልምድ ያላቸው መምህራን ያሉበት በመሆኑ ለጥናቱ ብቂ መረጃ ስለሚገኝበት ተመርጧል።

### 3.3.3 የመምህራን አመራረጥ

በጉራጌ ዞን ውስጥ በገደባኖ ጉታዘር ወለኔ ወረዳ ካሉት የመንግስት ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ብዛት ስምንት ሲሆኑ ከነዚህም ውስጥ ሶስት በገደባኖ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ። አንድ በኢንጌ ሁለተኛ ደረጃ

ትምህርት ቤት፣ አንድ በተበተባን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣፡አንድ በወለጋ ደሴ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ አንድ በጉታዘር ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ፤ አንድ በጅማ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ይገኛሉ፡፡ ነገር ግን እነዚህን መምህራን ካለው ጊዜ አንጻር በጥናቱ ውስጥ ለማካተት አስቸጋሪ ስለሆነ በገደባኖ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የዘጠንኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ሶስት በመሆናቸው እንዳሉ በጥናቱ የተካተቱ ሲሆኑ በጠላይ ናሙና ዘዴ አማካኝነት ተመርጠዋል ኣ፡፡

### 3.3.4 የምድብና የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ

ይህ ጥናት የሚካሄው በገደባኖ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ2015 ዓ.ም የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ነው፡፡ ለነዚህ ተማሪዎች ለሚቀርብላቸው የተለያዩ ጥያቄዎች መልስ እንዲሰጡ በማድረግ ነው፡፡በመሆኑም እነዚህ በቀጥታ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የ9ኛ ክፍል ተማሩዎች እንደ መጀመሪያ የመረጃ ምንጭነት ያገለግላለ፡፡ስለዚህ እነዚህን በናሙናነት የተመረጡ ምድቦች በመማር ላይ የሚገኙ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ከ ሀ እስከ ረ ምድቦች ሲሆኑ ጠቅላላ ቁጥራቸው 330(ሶስት መቶሰላሳ) ተማሪዎች ሲሆኑ በእያንዳንዱ መማሪያ ክፍል ውስጥ አማካይ ከ54 እስከ 55 ተማሪዎች ይገኛሉ ፡፡ ሁሉንም ምድቦች በጥናቱ ውስጥ ለማካተት አስቸጋሪ ስለሚሆን የ9ኛ ለ ክፍል ምድቦችን በእጣ ናሙና ዘዴ 50 ተማሪዎች የሚሆኑት ተመረጠው በጥናቱ ውስጥ ተካተዋል፡፡

## 3.4 የጥናቱ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

ከበርካታ የመረጃ መተንተኛ ዘዴዎች ውስጥ የተሰበሰበውን መረጃ ለመተንተን የሚያስችል ተስማሚ ዘዴ መረጣ ለተገቢው አላማ ማዋል መቻል አንዱ የምርምር አብይ ሂደት ነው ያለው እንዳወቀ /2009፣240) ፡፡ ይህንን ለማድረግ በዋናነት ጥቅም ላይ የዋለው መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ የክፍል ውስጥ ምልከታ ሲሆን በአጋዥነት ለመምህራን እና ለተማሪዎች ቃለ መጠይቅ በማቅረብ እንዲሁም ለተማሪዎች ቅደመና ድህረ ትምህርት ፈተና በመስጠት የሚፈለጉት መረጃዎች ተሰብሰበዋል፡፡

### 3.4.1 ፈተና

የጥናቱን ዓላማ መሰረት በማድረግ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ቅድመና ድህረ ትምህርት አዘገጃጀትና አተገባበር ላይ ፈተና ቀርቧል፡፡

### 3.4.1.1.ቅድመ ትምህርት ፈተና

ተተኳሪ የሆኑት የ9ኛለ ክፍል ተማሪዎች የሙከራ ትምህርቱ ከመጀመሩ በፊት የማንበብና የመፃፍ ችሎታቸውን ዳራዊ ሁኔታና የግንዛቤ ደረጃቸውን በምን ሁኔታ ላይ እንዳለ ማወቅ ለጥናቱ ጠቃሚ ነው፡፡ ስለዚህ አንብቦ የመረዳትና የመፃፍ ችሎታቸውን የሚለካ ሦስት ክፍሎች ያሉት ቅድመ ትምህርት ፈተና በአጥኚዋ ተዘጋጅቷል፡፡ የፈተናውን ተገቢነትና ጥራት ለማረጋገጥ አማካሪዬ በሚገባ ገምግመውታል፡፡ በሰጡት የሀሳብ ማሻሻያ መሰረት እንደገና ተዘጋጅቷል፡፡ ( አባሪአንድን ከገጽ አንድ እስከ አራት ያለውን ይመልከቱ፡፡)

በመጀመሪያው የፈተና ክፍል ቅደም ተከተላቸው ተዘበራርቀው የተቀመጡ ዓረፍተ ነገሮችን በማስተካከል አንድ ተራኪ ድርሰት እንዲጽፉ የሚያዝ ነው፡፡ ለእያንዳንዳቸው ቁጥር ተሰጥቷቸው ቅደም ተከተላቸው የተዘበራረቁ አስር ዓረፍተ ነገሮች ቁልቁል በረድፍ ተጽፈው ቀርበዋል ፡፡ ተማሪዎቹ እነዚህ ቅደም ተከተላቸው የተፋለሱ ዓረፍተ ነገሮች አንብበው እንደገና አደራጅተው በትክክለኛው የሀሳብ ቅደም ተከተል እንዲጽፉ ይጠበቃል ፡፡ ለእያዳንዱ ጥያቄ ምላሽ አስር ነጥብ እንዲይዝ ተደርጎ ሃምሳ ነጥብ ይዟል፡፡

በሁለተኛው የፈተና ክፍል ኢሰያስ አለሜ መጽሀፊ ምክር ገጽ 54–55 ማሻሻያ ተደርጎበት የተወሰደን አንድ ግጥም መሰረት ተደርጎ ተዘጋጅቷል፡፡ ተማሪዎቹ የግጥሙን መልዕክት መገንዘባቸውን ለመለካት በግጥሙ ውስጥ ሊመለሱ የሚችሉ ጥያቄዎችን በማካተት ሁለት ንዑስ ክፍሎችን እንዲይዝ ተደርጓል፡፡በመጀመሪያው ንዑስ ክፍል ለቀረቡት ጥያቄዎች ግጥሙን ከማንበባቸው በፊት መልሳቸውን አብራርተው እንዲጽፉ የሚያደርጉ ናቸው፡፡ ከቀደመ ዕውቀትና ልምድ በመነሳት ለሚጽፉት መልስ እንደ ጥያቄው መልስ በማየት በድምሩ ሃያ ነጥብ ይዟል፡፡ ሁለተኛው ንዑስ ክፍል ከምንባቡ በኃላ የወጡትን ጥያቄዎች ሲመልሱ ከጽሑፉ በሰፈረ ሀሳብ ፣ከቀድሞ ልምድና ዕውቀት በመነሳት የሚመልሷቸው ናቸው፡፡ለእያንዳንዱ ጥያቄ 6 ነጥብ በመስጠት በድምሩ አስራስምንት ነጥብ ይዟል፡፡

በሦስተኛው የፈተና ክፍል የተለያዩ አያያዥና የመሸጋገሪያ ቃላት ተዘርዝረዋል፡፡ያልተሟሉ ስድስት ዓረፍተ ነገሮች ተዘርዝረዋል፡፡ ከተዘረዘሩት አያያዥና የመሸጋገሪያ ቃላት ውስጥ የሚስማማቸውን በመምረጥ ክፍት ቦታዎችን እንዲያሟሉ ተደርጓል፡፡ ለእያንዳንዱ በትክክል ለሚሰጡት መልስ አስራሁለት ነጥብ እንዲይዝ ተደርጓል፡፡

### 3.4.1.2. ድህረ ትምህርት ፈተና

ከድህረ ትምህርት ፈተና ተገቢውን መረጃ መሰብሰብ እንዲቻል የፈተናው አስተማማኝነት ለማረጋገጥ ሲባል ቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተናዎች ተመሳሳይ ይዘት እንዲኖራቸው ተደርጓል። በመሆኑም ፈተናዎቹ በጥያቄ ቁጥር ብዛት ፣ በአቀራረብ ፣ በይዘትና በአወቃቀራቸው ተመሳሳይ እንዲሆኑ ተደርጓል። ቡድኖቹ በተለያያ ሁኔታ በየግላቸው የተዘጋጀላቸውን ትምህርት ለአንድ ወር ተምረዋል። ቡድኖቹ ከትምህርት በኃላ በትምህርቱ አቀራረብ ልዩነት ምክንያት የችሎታ ልዩነታቸው በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ማወቅ ያስፈልጋል። በመሆኑም በሙከራ ቡድኑ የአምብቦ መረዳትና የመፃህፍ ችሎታቸውን የሚለካ ድህረ ትምህርት የጽሑፍ ፈተና በአጥኝዋ ተዘጋጅቷል። ፈተናውን አማካሪዬና የትምህርት ቤቱ የቋንቋ ትምህርት ክፍል ገምግመው በሰጡት አስተያት መሰረት ተሻሽሎ ተዘጋጅቷል። በመሆኑም ፈተናው ሦስት ክፍሎች አሉት ። የእያንዳንዱን ክፍል መመሪያ  በጥንቃቄ ካነበቡ በኃላ ለሚቀርቡት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ ይሰጣሉ። ጥያቄዎቹን ለመስራት የተፈቀደው ጊዜ  1፡40 ሲሆን አጠቃላይ 100 ነጥብ አለው (አባሪ አምስትን ይመልከቱ)።

በመጀመሪያው የፈተና ክፍል የተጀመረውን ሀሳብ ለመጨረስ በርካታ መንገዶችን ተጠቅመው ጅምር አረፍተ ነገሮችን አስፈላጊውን ቃላትና ሐረጋት በመጠቀም በራሳቸው አባባል እንዲጨርሱ የሚያዝ ነው።  ለያንዳንዱ ጥያቄ ምላሽ አስር ነጥብ እንዲይዝ ተደርጎ በድምሩ ሃምሳ ነጥብ ይዟል።

በሁለተኛው የፈተና ክፍል ጠቃሚ ምክር የሚል አንድ ምንባብ መሰረት ተደርጎ ተዘጋጅቷል። ተማሪዎቹ የምንባቡን መልዕክት መገንዘባቸውን ለመለካት በምንባቡ ውስጥ ሊመለሱ የሚችሉ ጥያቄዎችን በማካተት ሁለት ንዑሳን ክፍሎችን እነዲይዝ ተደርጉዋል። በመጀመሪያው ንዑስ ክፍል ለቀረቡት ጥያቄዎች ምንባቡን ከማንበባቸው በፊት መልሳቸውን አብራርተው እንዲፅፉ የሚያደርጉ ናቸው። ከቀደመ ዕውቀትና ልምድ በመነሳት ለሚፅፉት አንድ ጥያቄ አምስት ነጥብ በመስጠት በድምሩ አስራ አምስት ነጥብ ይይዛል። በሁለተኛው ንዑስ ክፍል ከምንባቡ በኃላ የወጡትን ጥያቄዎች  ሲመልሱ በፅሁፉ በሰፈረ ሃሳብ በመነሳት የሚመልሷቸው ናቸው። ለእያንዳንዱ ጥያቄ ተገቢ መልስ በመስጠት ከመቶ ሃያ ድርሻ ይዟል ።

በሦስተኛው የፈተና ክፍልይግሞም ፤ አጭርና ቀላል የአማርኛ ሰዋሰው (2002) ላይ አያ ጥበቡ የሚል አንድ አጭር ፅሁፍ ቀርቦላቸዋል ። ምንባቡን ከአነበቡ በኃላበውስጡ የተካተቱትን ፈሊጣዊ አነጋገሮች ለይተው እንዲያወጡና ፍቻቸውን በፅሁፍ እንዲያብራሩ የሚያዝ ነው። ለያንዳንዱ ጥያቄ መልስ ከመቶ አስራ አምስትነጥብ ይዟል ።

### 3.4.2 ምልከታ

የክፍል ውስጥ ምልከታ የዚህ ጥናት ዋነኛ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ነው። ምልከታው የተካሄደው ወሰን (fixed) የምልክት ስልትን በመከተል ነው።በዚህ ወስን ምልከታ በመማሪያ ክፍል ውስጥ በሚደረገው መማር ማስተማር ሂደት ላይ የሚከናወነውን ክንውኖች ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑትን መረጃዎች ቀደም ብሎ በተዘጋጀው የመከታተያ ቅፅ መከናወኑን ወይም አለመከናወኑን በማየት እንዲረጋገጥ ተደርጓል። የመከታተያ ቅፅ የተዘጋጀው ቀደም ሲል በምዕራፍ ሁለት ከተገለፀው ፅንስ ሀሳብ በመነሳት ሲሆን ተግባራዊ ከመደረጉ በፊትም በአማካሪው ተገምግሞ እና አስተያየት ተሰጥቶበት የዓረፍት ነግር አውቃቅር፣ ይስርዓተ ንጥብ አጠቃቀም ማሻሻያ ተደረጎበት ተዘጋጅቷል።/ አባሪ አራትን ይመለከቱ/

የመከታተያ ቅፅን በመጠቀም በናሙናነት በተመረጠ አንድ ትምህርት ቤት ውስጥ የሚያስተምሩ ሶስት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በእያንዳንዳቸው ላይ ሶስት ሶስት ጊዜ ያህል የምልከታ ግምገማ ተካሂዷል። በምልከታ የተገኘውን መረጃ አስተማማኝነት ለማረጋገጥ ከአጥኚዋ በተጨማሪ አንድ በአማርኛ ቋንቋ የመጀመሪያ ዲግሪ ያላቸው መምህር ምልከታው በሚከናወንባቸው ክፍሎች ውስጥ በመገኘት እገዛ አድረገዋል።ለአጋዥ መምህር ምልከታው ከመከናወኑ በፊት ከአጥኘዋ ጋር በቂ የጋራ ውይይት ከተደረገ በኋላ ስለአሰራሩ መረጃ ተሰጥቷቸዋል።በዚህም መሰረት መረጃዎች ከተሰበሰቡ በኋላ ሁለቱ የምልከታ ውጤቶች ተደምረው አማካይ ውጤታቸውን በመውሰድ ለትንተና ቀርቧል።

### 3.4.3 የተማሪዎች ቃለ መጠይቅ

ለነቱ መረብጃ ማስገኘት የተመረጡው ሌላው የመርጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ቃለ መጠይቅ ነው ። የመረጃ ውን ትክክለኛ ነት ለመጠበቅ ሲባል ከሙከራ ቡድኑ 50 ተማሪዎች መካከል አራት ተማራዎች በቅድመ ትምህርት ፈተናው ለውጤት መስረት ት ተመርጠዋል።አመራረጡም ከፍተኛ ውጤት ካስመዝገቡት 2፣ መካከልኛ ውጤት ካስመዘግቡት 1እና ዝቅተኛ ውጤት

ካስመዝገቡት 1 በድምሩ አራት ተማሪዎች ተመርጠዋል። ለተማሪዎቹ ቅድመ ትምህርት ቃለ ምጠይቅ የትድረገበት ምክኒያት ከሙከራ ትምህርቱ በፊት አንብቦ የመረዳትና የምፃፍ ክህሎችንበሚመልክት ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት ታስቦ ነው። የጥያቄዎችን ምላሽ ልመተንትን እንዲመች በመቅረፀ ድምፀ በተደገፍ የሀለቱም ጊዜ ቃለ መጠይቅ ተከናውኗል በማዳመጥ ተተንቱኗል።በአጥኝዋ አማካኝነት ቅድመ ቃለ መጠይቁ 15/8/2015 ዓ.ም ፤ ድህረ ትምህርት ቃለ መጠይቅ ደግሞ 18/9/ 2015ዓ.ም ተደርጉል። ( አባሪ ሁለትና ስድስትን ይመልከቱ ) ።

### 3.4.4 የመምህራን ቃለ መጠይቅ

ከፈተና እና ምልከታ በተጨማሪ ቃለ መጠይቅም የዚህ ጥናት አጋዥ የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያ በመሆኑ አገልግሏል። ቃለ-መጠይቅ በጥናቱ ተተኳሪ በሆኑ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ለሚገኙ የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ የማበብና የመፃፍ ክሂሎችን ቅንጅታዊ በሆነ መንገድ እንዴት እየቀረበ እንደሆነ፣ስለቋንቋ ቅንጅታዊ አቀራረብ ያላቸውን ግንዛቤና የማበብና የመጻፉ ክሂልን በቅንጅት ሊተገበሩ ስለሚገጥሟቸው ችግሮች መረጃ ለመሰብስብ የተዘጋጀ ነው። ከዚህም በተጨማሪ በቃለ መጠይቁ የመምህራንን ዳራዊ መግለጫ አካቶ ይዟል ።ቃለ መጠይቁም እንደ ምልከታና ፈተና ለጥናቱ እንዲስማማ ሆኖ ከተዘጋጅ ቡኋላ በአማካሪዬ ተገምግሞና ማሻሻያ ተደረጎበት በአግልጋሎት ላይ ዉሏል ። /አባሪ ሶስት ይመለከቱ/ ቃለ መጠይቁ ተግባራዊ በሚሆንበት ጊዜ አጥኚዉ መቅረጽ ድምጽን (tape recorder) ተጠቅማለች።

## 3.5 አጠነቃቀር አቀራረብና አተናተን ዘዴዎች

በዚህ ጥናት ከክፍል ምልከታ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ከቅድመና ድህረ ፈተና የተገኙ መረጃዎች በማጠናከር ለትታኔ ቀርበዋል። በመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የተገኙ መረጃዎችን በመማር ማስተማር ሂደቱ መምህራን የአማርኛ ቋንቋ የማንበብና የመጻፍ ክሂል ቅንጅታዊ አቀራረብ ምን እንደሚመስል በዝርዝር የሚያሳዩና በምልከታ እና በፈተና የተገኙት ዉጤቶችን የድግግሞሽ መጠናቸውን በመግለፅ በመጠናዊ የምርምር ዘዴ ተተንትነዋል።

የቅድመ ትምህርቱ ሆነ ድህረ ትምህርቱ የጽሑፍ ፍተናዎች በቋንቋ ትምህርት ክፍል በተመረጠ አንድ መምህር እና ብአጥኝዋ ታርሞል። በአስተራረሙ መሰረት ለቅድምና ድህር ፍትናዎች ለያንዳንዱ ንኡስ ጥያቄዎ ተገቢ ነጥብ ተሰጥቷል። በተማሪ መለያ ቁጥር

መስረትዝርዝር ውጤቱን በምድመር ከ100% ያገኙት ተማዝግቧል። ይህን ለማረጋግጥ ከተካሄድው የቅድመና ድህረት ትምህርት ፍተና አማካይ ውጤት ንፅፅር 45.6 ለ66.9 ሆኖ ሙዝገቡና የ21.3 አሀዝ ልዩነት ታይቷል። ስለዚህ የቅድመና ድህረ ትምህርት ፈትናው በመቶኛ ተሰልቶ ተነፃፅሮ ተተንትኗል። የቃለ መጠይቁ ምላሽ በትምህርቱ አሰጣጥ ሂደቱ ወቅት ከመምህራን ጋር በነብራቸው ተራክቦ በክፍል ውስጥ ምልከታ የሚገኙ እሙን መረጃዎች እንዳይዝቡ በቅደም ተከትል ተገናዝበው ተብራርተው ቀርበዋል።

# ምዕራፍ አራት

# የመረጃ ትንተናና የጥናቱ ውጤት

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የዘጠንኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ  መምህራን የማንበብና የመፃፍ ክሂልን አቀናጅቶ ማስተማር።የሚያስተምሩት በአህዛዊ የምርምር ዘዴን ተጠቅሞ በመተንተን ከዉጤት መድርስ እንደሚቻል በዚህ ምዕራፈ  አራት ዉስጥ እንደሚከተለው ተተንትኗል፡፡

የጥናቱ መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የክፍል ዉስጥ ምልከት ቅድመና ድሀረ ትምህርት ፈተና፣ መምህራን የቃል መጠይቅና የተማሪዎች ቅድመ እና ድህረ የቃል መጠይቅ እንዲሁም ምልከታ እንደሆኑ በምዕራፍ ሶስት ተጠቅሰዋል፡፡ አጥኝዋ በእነዚህ መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች አማካይነት መረጃዎችን ሰብስባለች፡፡ የዚህ ጥናት ክፍል ዓላማ ደግሞ ለተጠየቁት መሰረታዊ ጥያቄዎች መልስ መስጠት ነው፡፡ ስለዚህ አላማውን በተግባር ለመፈትሽ በፍተና፣ በምልከታና በቃለ መጠይቅ ተሰብስበው የትገኙት የምረጃ ውጤቶች ተተንትነዋል።

## 4.1 መፃፉ አንብቦ የመረዳትና የመፃፍ ክሂልን ለማቀናጀት ያለው እገዛ

አማርኛ ቋንቋ ትምህርት መማርና ማስተማርሂደት ላይ የሚቀርቡ ይዘቶችን ከማንበብና ከመፃፍ ክሂል ጋር አቀናጅቶ ለማስተማር የሚሰጠው ጠቀሜታን እንዳለው ይታወቃል፡፡ በመሆኑም እነዚህን ክሂል ተጠቅመው የማንበብና የመፃፍ ክሂልን በማቀናጀት መማር፡፡ርዕስ ላይ የተማሪዎቹን የማንበብና የመፃፍ ችሎታን የሚፈትሹበት ነው፡፡የማንበብና የመፃፍ ክሂልን ተማሪዎች የሚያጎለበትን መንገድ በመምህራኖቹ ሲሰነዘሩ ነበር እንዲሁም ተማሪዎች እርስ በርስ ለማንበብና ለመፃፍ ክሂል ለማዳበር ይረዳዱ ነበር፡፡ስለዚህ የማንበብና የመፃፍ ክሂልን በቅንጅት ለማስተማር  የሚቀርቡ ይዘቶችን መፈተሽ አስፈላጊ ነው፡፡

## 4.2  ከምልከታ የተገኘ መረጃ ትንተና

በገደባኖ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ2015 ዓ.ም በየካቲት ወር  በቀን15/08/2015 ዓ.ም እስከ ግንቦት 18/09/2015ዓ.ም ድርስ የተደረገ ምልከታ ነው፡፡ በ4ኛ ውክፍል ጊዜ በ9ኛ‹‹ለ››ክፍል አጥኚዋ ተገኝታ ምልከታ አካሂዳለች በእያንዳንዱ ምልከታ የትምህርቱ ርዕስ መገናኛ ብዙሃን፣ ዐረፈተ ነገር፣ ምንባብ፣ ፅህፈት፣ ሀረግ፣ ምንባብ፣ ማሰሪ አንቀፅና ክርክር ናቸው በየዕለቱም የትምህሪቱ ርዕስ የቆሻሻ አወጋገድ ዘዴ በሚል የቀረብ በገፅ 121 ላይ ያለ ሲሆን፡- ርዕሱ በጥቁር ሰሌዳው ላይ ተፅፏል፡፡ በዛውቀን መምህሩ ማስታወሻዎችን በጥቁር ሰሌዳ ላይ በመጻፍ ተማሪዎቹ ከጥቁር ሰሌዳዉ ላይ አዳዲስ ቃሉን እያነበቡ እንዲፅፉ ያደርጉ ነበር፡፡ነገር

ግን ትንሽ ተማሪዎች በጥቁር ሰሌዳ ላይ የተፃፈውን ማስታወሻ እያነበቡ መፃፍ ሲያስቸግራቸው አስተውያለሁ፡፡በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ በሶስቱም መምህራን በተደረገው የሶስት ተከታታይ ምልከታዎች የቀረቡት ይዘቶች የማንበብና የመፃፍ ክሂልን ለማቀናጀት ለማዳበር ያላቸው ሚና ለማወቅ በተደረገው ምልከታ የተገኘው መረጃ ከዚህ ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

ከተሰበሰቡት የሶስት ክንውን ምልከታዎች መረጃዎች፡፡ እንደተረጋገጠው ማንበብና መፃፍ በቅንጅት ሲማሩ ሁሉም ተማሪዎች የተሰጣቸውን ተግባር በንቃትና በፍላጎት ሲያከናውኑ ተስተውሏል፡፡ የድህር ትምህርት ፈተናው ውጤትም ይህንን ሀሳብ የሚያጠናክር ሆኖ ተገኝቷል፡፡

<u>ሠንጠረዥ 1፡- መፀሀፉ አንብቦ የመዳትና የመፃፍ ክሂልን ለማቀናጅት ያለው እገዛ፡፡</u>

| ተ.ቀ | የመከታተያ ነጥቦች | ድግግሞሽ | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በጣም ከፍተኛ | | ከፍተኛ | | መካከለኛ | | ዝቅተኛ | | በጣም ዝቅተኛ | |
| | | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % |
| 1 | የክፍለ ጊዜው ይዘት አንብቦ የመረዳትና የመፃፍ ክሂልን ለማቀናጀት ያለው እገዛ | - | - | 2 | 22.22 | 5 | 55.55% | 1 | 11.1 | 1 | 11.1 |
| 2 | አንብቦ የመረዳትና የመፃፍ ክሂልንበቅንጅት ለማስተማር የሚቀርበው ይዘት ከተማሪዎች ህይወት ጋራ ያለው ቁርኝት | - | - | 4 | 44.44 | 3 | 33.33 | 1 | 11.1 | 1 | 11.1 |
| 3 | መ/ሩ(ሯ)ተማሪዎችበትምህ ርት ጊዜ ምንባብ እዲያነቡ የማድረግ ሁኔታ | - | - | 1 | 11.11 | 3 | 33.33 | 4 | 44.4 | 1 | 11.11 |

ከላይ የቀረበው የምልከታ ሠንጠረዥ እንደሚያመለክተው በሶስት መምህራን በተደረገው 9 ተከታታይ ምልከታዎች ላይ የክፍል ጊዜው ይዘት ማንበብና የመፃፍ ክሂልን ለማቀናጀት ያለው እገዛ ምን እንደሚመስል ለቀረበው ጥያቄ የተገኘው ምላሽ፡፡ምልከታዎች ላይ የክፍለ ጊዜው

ይዘት አንብቦ የመረዳትና የመፃፍ ክሂልን ለማቀናጀት ያለው እገዛ ምን እንደሚመስል ለቀረበው ጥያቄ የተገኘው 2(22.22%) ከፍተኛ፣ 5(55.55%)መካከለኛ፣1(11.11%)ዝቅተኛና 1(11.11%) በጣም ዝቅተኛ እንደሆነ ለመመለከት ችያለሁ።

በተራ ቁጥር 2 ላይ ለቀረበው ጥያቄ እንደሚያሳየውአንብቦ የመረዳትና የመፃፍ ክሂልን በቅንጅት ለማስተማር የሚቀርበው ይዘት ከተማሪዎች ህይወት ጋራ ያለው ቁርኝት ጥያቄ የተገኘው 4(44.44%) ከፍተኛ፣ 3(33.33%)መካከለኛ፣ 1(11.11%)ዝቅተኛና 1(11.11%)በጣም ዝቅተኛ እንደሆነ ለመመልከት ተችሏል።

በተራ ቁጥር 3 ላይ ለቀረበው ጥያቄ እንደሚያሳየው መ/ሩ(ሯ)ተማሪዎችበትምህርት ጊዜ ምንባብ እዲያነቡ የማድረግ ሁኔታ ጥያቄ የተገኘው 1(11.11%) ከፍተኛ፣ 3(33.33%) መካከለኛ፣ 4(44.44%) ዝቅተኛና 1(11.11%) በጣም ዝቅተኛ እንደሆነ ለመመልከት ተችሏል።

ጠቅለል ባለ መልኩ ክፍል ጊዜው ይዘት የማበብና የመፃፍ ክሂልን ለማቀናጀትና ለማዳበር ያለው እገዛ ምን አንድሚመስል ለመመርመር በተደረገው ምልከታ የተገኘው ምላሽ እንደሆነ ነው።

## 4.3 ከመምህራን ቃለ መጠይቅ የተገኘ ምላሽ

የዘጠንኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የማንበብና መፃፍ ክሂልን አቀናጅተው ለማስተማር የሚያቀርቧቸው ይዘቶች ምን እንደሚመስሉ ለማወቅ በተደረገው ቃለ መጠይቅ የሚከተለው ምላሽ ሊገኝ ችሏል። የማንበብና የመፃፍ ክሂልን በማቀናጀት ለማስተማር የሚያቀርቧቸው ይዘቶች ክሂሎቹን በተገቢው ለማቀናጀትና ለማዳበር ያላቸው እገዛ ምን ያህል ነው? ለሚለው ጥያቄ ሶስቱም መምህራን ክሂሎቹን በቅንጅት ለማስተማርና ለማዳበር የሚያቀርቧቸው ይዘቶች ያላቸው ሚና ክሂሎችከፍተኛ እንደሆነ ገልፀዋል።

ከምልከታ የተሰበሰቡት መረጃዎች ተተኳሪ መምህራን የማንበብና መፃፍ ክሂልን በቅንጅት ለማስተማር የሚያቀርቧቸው ይዘቶች ክሂሎችን በተገቢው ሁኔታ ለማቀናጀትና የተማሪዎቹን የቋንቋ ችሎታ ለማዳበር ያላቸው እገዛ ዝቅተኛ እንደሆነ ያመለክታሉ።ከቃለ መጠይቅ የተገኘው መረጃ ሶስቱም መምህራን የሚያቀርቧቸው ይዘቶች ክሂሎችን ለማቀናጀት ለማዳበር ያላቸው እገዛ ከፍተኛ እንደሆነ ቢገልጹም ተአማኒነት የለውም ።ምክንያቱም በተካሄደው 9 ምልከታዎች ላይ የቀረቡት ይዘቶች 4(44.44%) ብቻ የሆኑ ይዘቶች አስተዋፆአቸው ከፍተኛ እንደነበር

ለመረዳት ተችሏል፡፡በተለያየ መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የተገኘ ምላሾች ሲጠቃለሉ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የማንበብና የመፃፍ ክሂልን በቅንጅት የሚያቀርቧቸው ይዘቶች ክሂሎች በተገቢው ሁኔታ ለማቀናጀትና ለማዳበር ያላቸው ሚና ዝቅተኛ እንደሆነ ነው፡፡

በዚህ ክፍል ውስጥ የማንበብና የመፃፍ ክሂልን አቀናጅቶ የማስተማር ሥነ ዘዴ ከተማሪዎቹ ፍላጎትና እንዲሁም የሚቀርብላቸው ይዘቶች፣ ዳራና ችሎታ ጋረ በተዛመደ መልኩ እንዲሆን ያደረጋል፡፡መምህራን ለሚያቀረቡት ርዕስ የማንበብና የመፃፍ ክሂልን አቀናጅቶ ማስተማር ለተማሪዎቹ ምን እንደሚጠቅም ያሳያል፡፡ ሶስት መምህራን የተማሪዎች የማንበብና የመፃፍ ክሂልን ቅንጅታዊ ትምህርቱ የተማሪዎቹን ፍላጎት፣ ችሎታና ዳራ መሰረት ያደረጉ እንዲሆኑ ጥረት እንደሚያደረጉ ሲገልፅ በመማሪያ መጸሐፍ ላይ ያሉ ይዘቶች እንዲሁም ለዚህ ቅንጅታዊ ክሂል የሚረዱ ነገሮችን በክፍሉ ውስጥ የማንበብና የመፃፍ ክሂልን አቀናጅተው እንዲያስተምሩ ይረዳል፡፡ ከመምህራን ቃለ መጠይቅ የተገኘዉን ምላሽ ተመሳሳይነት ይታይባቸዋል፡፡ መምህራን የማነበብና የመፃፍ ክሂልን አቀናጅተው ለማስተማር የሚያቀርቡት ይዘቶች ከተማሪዎቹ ፍላጎት፣ገጠመኝና ችሎታ ጋር የማይጣጣሙ እንዲሁም ተማሪዎቹለመሳተፍ ያላቸው እስተዋፆ ዝቅተኛ እንደሆነ ከምልከታው ከጸሑፍ መጠይቅ የተገኘው ምላሽምሶስት መምህራን ጥናት ማድረጋቸው ተገልፃዋል፡፡

አንብቦ መረዳትና የመፃፍ ክሂል ተቀናጅተው ቢቀርቡ ተማሪዎች የቋንቋ ችሎታ ላያ ለውጥ ይመጣል ብለው የስባሉ? ከሆነ እንዴት? አዎ ጠቀሜታ አለዉ ምክንያቱም በቃል ያለ ይረሳል በፁሁፊ ያለ ይወረሳል እንደሚባለዉ ሁሉ ተማሪዎች ይሄንን በማሰብ ማንበብ ብቻ ሳይሆን በፅሁፍም መጻፍ አለባቸው፡፡

- በመምህር 1 የተሰጠ ማብራሪያ በመጸሐፉ ላይ ያሉት ክሂሎች በተናጥል ሲሆኑ እኛ ግን እነዚህን ክሂሎችን አንድላይ በማድረገ ነው፡፡ ምክንያቱም ሁለቱም ክሂሎች የአንድ ሳነቲም ሁለት ገፆች ናቸው፡፡ስለዚህ ተማሪዎችን የተሻለ ግንዛቤ እነዲኖራቸው ሁለቱንም ክሂሎች አጣምረን በማስተማር ነው፡፡
- የመምሀሩ መጸሓፍና የተማሪዉ መጸሀፍ ተየያዥነት አለው ፡፡በተማሪዎች የመማሪያ መጸሀፍ ስልቶችን የያዘ ሲሆን ታመሪዎቹ የአንብቦና የመጸሀፍ ክሂሎችን አዋህዶ መጠቀምን የያዘ ነው፡፡
- ተማሪዎች የማንበብና የመጻሀፍ ክሂሎችን መጠቀም በተማሪዎች ላይ ለውጥ ያመጣ ተማሪዎች የመፃፍ ክሂልን ብቻ ብናስተምራቸው የማነበብን ክሂል ላይረዱልን ይችላሉ

ስለዚህ ሁለቱም ተቀናጅቶ ሊማሩ ይገባል።

- የመምህሩን መምሪያ እጠቀማለሁ ምክንያቱም የተማሪዎች መጸሐፍ እና የመምህርን መምሪያ ስጠቀም ሁለቱም የማንበብና የመፃፍ ክሂልን አብሮ እንድጠቀም ይረዱኛል።

- ➢ በመምህር  የተሰጠ ትንትና በዚህ 9ኛ ክፍል መማሪያ መጸሐፍ ውስጥ አራቱም ክሂሎች አሉ በመሆኑም የማንበብ እና የመፃፍ ክሂል አቀናጅቶ ነው የምናስተመረው መክንያቱም ይህ ክሂል ለተማሪዎቹ ወሳኝ ከመሆኑ አንፃር ተማሪው አንብቦ የመረዳት እና አምብቦ የመፃፍ ክሂል ሊኖረዉ የገባል።
- ➢ የማንበብና የመፃፍ ክሂል አቀናጅቶ ማስተማር ለታመሪዎች ብዙ ጠቀሜታ አለው ብዙ ጊዜ ተማሪዎች የመፃፍ ክሂል ከራሳቸው አዉጥተው የሚፅፉ ስለሆን ስለዚህ ለመፃፍ ብዙ ማንበብ ይጠበቀባቸዋል።ተማሪዎች ብዙ ባነበቡ ቁጥር ብዙ ነገር ሊፅፉ ይችላሉ ለምሳሌ ልቦለድ፣ተወኔት ግጥም የመሳሰሉትን ሊፅፉ ይችላሉ ስለዚህ ማንበብና የመፃሓፍ ክሂል አብሮ ሊሄዱ የሚችሉ ክሂልና ሊነጣጠሉ የማይችሉ ናቸው።
- ➢ የማንብብና የመፃፍ ክሂል በተማሪዎች ላይ ድክመት አለ ምክንያቱም ሁሉም ተማሪዎች እኩል የሆነ ተሰጦ የላቸዉም አንዳዶቹ ተማሪዎች የመፃፍ ክሂል ሲኖራቸው አንዳንዶቹ ደግሞ የማንበብ ክሂል ይኖራቸዋል ።ይህን ድክምት የምንቀርፈው ተማሪዎቹነ ለይቶ በማዉጣት የማንበብ እና የመፃፍ ክሂል የለባቸውን ለይቶ የድጋፍ ትምህረት መስጥት እና ማንበብ ችግር ያለባቸውን ተማሪዎች በድጋፍ ትምህርቱ ጊዜ እንዲያነቡ በማድረግ ነው።
- ➢ በዚህ መጸሀፍ ውስጥ አራቱንም ክሂሎችን የያዘ ነው።ይህ መጸሐፍ አስር ምዕራፍ ሲኖረው በያንዳንዱ መንባብ ስር የመፃፍ ክሂል አላቸው ።እነዚህ አራቱ ክሂሎች በተናጥል ይገኛሉ ሆኖም ግን ለኛ ለማስተማር ይረዳን ዘንድ እና ተማሪዎቹን ጥሩ የማንበብና የመፃፍ ክሂል እነዲኖራቸው እኔ በማቀናጀት ነው የማስተምረው። በምዕራፍ ሁለት ገፅ23 ላይ ተማሪዎቹን የማንበብና የመፃፍ ክሂልን አቀናጅቶ እንደፅፍ የሚያደረግ ርዕስ አለ እሱም ተማሪዎቹን ከመጽሔትና ከመጸሐፍ እና ከተለያዩ ጋዜጣዎች ላይ አንብባቹ ተውኔት ፃፉ ይላል፣ስለዚህ እዚህ ላይ የምናየው የማንበብና የመፃፍ ክሂልን አቀናጅቶ የማስተማር ስነ-ዘዴ ነው።እነዲሁም ምዕራፍ ሶስትም ላይ እንደዚሁ ተመሳሳይ የማስተማር ስነ-ዘዴ አለ አንዳንድ ቦታ ግን የመፃፈ ወይም የማንበብ ክሂልን ብቻ የያዘ ዘዴ ነው።
- ➢ የመምህሩ መጸሓፍና የተማሪዉ መጸሀፍ  ተየያዥነት አለው ።በተማሪዎች የመማሪያ

መጸሀፍ ስልቶችን የያዘ ሲሆን ታመሪዎቹ የማንበብና  የመፃፍ ክሂሎችን አዋሀዶ መጠቀምን የያዘ ነው፡፡ስለዚህ ይህ መጸሐፍ የማንበብና መፃፍ ክሂልን አቀናጅቶና በተናጥል የያዘ ነው፡፡

- በመምህርት 2 የተሰጠ ትንተና በዚህ 9ኛ ክፍል መማሪያ መጸሐፍ ውስጥ አራቱም ክሂሎች አሉ በመሆኑም የማንበብ እና የመፀሐፍ ክሂል አቀናጅቼ አላስተመርም፡፡በዚህ መጸሐፍ ውስጥ አራቱም ክሂል ቢኖሩም ለብቻ ናቸው ስለዚህ ማዳመጥ ምንድነው፣ ማንበብ ምነድነው፣ መፃፍ ምነደነው፣ መናገር ምነድነው ነው ብዬ አስተምራለው፡፡ ይህ ክሂል ለተማሪዎቹ ወሳኝ ከመሆኑ አንፃር ተማሪው አንብቦ የመረዳት እና አምብቦ የመፃፍ ክሂል እንዲኖረዉ ያረጋል፡፡የማንበብና የመፃፍ ክሂል የአንድ ሳነቲም ሁለት ገፅታ ቢሆኑም እኔ ግን እነዚህን ክሂሎች አቀናጅቼ አላስተምርም፡፡
- የማንበብና የመፃፍ ክሂል አቀናጅቶ ማስተማር ለታመሪዎች ብዙ ጠቀሜታ አለው ብዙ ጊዜ ተማሪዎች መፃፍ ክሂል ለተማሪዎቹ እወቀት እንዲኖራቸው ይረዳቸዋል ፡፡የማነበብ ክሂልን ለማዳበር ተማሪዎች ዕለት ከዕለት ማንበብ ይጠበቅባቸዋል፡፡ሥለዚህ መምህሩ ትልቅ ድርሻ አለበት እነዚህን ክሂሎች አቀናጅቶ ማስተማር፡፡
- የማንበብና የመፃፍ ክሂል በተማሪዎች ላይ ድክመት አለ ብሎ ለመናገር ብዙ ይከብደኛል ምክንያቱም ተማሪዎችን የቱ እንደሚያነብ እና እንደማያነብ ለመለየት ይከብደኛል፡፡ የመፃፍ ክሂል ግን በተወሰኑት ተማሪዎች ላይ ይታያል ተማሪዎችን በምጠይቅበት ወቅት አስተካክለው የሚፅፉ በጣም ጠቂት ናቸው፡፡
- በዚህ መጸሀፍ ውስጥ አራቱም ክሂሎችን የያዘ ነው፡፡ይህ መጸሐፍ በያንዳንዱ ምንባብ ስር የመፃፍና የማንበብ ክሂል አላቸው፡፡ እነዚህ አራቱ ክሂሎች በተናጥል ይገኛሉ ሆኖም ግን ማንበብ ካለ መፃፍ አለ እርስ በራሳቸው የተያያዙ እንደመሆናቸው አንፃር በዚህ መፃፍ ውስጥ የማንበብ ክሂል ይዞ ይገኛል፡፡
- የመምሀሩ መጸሓፍና የተማሪዉ መጸሀፍ  ተየያዥነት አለው ብሎ ለመግለፅ አይቻልም ምክንያቱም የመምህሩ መምሪያ እነደኛ ትምህርት ቤት የለም፡፡ በዚህ ሁኔታ ላይ የመምሀሩ መምሪያ ከተማሪው መምሪያ ጋር ያለዉን  ቁረኝት ማወቅ አይቻልም ፡፡ ሆኖም ግን በመምሀሩ መምሪያ ውሰጥ የማስተማሪያው ስነዘዴን ጨምሮ የሚይዝልን ነው ፣የተማሪው መጸሐፍ ግን ይህን አጠቃሎ ላይዝልን ይችላል፡፡
- ተማሪዎች የማንበብና የመጻሀፍ ክሂሎችን መጠቀም በተማሪዎች ላይ ለውጥ ያመጣል፡፡ ተማሪዎች የመፃፍ ክሂልን ብቻ ብናስተምራቸው የማነበብን ክሂል ላይረዱልን ይችላሉ

ስለዚህ ሁለቱም ተቀናጅቶ ሊማሩ ይገባል፡፡አንድ ተማሪ የማንበብ ክሂልን ወይም የመፃፍ ክሂልን ብቻ ብናስተምር ጥሩ አንባቢ ቢሆን ጥሩ ፃፊ ላይሆን ይችላል ፡፡መሆን ያለበት ጥሩ አንባቢና ጥሩ ፅሃፊ እንዲሆኑ ሁለቱንም ክሂሎች አቀናጅቶ ማስተማረ በተማሪዉ ላይ ትልቅ ለውጥ ሊያመጣ ይችላል፡፡

❖ የመምህሩን መምሪያ እልጠቀምም ምክንያቱም የተማሪዎች መጸሐፍ እንጂ የመምህራን መምሪያ የለም፡፡ነገር ግን የመምህርን መምሪያ ቢኖር ሁለቱም የማንበብና የመጸሃፍ ክሂልን አብሮ እንድጠቀም ዬረዱኛል፡፡መምሪያውን በምጠቀምበትጊዜ በመምሪያው ላይ የተለያዩ ትዛዞች ሊኖሩት ይችላሉ ለምሳል ድረስት እነዲያነቡ ወይም እንዲፅፉ ስለዚህ ተጨማሪ ተግባሪ ስላለው እሱን ብጠቀም የተሻለ ለውጥ በተማሪዎች ላይ ሊያመጣ ይችላል፡፡

<u>ሠንጠረዥ 2 ፡- ከመምህራ ቃለ መጠይቅ የትግኙ መረጃዎች</u>

| ተ.ቁ | የቀረቡት ጥያቄዎች | | በቁጥር | በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | የማንበብናየመፃፍ ክሂልን አቀናጅተው ያስተምራሉ ለም? | አዎ | 3 | 100% |
| | | አይ | - | - |
| | | ድምር | 3 | 100% |
| 2 | የማንበብና የመፃሀፍ ክሂልን አቀናጅተው ለማስተማር ደስተኛ ነዎት? ለምን? | አዎ | 3 | 100% |
| | | አይ | - | - |
| | | ድምር | 3 | 100% |
| 3 | የማንበብና የመፃሀፍ ክሂልን በማቀናጀት በሚያስተምሩበት ጊዜ በተማሪዎች ላይ የተመለከቷቸው ድክመቶች አሉ? | አለ | 3 | 100% |
| | | የለም | - | - |
| | | ድምር | 3 | 100% |
| 4 | በመማሪያ መፃሀፍት ውስጥ ያሉትን የማንባብና የመፃሀፍ ክሂል የሚያቀርቧቸው በአንድ ላይ ነው? | አንዳንዴ | 3 | 100% |
| | | ሁለለግዜ | - | - |
| | | ድምር | 3 | 100% |
| 5 | የተማሪው መማሪያ መፃሀፍ፣ የመምህሩ መምሪያ እና መርሃ ትምህርቱ አንብቦ የመረዳትና የመፃሀፍ ክሂሎችን እርስ በእርስ ተያይዘው እንዲቀርቡ በማድረግ የመማር ማስተማር ዘዴን ለመምራት አጋዥ ናቸው ? | ነው | 2 | 66.67% |
| | | አይደለም | 1 | 33.33% |
| | | ድምር | 3 | 100% |
| 6 | አንብቦ መረዳትና የመፃሀፍ ክሂል ተቀናጅተው ቢቀርቡ ተማሪዎች የቋንቋ ችሎታ ላያ ለውጥ ይመጣል ብለው የስባሉ? | አዎ | 3 | 100% |
| | | አያ | - | - |
| | | ድምር | 3 | 100% |
| 7 | የመምህሩን መምሪያ መጸሐፍ ይጠቀማሉ?የማንባብና የመፃሀፍ ክሂልን ቅንጅታዊ ትምህርት እንዴት ያቀርበዋል? | አዎ | 2 | 66.67% |
| | | አይ | 1 | 33.33% |
| | | ድምር | 3 | 100% |

ከዚህ ሠንጠረዥ የምንረዳዉ በጥያቄ ቁጥር 1 የቀረበው ጥያቄ እንደሚያሳው የማንበብና የመፃፍ ክሂልን አቀናጅተው ያስተምራሉ ለሚለው ጥያቄ አዎ አስተምራለሁ ያሉ መምህራን 3(100%)ነው፡፡በጥያቄ ቁጥር 2 የቀረበው ጥያቄ እንደሚያሳው የማንበብና የመፃፍ ክሂልን አቀናጅተው ለማስተማር ደስተኛ ነዎት ለሚለው አዎ ያሉ መምህራን 3(100%)ነው፡፡ከዚህ መረዳት እንደሚቻለው የማንበብና የመፃፍ ክሂልን አቀናጅተው ለማስተማር ደስተኛ እንደሆኑ ነው፡፡

በጥያቄ ቁጥር3የቀረበው ጥያቄ እንደሚያሳው የማንበብና የመፃፍ ክሂልን በማቀናጀት በሚያስተምሩበት ጊዜ በተማሪዎች ላይ የተመለከቷቸው ድክመቶች አሉ በማለት የመለሱት 3(100%) ሲሆኑከዚህ መረዳት እንደሚቻለው የማንበብና የመፃፍ ክሂልን አቀናጅተው ለማስተማር ድክመቶቸ እንዳሉ ነው፡፡በጥያቄ ቁጥር 4 የቀረበው ጥያቄ እንደሚያሳው በመማሪያ መፃህፍት ውስጥ ያሉትን የማንባብና የመፃፍ ክሂል የሚያቀርቧቸው በአንድ ላይ ነው በሚባሉበት ወቅት አንዳንዴ በማለት የመለሱት 3(100%) ሲሆኑ ከዚህ መረዳት እንደሚቻለው የማንበብና የመፃፍ ክሂልን አቀናጅተው የሚያስተምሩት አንዳንዴ ነው ማለተ ነው፡በጥያቄ ቁጥር 5 የቀረበው ጥያቄ እንደሚያሳው የተማሪው መማሪያ መፃህፍ፣ የመምህሩ መምሪያ እና መርሃ ትምህርቱ አንብቦ የመረዳትና የመፃህፍ ክሂሎችን እርስ በእርስ ተያይዘው እንዲቀርቡ በማድረግ የመማር ማስተማር ዘዴን ለመምህራኑ አጋዥ ነው ተብሎ በሚጠየቁ ጊዜ 2(66.67%) አጋዥ ነወ በማለት ሲመልሱ  1(33.33%) አጋዥ አይደለም በማለት የመለሱ ናቸው፡፡ከዚህ መረዳት እንደሚቻለው የማንበብና የመፃፍ ክሂልን አቀናጅተው በመምህሩ መምሪያ በተማሪ መጸሐፍ አቀናጅተው የሚያስተምሩት ትነሽ መሆናቸው ነው፡፡

በጥያቄ ቁጥር 6 የቀረበው ጥያቄ እንደሚያሳው አንብቦ መረዳትና የመፃፍ ክሂል ተቀናጅተው ቢቀርቡ ተማሪዎች የቋንቋ ችሎታ ላያ ለውጥ ይመጣል በማለት የመለሱት 3(100%)ናቸው፡፡ ከዚህ መረዳት እንደሚቻለው የማንበብና የመፃፍ ክሂልን አቀናጅተው ማስተማር በተማሪዎች ላይ ለውጥ ያመጣል፡፡

በጥያቄ ቁጥር 7 የቀረበው ጥያቄ እንደሚያሳው የመምህሩን መምሪያ መጸሐፍ ይጠቀማሉ?የማንባብና የመፃህፍ ክሂልን ቅንጅታዊ ትምህርት እንዴት ያቀርበዋል ተብለው በሚጠየቁበት ጊዜ  2(66.67%) አቀናጅተን  ነው የማስተምረው ሲሉ መልሳቸዉን የሰጡት 1(33.33%)  በተናጥል ነው የማናቀርበው ሲሉ ገልፅዋል፡፡

## 4.4 ከተማሪዎች ቃል መጠይቅ የተገኘ የመረጃ ትነተና

ከዚህ በታቸች የተዘረዘረው የተማሪዎች ቅድመ ትምህርት ቃለ መጠይቅሲሆን በ 4 ተማሪዎች የተሰጠ ቃለመጠይቅ እንደሚቀርብና ትንተናዉም ከዚህ በታች በጽሁፍና በሠንጠረዥ ተተንትኗል፡፡

ልቃለ መጠይቅ የተመረጡ 4ቱ ተማሪዎች አንብቦ መረዳትና የመፃፍ ክሂሎችን ትምህርት በቅንጅት በመማራቸው ያገኙት አዲስ ነገር ወይንም፡፡ ያጋጠማቸው ችግር ምን እንድሆነ እንዲገልፁ ተጠይቀዋል፡፡ ከሰጡት ምላሽ ውስጥ መደበኛ የመማሪያ መፅሐፍ አዘገጃጀትና አቀራርቡ ችግር አለበት ፡፡ በመሆኑም ከምን ተነስተን ምን እንድምንፅፍና እንድናነብ የሚያስጨንቅ ነበር፡፡ በማለት ገልፀዋል፡፡ በቅንጅት የትምህርት አቀራረብ ግን እያነበብን መፃፍ/ እየፃፍን ማንበብ መሆኑ ትልቅ በመነቃቃት ፈጥሮልናል፡፡ በማለት ለውጥ እንዳለው ገልፀዋል፡፡

- በተማሪዎች የተሰጠ ትነተና የማንበብና የመፃፍ ክሂል በቅንጅት የተቀመጠ የለም እኔ እስካሁን ድረስ በ9ኛክፍል አማርኛ መጸሐፍ ውስጥ የማንበብና የመፃፍ ክሂል ለየብቻ የተቀመጡ ናቸው፡፡የማንበብና የመፃፍ ክሂልን ተቀናጅተው የቀረበ መልመጃ የለዉም፡፡
- የማንበብና የመፃፍ ክሂልን በመጸሐፍ ውስጥ የተቀመጡት ለየብቻ እንጅ መልመጃዎች በአንድላይ አልተቀመጡም፡፡
- የማንበብና የመፃፍ ክሂልን በቅንጅት ቢሰጡ አሪፍ ነገር ነው ምክንያቱም ሁለቱም ተያያዥነት ስላላቸው ባይነጣጠሉ የተሸለ ነው፡፡
- የማንበብና የመፃፍ ክሂልን በቅንጅት ብንማር ጥቅም አለው ምክንያቱም አንድ ተማሪ የማንብና የመፃፍ ክሂሉን ለማዳበር መማር አለበት እሱም ጥሩ አንባቢና ጥሩ ፀሀፊ እንዲወጣዉ ይረደዋል፣ አንድ ተማሪ አንድን ምንባብ ከነበበ ቡኃላ ያነበበውን በፅሁፍ ቢያሰቀምጠው የተሻለ ይሆናል፡፡

❖ የማንበብና የመፃፍ ክሂል በቅንጅት የተቀመጠ የለም እኔ እስካሁን ድረስ በ9ኛ አማርኛ መጸሐፍ ውስጥ የማንበብና የመፃፍ ክሂል ለየብቻ የተቀመጡ ናቸው፡፡የማንበብና የመፃፍ ክሂልን የቀረብ መልመጃ የለዉም፡፡ለምሳሌ ክፍል አንድ የመፃፍ ከሆን ክፍል ሁለት ደግሞ የማንበብ ነው፡፡የማንበብና የመፃፍ ክሂልን በመጸሐፍ ውስጥ የተቀመጡ መልመጃዎች በአንድላይ አልተቀመጡም፡፡

❖ የማንበብና የመፃፍ ክሂልን በቅንጅት ቢሰጡ አሪፍ ነገር ነው ምክንያቱም ሁለቱም ተያያዥነት ስላላቸው ባይነጣጠሉ የተሸለ ነው፡፡ማንበብ ካለ መፃፍ አለ መፃፍ ካለ ደግሞ

ማንበብ አለ ስለዚህ ሁለቱም አብረዉ ጎን ለጎን የሚሄዱ ናቸው፡፡

❖ የማንበብና የመፃፍ ክሂልን  በቅንጅት ብትማር ጠቅም አለው ምክንያቱም አንድ ተማሪ የማንበብና የመፃፍ ክሂሉን ለማዳበር መማር አለበት እሱም ጥሩ አንባቢና ጥሩ ፀሀፊ እንዲወጣዉ አንድ ተማሪ አንድን ምንባብ ከነበበ ቡኃላ የነበበውን በፅሁፍ ቢያስቀምጠው የተሻለ ይሆናል፡፡ሁለቱም በአንድላይ ቢሰጥ የተሸለ የተማሪዎችን ችሎታ ሊጨምሩ ይችላሉ፡፡

➢ የማንበብና የመፃፍ ክህል በቅንጅት የተቀመጠ የለም እኔ እስካሁን ድረስ በ9ኛለ አማርኛ መጸሐፍ ውስጥ የማንበብና የመፃፍ ክሂል ለየብቻ የተቀመጡ ናቸው፡፡የማንበብና የመፃፍ ክሂልን የቀረብ መልመጃ የለዉም፡፡ለምሳሌ ክፍል አንድ የመፃፍ ከሆን ክፍል ሁለት ደግሞ የማንበብ ነው፡፡የማንበብና የመፃፍ ክሂልን በመጸሐፍ ውስጥ የተቀመጡ መልመጃዎች በአንድላይ አልተቀመጡም፡፡ መምህሮቹ ለኛ በሚጠቅም ሁኔታ አመቻችተው በአንድ ላይ ይሰጡናል፡፡

➢ የማንበብና የመፃፍ ክሂልን በቅንጅት ቢሰጡ አሪፍ ነገር ነው ምክንያቱም ሁለቱም ተያያዥነት ስላላቸው ባይነጣጠሉ የተሸለ ነው፡፡ማንበብ ካለ መፃፍ አለ መፃፍ ካለ ደግሞ ማንበብ አለ ስለዚህ ሁለቱም አብረዉ ጎን ለጎን የሚሄዱ ናቸው፡፡

➢ የማንበብና የመፃፍ ክሂልን በቅንጅት ብትማር ጠቅም አለው ምክንያቱም አንድ ተማሪ የማንበብና የመፃፍ ክሂሉን ለማዳበር መማር አለበት እሱም ጥሩ አንባቢና ጥሩ ፀሀፊ እንዲወጣዉ አንድ ተማሪ አንድን ምንባብ ከነበበ ቡኃላ የነበበውን በፅሁፍ ቢያስቀምጠው የተሻለ ይናል፡፡ሁለቱም በአንድላይ ቢሰጥ የተሸለ የተማሪዎችን ችሎታ ሊጨምሩ ይችላሉ፡፡ለምሳል ቃለ ጉባኤ ብንይዝ የተነበበውን ነው የምንፅፈው ስለዚህ አቀናጅቶ መማር የተሸለ ነው፡

✓ የማንበብና የመፃፍ ክሂል በቅንጅት የተቀመጠ የለም እኔ እስካሁን ድረስ በ9ኛለ አማርኛ መጸሐፍ ውስጥ የማንበብና የመፃፍ ክሂል ለየብቻ የተቀመጡ ናቸው፡፡የማንበብና የመፃፍ ክሂልን የቀረብ መልመጃ የለዉም፡፡ለምሳሌ ክፍል አንድ የመፃፍ ከሆን ክፍል ሁለት ደግሞ የማንበብ ነው፡፡የማንበብና የመፃፍ ክሂልን በመጸሐፍ ውስጥ የተቀመጡ መልመጃዎች በአንድላይ አልተቀመጡም፡፡

✓ የማንበብና የመፃፍ ክሂልን  በቅንጅት ብንማር ጠቅም አለው ምክንያቱም አንድ ተማሪ የማንበብና የመፃፍ ክሂሉን ለማዳበር መማር አለበት እሱም ጥሩ አንባቢና ጥሩ ፀሀፊ እንዲወጣዉ አንድ ተማሪ አንድን ምንባብ ከነበበ ቡኃላ የነበበውን በፅሁፍ ቢያስቀምጠው

የተሻለ ይሆናል፡፡ሁለቱም በአንድላይ ቢሰጥ የተሸለ የተማሪዎችን ችሎታ ሊጨምሩ ይችላሉ፡፡

## 4.5 ከሙከራ ቡድኑ የተወሰደ የድህረ ትምህርት ቃለ መጠይቅ ትንተና

### ቃለ መጠይቁ የተደረገበት ቀን ግንቦት 15 ሰዓት 4:00

- ✓ ለአንድ ወር የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን የተማርክበት መንገድ እንዴት ተመለከትከው?

  ለአንድ ውር የተማርኩት ትምህርት በጣም ጥሩ ነው ፡፡ እኔም እንደ ተማሪ የተለያዩና ብዙ ልምዶችን ቀስሜበታለሁ ስለዚህ ጥሩ ነበር፡፡

- ✓ የዚህ ወር ትምህርት አቀራረብ ከዚህ በፊት ከተማርከው የትምርት አቀራረብ ጋር ሲነፃፀር ልዩነቱ ምንድነው? የትኛው ይሻላል ?

  ከዚህ በፊት የሚሰጠው ትምህርትም ሆነ በመፀሀፉ ውስጥ የቀረበውም አራቱ ክሂሎች ተያይዘው ሳይሆን ለየብቻ ነው ፡፡ ምክኒያቱም ሁሌም የምንማረው በመፀሃፉ ስለሆነ የቀረበበት ምንገድ ደግሞ ለየብቻ ስለሆነ ነው፡፡ አሁን ግን ማንበብና መፃፍን በአንድ ላይ በመጣመር ነው ልዩነቱ ይህ ነው፡፡ የትኛው ይሻላል ለሚለው ጥያቄ በአንድላይ የሚሰጠው ይሻላል ምክኒያቱም የሚሰጠው ትምህርት ተደጋጋሚነት ያለው ነው ማለትም እንድንፅፍ እንደገና እንድናነብበቡድን እንድንወያይ ደግመን እንድንፅፍ እንድንወያይ ይረዳናል፡፡በመሆኑም ሁለቱ ስለማይለያዩ በጥምረት የሚሰጠው ትምህርት የበለጠ የተሻለ ነው፡፡

- ✓ በቅንጅት የሚሰጠው ትምህርት እንዲሰጥ ምን ምን መደረግ አለበን?

  በመጀመሪያ መፃህፉ በቅንጅት ለማስተምር እንዲመች ተደርጎ ቢዘጋጅ፡፡ ለሚያስተምሩ መምህራን ስልጠና ቢሰጥ እና የሚያስተምሩ መምህራን ከመፀሀፉ ውጭ በራሳቸው ስነ-ዘዴ በማቀናጀት ቢያስተምሩ የሚመረጥ ይመስለኛል፡፡

- ✓ አሁን በተማርክበት መንገድ በሁሉም የክፍል ደረጃ ትምህርቱ በቅንጅት ቢሰጥ ምን ለውጥ ሊመጣ ይችላል ብለህ ትገምታለህ ?

  ትምህርቱ አሁን በተማርኩበት መንገድ ቢሰጥ የተማሪዎች የማንበብ ችሎታ ይዳብራል፡ ፡ ለማንበብና ለመፃፍ አይቸገሩም ፡፡ በጠበቀ ትስስር ስለሚሰጥ የማንበብና የመፃፍ ክህሎታቸው ይዳብራል፡፡ በአጠቃላይ አንብቦ የመረዳት ችሎታም ይኖራቸዋል፡፡

የማንበብና የመፃፍ ክሂሎን ለማስተማር የሚቀርቡትይዘቶች የክሂሎቹን ደረጃዎች ለመተግበር ፣ንዑሳን ክሂሎችን ለማስተማር የሚያስችል ፣ከእዉነተኛው አለም ሃሳብ ጋር በመለዋወጥ በአቅርቢያቸው የሚመሳሰሉ፣የተማሪዎች ፍላጎት ፣ገጠመኝና የክፍል ደረጃዎችን ያገናዘቡ፣ ለውይይት የማንበብ የሚጋብዙ ሊሆኑ እንደሚገባ በተዛማጅ ጸሑፍ ቅኝት ውስጥ ተገልፀዋል፡፡ ስለዚህ የማንበብና የመፃፍ ክሂልን አቀናጅቶ ለማስተማር የሚቀርቡበትን ይዘቶች መፈተሽ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በተተኳሪ መምህራን ዘጠኝ ያህል ጊዝ በተካሄደው ምልከታ የቀረቡት ይዘቶች የማንበብና የመፃፍ ክሂል ደረጃዎችን ፍላጎት ለማነሳሳት ያለቸው ሚና ምን እንደሚመስል ለመፈተሽ በተደረገው ምልከታ የተገኘው መረጃ  የሚከተለውን ይመስላል፡፡

**ሠንጠረዥ 3 ፡- የእለቱ ትምህርት  ይዘት የማበብና የመፃፍ ክሂል ደረጃዎችን ለማከናወን ናየተማሪዎችን ፍላጎት ለማነሳሳት ያለው ሚና ምን እንደሚመስል ለመፈተሽ በተደረገው ምልከታ የተገኘው ምላሽ**

| ተ.ቁ | የቀረቡ ጥያቄዎች | ድግግሞሽ | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሀ በጣም ከፍተኛ | | ለ ከፍተኛ | | ሐ መካከለኛ | | መ ዝቅተኛ | | ሠ በጣም ዝቅተኛ | |
| | | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % |
| 4 | መ/ሩ(ሯ) ተማሪዎች አንድን ምንባብ ከአነበቡ በኃላ በራሳቸው አባባል እንዲፅፉ የማድረግ ሁኔታዎች | - | - | 3 | 33.3 | 2 | 22.2 | 4 | 44.4 | - | - |
| 5 | መ/ሩ(ሯ)ተማሪዎች የሚፅፋቸውን ፅሁፎች ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያነቡላቸው የማድረግ ሁኔታ | - | - | 5 | 55.5 | 1 | 11.1 | 2 | 22.2 | 1 | 11.1 |

ከላይ የቀረበው የምልከታ ሠንጠረዥ እንደሚያመለክተው በሶስት መምህራን በተደረገው 9 ተከታታይ ምልከታዎች ላይ የክፍል ጊዜው ይዘት ማንበብና የመፃፍ ክሂልን ለማቀናጀት ያለው አስተዋፆ ምን እንደሚመስል ለቀረበው ጥያቄ የተገኘው ምላሽ፡፡ ምልከታዎች ላይ የክፍለ ጊዜው

ይዘት በተራ ቁጥር 4 መ/ሩ(ሯ) ተማሪዎች አንድን ምንባብ ከአነበቡ በኃላ በራሳቸው አባባል እንዲፅፉ የማድረግ ሁኔታዎች 3(33.3%) ከፍተኛ፣ 2(22.2%)መካከለኛ፣ 4(44.4%)ዝቅተኛና እንደሆነ ለመመልከት ችያለሁ።

በተራ ቁጥር 5 ላይ ለቀረበው ጥያቄ እንደሚያሳየው መ/ሩ(ሯ)ተማሪዎች የሚፅፋቸውን ፅሁፎች ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያነቡላቸው የማድረግ ሁኔታ5(55.56%) ከፍተኛ፣ 1(11.1%)መካከለኛ፣ 2(22.2%)ዝቅተኛና 1(11.11%)በጣም ዝቅተኛ አንደሆነ ለመመልከት ተችሏል።

ጠቅለል ባለ መልኩ ክፍል ጊዜው ይዘት የማበብና የመፃፍ ክሂልን ለማቀናጀትና ለማዳበር ያለው አስተዋፆ ምን አንድሚመስል ለመመርመር በተደረገው ምልከታ የተገኘው ምላሽ እንደሆነ ነው።

## 4.5.1. ከመምህራን ቃለ መጠይቅ የተገኘ ምላሽ

የዘጠንኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የማንበብና መፃፍ ክሂልን አቀናጅተው ለማስተማር የሚያቀርቧቸው ይዘቶች ምን እነደሚመስሉ ለማወቅ በተደረገው ቃለ መጠይቅ የሚከተለው ምላሽ ሊገኝ ችሏል። የማንበብና የመፃፍ ክሂልን በማቀናጀት ለማስትማር የሚያቀርቧቸው ይዘቶች ክሂሎቹን በተገቢው ለማቀናጀትና ለማዳበር ያላቸው እገዛ ምን ያህል ነው? ለሚለው ጥያቄ ሶስቱም መምህራን ክሂሎቹን በቅንጅት ለማስተማርና ለማዳበር የሚያቀርቧቸው ይዘቶች ያላቸው ሚና ክሂሎች ከፍተኛ እንደሆነ ገልፀዋል።

በዚህ ክፍል የማበብና የመፃፍ ክሂልን በቅንጅት ለማስተማር የማያቀርቧቸው ይዘቶች ከተማሪዎች ፍላጎት ፣ዳራና ችሎታ ጋር የተዛመዱ እንደሆኑ ጥረት ያደርጋሉ ? የሚል ጥያቄ ቀርቦላቸው ሶስቱም መምህራን የተማሪዎች ዳራ ለመጠበቅ ተማሪዎች እነማን ናቸው ? ከየት ነው የመጡት? ወዘተ… የመሳሰሉትን ነጥቦች በማንሳት የማንበብና የመፃፍ ክሂልን ቅንጅታዊ ትምህርቱ የተማሪዎቹን ፍላጎት ፣ችሎታና ዳራ መሰረት ያደረገ እነደሆን ጥረት እነደሚያደረጉ ገልጸዋል።

ከላይ ከምልከታ፣ከተማሪዎች የፅሁፍና ከመምህራን ቃል መጠይቅ የተገኘውን ምላሽ ተመሳሳይነት ይታይባቸዋል።መምህራን የማንበብና የመፃፍ ክሂልን በቅንጅት ለማስተማር የሚያቀርቡበት ይዘቶች ከተማሪዎች ፍላጎት ፣ገጠመኝና ችሎታ ጋር የማይጣጣም እንዲሆም

ተማሪዎችን ለማሳተፍ ያላቸው አስተዋፆ ዝቅተኛ እንደሆነ ከምልከታውና ከቃለ መጠይቅየተገኘው መረጃ ያስረዳል፡፡ከመምህራን ቃለ መጠይቅ የተገኘ ምላሽም ሁሉም መምህራን ብቻ ጥረት ማድረጋቸውን ገልፀዋል፡

**ሠንጠረዥ 4 ፡- የእልቱ ትምህርት የማንበብና የመፃፍ ክሂልን ለማቀናጀትና ለማዳበር ያላቸው ሚና ምን እንደሚመስል ለማወቅ በተደረገው ምልከታ የተገኘ ምላሽ**

| ተ.ቀ | የመከታተያ ነጥቦች | ድግግሞሽ | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በጣም ከፍተኛ | | ከፍተኛ | | መካከለኛ | | ዝቅተኛ | | በጣም ዝቅተኛ | |
| | | በቁጥ | % | በቁጥ | % | በቁጥ | % | በቁጥ | % | በቁጥ | % |
| 6 | አንብቦ መረዳትና የመፃፍ ክሂልን በቅንጅት ለማስተማር የሚረዱ ብልሃቶች ለምሳሌ ፡-ጥያቄ መጠየቅ ፤ መተንበይ፤ መገመት ፤ማብራራት ፤ መተርጎምና ያጠቃልል ነው፡፡ | - | - | 4 | 44.4 | 3 | 33.33 | 1 | 11.1 | 1 | 11.1 1 |
| 7 | መ/ሩ(ሯ)አንብቦ መረዳትን ከመፃፍ ክሂል ጋር ትኩረት በመስጠት የማቀናጀት ሁኔታ | - | - | 3 | 33.33 | 1 | 11.1 | 5 | 55.5 | - | - |

ከላይ ለቀረበው ሠንጠረዥ እንደምንመለከተው የክፍል ስራዎች የማንበብና የመፃፍ ክሂል ለማቀናጀትና ለማዳበር ያላቸውን ብቃት ለመፈተሽ በተደረገው ተከተታይ ምልከታ የተገኘ ምላሽ በተራ ቁጥር 6 የቀረበው ጥያቄ እንደሚያሳየው አንብቦ መረዳትና የመፃፍ ክሂልን በቅንጅት ለማስተማር የሚረዱ ብልሃቶች ለምሳሌ ፡-ጥያቄ መጠየቅ ፤ መተንበይ፤ መገመት ፤

ማብራራት ፤መተርጎምን ያጠቃልል ነው4(44.4%) ከፍተኛ፣ 3(33.3%)መካከለኛ፣ 1(11.1%) ዝቅተኛና 1(11.1%)በጣም ዝቅተኛእንደሆነ ለመመልከት ችያለሁ፡፡

በተራ ቁጥር7ላይ ለቀረበው ጥያቄ እንደሚያሳየው መ/ሩ(ሯ) ተማሪዎች የሚፅፋቸውን ፅሁፎች ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያነቡላቸው የማድረግ ሁኔታ 3 (33.3%) ከፍተኛ፣ 1(11.1%) መካከለኛ፣ 5(55.5%) ዝቅተኛ አንደሆነ ለመመለከት ተችሏል፡፡ ከነዚህም የምንረዳው የክፍል ስራዎችን የማንበብና የመፃፍ ክሂልን ለማቀናጀትና ለማዳበር ያላቸው አስተዋፆ ከፍተኛ ቢሆንም ተማሪዎችና የቡድን ውይይቶች ያላቸው ብቃት ዝቅተኛ እንደሆነ ነው፡፡ይህ ደግሞ ተማሪዎች የማንበብና መፃፍ ክሂል ችሎታቸውን ያደብራሉ ለማለት አያሰደፍርም፡፡

### 4.5.2. ከተማሪዎች የቅድመና ድህረ ፈተና የተገኘ ውጤት ትንተና

የማንበብና የመፃፍ ክሂልን አዋህዶ ማስተማር ክሂሎችን በማጎልበት ረገድ የሚኖረዉን ሚና በሙከራዊ ጥናት ማረጋገጥ የጥናቱ አቢይ ዓላማ ነው፡፡ በመሆኑም ዓላማውን ለመተግበር ያስችል ዘንድ በምልከታ ና በቃል መጠይቅ አማካይነት ከተገኙት ግባዓቶች ተጨማሪ ተማሪዎችን በሁለት ዙሮች ማለትም በቅድመና ድህረ የፈተና አሰጣጥ ሂደት በማሳተፍ መረጃ ማካተት ተችሏል፡፡ በዚህ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ የሚገኘውን ውጤት በአግባቡ ለመረዳትና ለመለየት የፈተና አሰጣጡ ሂደት ላይ በትኩረት ተሰርቷል፡፡ በዚሁ መሰረትም በመጀመሪያ ለመረጃ ስብሰባው የተመረጡትን ተማሪዎች ምንም ዓይነት የማስተማር ድጋፍ ሳይሰጣቸው ፈተናውን እንዲወሰወዱ ተደርጓል፡፡ በሁለተኛ ዙር በተሰጠው ፈተና በአንጻሩ ተማሪዎቹ በተመረጡ የትምህርት ይዘቶች ላይ ልዩ ልዩ የማስተማር ዘዲዎችን በመጠቀም ለአንድ ወር ያህል ከተማሩ እና ድጋፍ ካገኙ በኋላ ፈተናውን መውሰድ ችለዋል፡፡ ይህን የመረጃ አሰባሰብ ሂደት ተከትሎ የተገኘውን ጠቅላላ ዝርዝር ውጤት እና የማጠቃለያ ሃሳብ በተመለከተ ቀጥሎ በቀረቡት ሁለት ተከታታይ ሰንጠረዦች ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡

### ሠንጠረዥ 5 ፡ - የቅድመ እና ድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት ዝርዝር

| ቅድመ ትምህርት ፈተና ውጤት | | | ድህረትምህርት ፈተና ወጤት | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ተቁ | መለያ ኮድ | ውጤት ከ100% | ተቁ | መለያ ኮድ | ውጤት ከ100% |
| 1 | 01-2 | 32 | 1 | 0.1-ለ | 74 |
| 2 | 0.2-2 | 27 | 2 | 0.2-ለ | 62 |
| 3 | 0.3-2 | 32 | 3 | 0.3-ለ | 51 |
| 4 | 0.4-2 | 51 | 4 | 0.4-ለ | 30 |
| 5 | 0.5-2 | 52 | 5 | 0.5-ለ | 67 |
| 6 | 0.6-2 | 51 | 6 | 0.6-ለ | 61 |
| 7 | 0.7-2 | 52 | 7 | 0.7-ለ | 57 |
| 8 | 0.8-2 | 46 | 8 | 0.8-ለ | 35 |
| 9 | 0.9-2 | 35 | 9 | 0.9-ለ | 58 |
| 10 | 10-2 | 30 | 10 | 10-ለ | 70 |
| 11 | 11-2 | 22 | 11 | 11-ለ | 56 |
| 12 | 12-2 | 41 | 12 | 12-ለ | 60 |
| 13 | 13-2 | 53 | 13 | 13-ለ | 100 |
| 14 | 14-2 | 41 | 14 | 14-ለ | 84 |
| 15 | 15-2 | 36 | 15 | 15-ለ | 52 |
| 16 | 16-2 | 41 | 16 | 16-ለ | 48 |
| 17 | 17-2 | 52 | 17 | 17-ለ1 | 71 |
| 18 | 18-2 | 25 | 18 | 18-ለ | 67 |
| 19 | 19-2 | 48 | 19 | 19-ለ | 62 |
| 20 | 20-2 | 27 | 20 | 20-ለ | 57 |
| 21 | 21-2 | 46 | 21 | 21-ለ | 75 |
| 22 | 22-2 | 33 | 22 | 22-ለ | 89 |
| 23 | 23-2 | 48 | 23 | 23-ለ | 87 |
| 24 | 24-2 | 31 | 24 | 24-ለ | 47 |
| 25 | 25-2 | 52 | 25 | 25-ለ | 67 |
| 26 | 26-2 | 58 | 26 | 26-ለ | 83 |
| 27 | 27-2 | 53 | 27 | 27-ለ | 58 |
| 28 | 28-2 | 27 | 28 | 28-ለ | 66 |
| 29 | 29-2 | 58 | 29 | 29-ለ | 71 |
| 30 | 30-2 | 37 | 30 | 30-ለ | 95 |
| 31 | 31-2 | 66 | 31 | 31-ለ | 79 |
| 32 | 32-2 | 53 | 32 | 32-ለ | 76 |
| 33 | 33-2 | 53 | 33 | 33-ለ | 76 |
| 34 | 34-2 | 13 | 34 | 34-ለ | 78 |
| 35 | 35-2 | 67 | 35 | 35-ለ | 66 |
| 36 | 36-2 | 63 | 36 | 36-ለ | 77 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 37 | 37-2 | 63 | 37 | 37-ለ | 70 |
| 38 | 38-2 | 40 | 38 | 38-ለ | 65 |
| 39 | 39-2 | 26 | 39 | 39-ለ | 41 |
| 40 | 40-2 | 50 | 40 | 40-ለ | 63 |
| 41 | 41-2 | 40 | 41 | 41-ለ | 77 |
| 42 | 42-2 | 30 | 42 | 42-ለ | 45 |
| 43 | 43-2 | 45 | 43 | 43-ለ | 61 |
| 44 | 44-2 | 57 | 44 | 44-ለ | 44 |
| 45 | 45-2 | 72 | 45 | 45-ለ | 59 |
| 46 | 46-2 | 56 | 46 | 46-ለ | 85 |
| 47 | 47-2 | 70 | 47 | 47-ለ | 78 |
| 48 | 48-2 | 48 | 48 | 48-ለ | 68 |
| 49 | 49-2 | 66 | 49 | 49-ለ | 97 |
| 50 | 50-2 | 65 | 50 | 50-ለ | 80 |

**ሠንጠረዥ 6፡ - በሁለት ዙር የተገኘው ውጤት ንጽጽራዊ ትንተና**

| የምዘና ሂደቶች | ዝቅተኛ ውጤት ከ100 በቁጥር | ከፍተኛ ውጤት ከ100 በቁጥር | ከ50%በታች ያስመዘገቡ ተማሪዎች ብዛት በቁጥር | ከ50% በታች ያስመዘገቡ ተማሪዎች ብዛት በ% | ከ50% በላይ ያስመዘገቡ ተማሪዎች ብዛት በቁጥር | ከ50% በላይ ያስመዘገቡ ተማሪዎች ብዛት በ% | የተገኘው ጥቅል አማካይ ውጤት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የቅድመ ፈተና ውጤት ዝርዝር | 13 | 72 | 26 | 52 | 24 | 48 | 45.6 |
| የድህረ ፈተና ውጤት ዝርዝር | 32 | 100 | 7 | 14 | 43 | 86 | 66.9 |

ከላይ በዝርዝር በሁለቱ ሰንጠረዦች ማለትም ሰንጠረዥ 7 እና 8 በተገኘው መረጃ መሰረት በጥናቱ የተካተቱትን የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ውጤት በቅድመና ድህረ ፈተና ውጤታቸው በማወዳደር የተገኘው ውጤት እንደሚያመለክተው በመደበኛዉ ክፍለ ጊዜ፣ለክፍል ደረጃዉ በተዘጋጀው መማሪያ መጻሃፍና በተለመደው የማስተማር ዘዴ ብቻ ተምረው ለፈተና ከተቀመጡት ተማሪዎች መካከል የተገኘው ከፍተኛ ውጤት 72 ከመቶ ሲሆን ዝቅተኛው ደግሞ 13 ከመቶ ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ በዚሁ መርሀ-ግብር የተገኘው ውጤት እንደሚያሳየው ከተፈታኞቹ መካከል 26ቱ ወይም 52% ከ 50% በታች ያስመዘገቡ ሲሆን፤24 ተማሪዎች

ወይም 48% የሚሆኑት ብቻ የማለፊያ ውጤት አግኝተዋል። ከዚሁ ጋር ተያይዞ በዚህ የምዘና ሂደት ወቅት  የታየው ጥቅል አማከይ ውጤትም 45.6 ሆኖ ተመዝግቧል።

ከዚህ በተቃራኒ ከተለመደው የማስተማር ዘዴ ወጣ ብሎ የማንበብና የመፃፍ ክሂልን አዋህዶ ማስተማር ስነ ዘዴን በተከተለ መልኩ  ለአንድ ወር ያህል ተምረው የተፈተኑት ተማሪዎች የተሻለ ውጤት ማስመዝገብ ችለዋል። በዚሁም መሰረት ከማጠቃለያ ሰንጠረዡ ለመረዳት እንደሚቻለው ዝቅተኛው ውጤት 32 ከመቶ ሲሆን ከፍተኛው ደግሞ 100 ፐርሰንት ሆኖ ተመዝግቧል። የተማሪዎቹን ውጤት እና ተሳትፎ ስንመለከት ከተፈታኞቹ 43 ያህሉ ወይም 86% ከመደበኛው የማለፊያ ውጤት ወይም 50% በላይ አስመዝገበዋል። በአንጻሩ ደግሞ 7 ተማሪዎች ወይም 14% የሚሆኑት ብቻ ከ50%  በታች ማስመዘገባቸው ተመላክቷል። በዚሁ የድህረ ፈተና ወቅት የተመዘገበው ውጤትም 66.9 ሲሆን ከመጀመሪያ አማካይ ውጤት ጋር ሲነጻጸር የ 21.3  ሆኖ ተመዝግቧል።

በሰንጠረዡ የተመለከቱት መረጃዎችና የቀረበው ትነተና እንደሚያመለክተው የማንበብና የመፃፍ ክሂልን አዋህዶ  የማስተማር ስነ ዘዴ ልማዳዊ ከሆነው የማስተማር ሂደት በእጅጉ የተሻለና ለተማሪዎች የውጤት መሻሻልም ያለው ፋይዳ የላቀ መሆኑንን ነው።

የቋንቋ ክሂሎችን በቅንጅት በሚቀርቡበት ሃሳብን በቃል በማቅረብ የፕሮጀክት ስራ በመስራት ሚና ነጠቅ በማከናወን ፣ልቦልድ ማስነበብና፣የግል ህይወት ታሪክ የመፃፍ ፣ቃለጉባኤዬ ማስያዝ የመሳሰሉትን ወዘተ…መሆናቸውን ተገልፀዋል።በዚህ ክፍልም ተተኳሪ መምህራን የማንበብና የመፃፍ  ክሂልን ለማቀናጀት ሚጠቀሙባቸው ስልቶችን ለማወቅ ከምልከታ፣ከተማሪዎች የቃለ መጠይቅ ከመምራን ቃለ መጠይቅ የተገኘ መረጃዎች እንደሚከተለው ተተንትነው ቀርበዋል።

## 4.6 ከምልከታ የተገኘ መረጃ ትንተና

በጉራጌ ዞን በተጠመረጡ ዘጠንኛ ክፍለ በአማርኛ ቋንቋ መምህራን  የማንበብና የመፃፈ ክሂልን አቀናጅቶ ለማስተማር የሚጠቀምባቸውን ስልቶች ለማወቅ በተደረገው ምልከታ የተገኘው ምላሽ እነደሚከተለው ቀርቧል።

**ሠንጠረዥ 7 ፡-መምህራን የማንበብና የመፃፍ ክሂልን አቀናጅቶ ለማስተማር የሚጠቀሙባቸው ስልቶችን ምን እንደሚመስሉ ለማወቅ በተደረገው ምልከታ የተገኘ ምላሽ፡፡**

| ተ.ቀ | የመከታተያ ነጥቦች | ድግግሞሽ | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በጣም ከፍተኛ | | ከፍተኛ | | መካከለኛ | | ዝቅተኛ | | በጣም ዝቅተኛ | |
| | | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % |
| 8 | መ/ሩ(ሯ) ተማሪዎች ሃሳባቸውን በፅሁፍ እንዲገልፁ በቂ ጊዜ የመስጠት ሁኔታ | - | - | 2 | 22.22 | 1 | 11.11 | 4 | 44.4 | 1 | 11 .1 |
| 9 | የሚሰጡ የክፍል ስራዎች አምብቦ መረዳትና የመፃፍ ክሂልን ለማቀናጀትና ለማዳበር ያላቸው ብቃት | - | - | 2 | 22.22 | 1 | 11.11 | 4 | 44.4 | 1 | 11 .1 |

ከላይ ከቀረበው ሠንጠረዥ መረዳት እንደሚቻለው መምህራን የማንበብና የመፃፍ ክሂልን በቅንጅት ለማስተማር ከመማሪያ መጽሐፍ በተጨማሪ ሌላ የማስተማሪያ መሳሪያ መጠቀም እንደ ግጥም ማስነበብ ና ማጻፍ፣ልቦለድ ማስነበብና ማጻፍየመሳሰሉት ወዘተ... ናቸው፡፡

በተራ ቁጥር 8 የቀረበው ጥያቄ እንደሚያሳየው መ/ሩ(ሯ) ተማሪዎች ሃሳባቸውን በፅሁፍ እንዲገልፁ በቂ ጊዜ የመስጠት ሁኔታ 2(22.2%) ከፍተኛ፣ 1(11.1%) መካከለኛ፣ 4(44.4%) ዝቅተኛና 1(11.1%) በጣም ዝቅተኛ አንደሆነ ለመመልከት ችያለሁ፡፡

በተራ ቁጥር 9 ላይ የቀረበው ጥያቄእንደሚያሳየው የሚሰጡ የክፍል ስራዎች አምብቦ መረዳትና የመፃፍ ክሂልን ለማቀናጀትናለማዳበር ያላቸውብቃት 2(22.2%) ከፍተኛ፣ 1(11.1%) መካከለኛ፣ 4(44.4%) ዝቅተኛና 1(11.1%) በጣም ዝቅተኛ አንደሆነ ለመመልከት ችያለሁ፡፡

## 4.7 ከመምህራን ቃል መጠይቅ የተገኘ ምላሽ

በዚህ ክፍል መምህራን የማንበብና የመፃፍ ክሂልን ለማቀናጀት የሚጠቀሙባቸውን ብልሀቶች ለመፈተሽ የቃል መጠይቅ ለመምህራን ቀርቦ የተገኘው ምላሽ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

በመማሪያ መጸሐፍ ያሉትን የማንበብና የመፃፍ ክሂልንመልመጃዎች የሚያቀርቡባቸው እንዴት ነው ? የሚል ጥያቄ ቀርቦላቸው ሶስቱም መምህራን በመፅሃፍ ያሉትን መልመጃዎች ክሂሎችን ለማስተማር ተስማሚ ስለሆነ እነዳለ እንደሚያቀርቧቸው ገልፀዋል፡፡

የማንበብና የመፃፈ ክሂልን በቅንጅት በሚያስተምሩባቸው ጊዜ ተማሪዎች ቋንቋውን ተጠቅመው ሃሳባቸውን እንዲገለጹና እንዲያዳመጡ ለማድረግ ምን አይነት ዘዴ ይጠቀማሉ ? ተበለው ለተጠየቁት ጥያቄ ሶስቱም መምህራን ተመሳሳይ የሆነ መልስ ሰጥተዋል፡፡ይህም በመጽሐፉ ውሰጥ የቀረበዉን የማንበብና የመፃፍ ጥያቄዎችን በቃላቸው እንዲመልሱና አልፎ አልፎም በቡድንና በጥንድ እንዲወያዩ በማድረግ እንደሚለማመዱ ገልጸዋል፡፡ ተማሪዎች ሰውችን ጠይቀው ዋይም ግጥሞችን አንበብው ፅፈው እንዲመጡ ማድረግ ነው፡፡

መምህራን የማንበብና የመፃፍ ክሂልን ለማቀናጀት የሚጠቀሙባቸው ብልሃቶች ምን እንደሚመስሉ ለማወቅ በተደረገው ምልከታ ፡የፅሁፍና የቃል መጠይቀቅ የተገኙት ምላሶች ተመሳሳይነት ይታይባቸዋል፡ይኸውም የማንበብና የመፃፍ ክሂልን መምህራን በቅንጅት በሚያስተምሩበት ጊዜ አብዛኛውን ተግባራዊ የሚያደርጉት ተማሪዎቹን ያነበቡትን በመፃፍ ነው፡ ፡ የማንበብና የመፃፍ ክሂልን በቅንጅት በሚያስተምሩበት ጊዜ ምን አይነት ዘዴ ይጠቀማሉ? የቀረቡት ተብለው መምህራን ለተጠየቁት የቃል ጥያቄ በመፅሀፍ ውስጥ የማንበብና የመፃፍ ጥያቄዎችን እንደሚመለሱት አልፎ አልፎም በቡድን በጥንድ እንዲወያዩ በማድረግ እንዲለማመዱ ምላሽ ስጥተዋል፡፡

በአጠቃላይ ከዚህ የምንረዳው ክሂሎችን አቀናጅቶ ለማስተማር የተለያዩ ስልቶችን ቢኖሩም መምህራን ግን ተማሪዎችን ሃሳባቸውን በቃል እንዲገልፁ ከማድረግ በቀር ልሎቹን ተግባራዊ እንደማያደርጉ ሊረጋገጥ ተችሏል፡፡

## 4.8 መምህራን የማንበብና የመፃፍ ክሂልን ለማቀናጀት የሚያደርጉት ጥረት

የማንበብና የመፃፍ ክሂል ተቀናጅተው እንዲቀርቡ ለማድረግ መምህራን ሚና ወሳኝ ነው፡፡ የቋንቋ ትምህርት ዋና አላማም የተማሪዎችን የተግባቦት ብቃት ማዳበር ማስቻል ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ መምህራን የቡድንና የጥንድ ስራዎችን መስጠት ፣ተማሪዎች እረስ በራስ እንዲወያዩ ፣ ሀሳብ እንዲለዋወጡ በማድረግ ማንበብ፣የተለያዩ ቡድኖችን መመስረት ፣ምቹ ሆኑ የክፍል ውስጥ ሁኔታዎችን መፍጠር መገምገምና መቆጣጠር እንዲሁም ክሂሎችን ለማቀናጀት የሚያግዙ መሳሪያዎችና የትክኖሎጂ ዉጤቶችን መምረጥ ፣እየተጠቀሙበት ያለው የአቀራረብ ዘዴ ክሂሎችን ምን ያህል እያቀናጀ እንደሆነ መገምገም እንደሚኖርባቸው በተዛማጅ ጽሁፍ ቅኝት ውስጥ ተገልጸዋል፡፡ ስለዚህ መምህራን የማንበብና የመፃፍ ክሂልን በቅንጅት ለማስተማር የሚያደርጉትን ጥረት መፈተሸ አስፈላጊ ሆኗል፡፡

በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፈለ ጊዜ በሶስቱም መምህራን በተደረገው የሶስት ተከታታይ ምልከታች መምህራን የማበብና የመፃፍ ክሂልን ለማቀናጀት የሚያደረጉት ሚና ለማወቅ በተደረገው ምልከታ የተገኘው መረጃ ከዚህ ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

**ሠንጠረዥ 8፡-መምህራን የማንበብና የመፃፍ ክሂልን ለማቀናጀት የሚያደረጉትን ጥረት ለመፈተሸ በተደረገው ምለከታ የተገኘ ምላሽ፡፡**

| ተ. ቁ | የመከታተያ ነጥቦች | ድግግሞሽ | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በጣም ከፍተኛ | | ከፍተኛ | | መካከለኛ | | ዝቅተኛ | | በጣም ዝቅተኛ | |
| | | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % |
| 10 | መ/ሩ(ሯ) የሚሰጧቸውን የቤት ስራዎች የአንብቦ መረዳትና የመፃፍ ክሂልን በማቀናጀት የሚሰሩ ነቸው | - | - | 5 | 55.55 | 2 | 22.2 | 1 | 11.1 | 1 | 11.1 |
| 11 | መ/ሩ(ሯ) ከተማሪ መፀሐፍ ውጭየተማሪዎችን የአንብቦ መረዳትና የመፅሃፍ ፍላጎት | - | - | 3 | 33.33 | 4 | 44.44 | 1 | 11.1 | 1 | 11.1 |

| | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | የሚያነሳሳ ይዘት የማካተት ሁኔታቸው | | | | | | | | | | |
| 12 | መ/ሩ(ሯ) አንብቦ የመረዳትና የመፃፍ ክሂልን ለማቀናጀት ከመሞከር አኳያ | - | - | 3 | 33.33 | 5 | 55.55 | 1 | 11.1 | - | - |
| 13 | .መ/ሩ(ሯ) በመማሪያ መፅሀፉ ላይ ካለው በተጨማሪ የቋንቋክሂሎችን ለማቀናጀት የሚጠቀሙባቸው ዘዴዎች አንፃር | - | - | 3 | 33.33 | 4 | 44.44 | 1 | 11.1 | 1 | 11.1 |
| 14 | አጠቃላይ በመማር ማስተማር ሂደቱ የአንብቦ መረዳትና የመፃፍ ክሂል ቅንጅታዊ አቀራረብ በተመለከተ አጭር ማብራሪያ ከመስጠት አኳያ፡፡ | - | - | 5 | 55.55 | 2 | 22.2 | 1 | 11.1 | 1 | 11.1 |

ከላይ ከቀረበው ሠንጠረዥ መረዳት እንደሚቻለው መምህራን የማንበብና የመፃፍ ክሂልን በቅንጅት ለማስተማር ከመማሪያ መጽሐፍ በተጨማሪ ሌላ የማስተማሪያ መሳሪያ መጠቀም እንደ ገጥም ማስነበብ ና ማጻፍ፣ልቦለድ ማስነበብና ማጻፍ የመሳሰሉት ወዘተ... ናቸው፡፡ የመጠቀም ሁኔታዎች ምን ያህል እነደሆነ ለማወቅ በተደረጉት ምለከታዎች አይቻለሁ፡፡ በተራ ቁጥር 10 ላይ የቀረበው ጥያቄ እንደሚያሳየው መ/ሩ(ሯ) የሚሰጧቸውን የቤት ስራዎች የአንብቦ መረዳትና የመፃፍ ክሂልን በማቀናጀት የሚሰሩ ነቸው5(55.5%) ከፍተኛ፣ 2(22.2%) መካከለኛ፣ 1(11.1%)ዝቅተኛና 1(11.1%) በጣም ዝቅተኛ አንደሆነ ለመመለከት ችያለሁ፡፡

በተራ ቁጥር 11 ላይ የቀረበው ጥያቄ እንደሚያሳየው መ/ሩ(ሯ) ከተማሪ መፀሐፍ ውጭየተማሪዎችን የአንብቦ -ረዳትና የመፅሃፍ ፍላጎት የሚያነሳሳ ይዘት የማካተት ሁኔታቸው3(33.33%) ከፍተኛ፣ 4(44.44%) መካከለኛ፣ 1(11.1%)ዝቅተኛና 1(11.1%) በጣም ዝቅተኛ አንደሆነ ለመመለከት ችያለሁ፡፡

በተራ ቁጥር 12 ላይ የቀረበው ጥያቄ እንደሚያሳየው መ/ሩ(ሯ) አንብቦ የመረዳትና የመፃፍ ክሂልን ለማቀናጀት ከመሞከር አኳያ 3(33.33%) ከፍተኛ፣ 5(55.55%) መካከለኛ፣ 1(11.1%)ዝቅተኛ አንደሆነ ለመመለከት ችያለሁ፡፡

በተራ ቁጥር 13 ላይ የቀረበው ጥያቄ እንደሚያሳየው .መ/ሩ(ሯ) በመማሪያ መፅሀፉ ላይ ካለው በተጨማሪ የቋንቋክሂሎችን ለማቀናጀት የሚጠቀሙባቸው ዘዴዎች አንፃር3(33.33%) ከፍተኛ፣ 4(44.44%) መካከለኛ፣ 1(11.1%)ዝቅተኛና 1(11.1%) በጣም ዝቅተኛ አንደሆነ ለመመለከት ችያለሁ፡፡

በተራ ቁጥር 14 ላይ የቀረበው ጥያቄ እንደሚያሳየው አጠቃላይ በመማር ማስተማር ሂደቱ የአንብቦ መረዳትና የመፃፍ ክሂል ቅንጅታዊ አቀራረብ በተመለከተ አጠር ያለ ማብራሪያ ከመስጠት አኳያ 5(55.5%) ከፍተኛ፣ 2(22.2%) መካከለኛ፣ 1(11.1%)ዝቅተኛና 1(11.1%) በጣም ዝቅተኛ አንደሆነ ለመመለከት ችያለሁ፡፡

በአጠቃላይ ከዚህ መረዳት እንደሚቻለው መምህራን በአማርኛ ቋንቋ በሚያስተምሩበት ጊዜ በመጸሐፉ ላይ ያለውን ብቻ ትኩረት በመስጠት ነው፡፡የመማር ማስተማሩን ተግባር እየፈፀምነው ያለው፡፡መጸሐፍ ሲዘጋጅ በተናጥል ስለቀረበ መምህራን በዛዉ ሰኣት ነው የመማር ማስተማሩን የሚሰጡት ነገር ግን መምህራን ሆን ብለውና አቅደው የማንበብና የመፃፍ ክሂልን አቀናጅተው ትምህርት በቃልም የሁለት ክሂሎች ከተፈጥሮዊ አንፃር በማወቅ አቀናጅተው ሲያሰተምሩ አይቻለሁ፡፡ ለምሳሌ የቀረበ ምንባብ ስር ተማሪዎች የቀደመ እውቀት የሚጠይቅ ስለሆን በከፊል መምህራን ሲያስተምሩ አቀናጅተው በማስተማር ተመልክቻለሁ፡፡

ከፍ ሲል የመራጃ ጥንቅሩን በዝርዝር ለማቅረብ እንደተሞከረው ተተኳሪ መምህራን የማንበብና የመፃፍ ክሂልን ለማቀናጀትና ትምህርትን የተሳካ ለማድረግ የሚያደርጉበትን ጥረት ስንመለከት ዝቅተኛ እነደሆነ ነው፡፡በተለይ የማንበብና የመፃፍ ክሂልን በቅንጅት ለማስተማር ከመማሪያ መጽሐፍ በተጨማሪ ሌላ ያማስተማሪያ መሳሪያ የመጠቀም ሁኔታና ሰዎች በመጠየቅ ወይም ዘገባዎችን በማንበብ መረጃ እንዲሰበሰቡናእንዲጽፉ ማደርግ የቤት ስራ በአግባቡ ፅፈዉ መተው ለክፍል ተማሪዎቹ እነዲያነቡ ማድረግ ነው፡፡

### 4.8.1 ከመምህራን ቃለ መጠይቅ የተገኘ ምላሽ

መምህራን የማንበብና የመፃፍ ክሂል ለማቅናጀት የሚያደርጉትን ጥረት ለማወቅ ተጨማሪ መረጃ መሰብሰብ አስፈላጊ በመሆኑ ከመምህራን የቃል መጠይቅ መረጃዎች ልሰበሰብ ችያለሁ፡፡ የተገኘውም ምላሽ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

የማንበብና የመፃፍ ክሂልን በቅንጅት በሚያስተምሩበት ጊዜ በተማሪዎች ላይ የተመለከቷቸው ድክመቶች አሉ? ለሚለው ጥያቄ ሁሉም መምህራን ተማሪዎቹ ላይ በቡድንም ሆነ በተናጥል ለመወያየት ፍላጎት እንደሌላቸው ፣ለትምህረቱ ትኩረት እንደማይሰጡ፣የቤት ስራቸዉን በተገቢዉ እንደማይሰሩ ፣በፍራሃት ማንበብ እንደማይሳተፉ፣አንዳነዶቹ ደግሞ ጭራሹንም ማንበብ እነደማይችሉ፣አንዳንዶቹ ደግሞ አስተካክለው መፃፍ እነደማይችሉ ገልፀዋል፡፡እነዚህን ችግሮች ለመፍታት ምን አይነት መፍትሔ ይጠቀማሉ?ተብለዉ ለተጠየቁት ጥያቄ ሶስቱም መምህራን የማንበብና የመፃፍ ክሂልን ችግር ያለባቸውን ተማሪዎች የድጋፍ ትምህርት በመስጠት ፣እንዲያነቡ በየቀኑ ማበረታታት ፣የፍረሃት ችግር ያለባቸውን ተማሪዎች በሳይኮሎጂስት የምክር አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግ፣እነዲሁም በክፍል ውስጥና ውጪ ከጉደኞቻቸው ጋር እንዲያነቡና እንዲፅፉ ማበረታታት ነው፡፡ተማሪዎቹ እንዴት ማንበብና መፃፍ ክሂልን እንዳለባቸው መመሪያ ይሰጧቸዋል ? የሚል ጥያቄ ቀርቦላቸው ሁሉም መምህራን መመሪያ እንደሚሰጡ ከገለፁ በኋላ ተማሪዎቹ ግን የሚሰጣቸዉን መመሪያ እንደማይተገብሩት ሶስቱም መምህራን ገልጸዋል፡፡

የማንበብና የመፃፍ ክሂልን በቅንጅት በሚያስተምሩበት ጊዜ ትምህርቱን አስቸጋሪ የሚያደርጉ ነገሮች አሉ? ካሉ ምንና ምን ናቸው? ለሚለው ጥያቄ ሁሉም መምህራን ችግሮች እነደሚያጋጥሟቸው ገልጸዋል፡፡ችግሮቹም ሊያብራሩ መማሪያ መፀሀፍ አብዛኛውን ጊዜ የማንበብና የመፃፍ ክሂልን ለማስተማር እንደማይጋበዝ፣በክፍለ ግዜና አስተዳደራዊ ጉዳዮች ጫና እንደሚፈጥሩባቸውና ለትምህረቱ የተመደበለት የግዜ መጠን አናሳ መሆኑን ጠቁመዋል፡ ፡ለነዚህ ችግሮች ምን አይነት አማራጭ መጠቀም ያስፈልጋል ብለው ያስባሉ? ተብሎ ለቀረበላቸው ጥያቄ መማሪያ መጸሐፍ እነደገና ቢሻሻል ፣አስተዳደራዊ ጉዳዮችን መጸሐፍ የግድ ማለቅ እንዳለበት ስለሚገልፅ ከመማሪያ መጸሐፍ በተጨማሪምሌሎች ተግባራትን በተፈለገው አጋጣሚ እንድንጠቀም ስላደረጉን ይህ ነገር ትኩረት ቢሰጠውመ ለትምህርት የተመደበለት ሳምንታዊ ክፈለ ጊዜ ክሂሎችን በተገቢዉ መንገድ ለማስተማር ስለማያስችል ተጨማሪ ክፍለ ጊዜ ቢመደብለት የተሸለ እንደሚሆን ጠቁሟል፡፡

ከላይ ምልከታ የተገኘው ምላሾች እንደሚያስረዱት የማንበብና የመፃፍ ክሂልን የማቀናጀትና ትምህርቱን የተሳካ የማድረግ ሀላፊነታቸውን በአግባቡ እየተወጡ እንዳለሆነ ነው። ምሳሌ በተራ ቁጥር 7 ላይ ተማሪዎች የሚፅፏቸውን ፅሁፎች ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያነቡላቸው የማድረግ ሁኔታ 3(100%) ባጣም ዝቅተኛ ነው ሲሉ ገልጽዋል።

በአጠቃላይ መምህራን የማንበብና የመፃፍ ክሂልን በቅንጅት በሚያስተምሩበት ጊዜ ውስን መምህራን ትምህርቱ የተሳካ እንዲሆን ጥረት የሚያደረጉ ቢሆንም አብዛኛዎቹ መምህራን ግን ሚናቸውን በአግባቡ ዕየተወጡ እንዳለሆነ ለማወቅ ተችሏል ።ነገር ግን በተዛማጅ ቅኝት ፅሁፍ ላይ መምህራን የማንበብና የመፃፍ ክሂልን በቅንጅት ለማስተማርና ትምህርቱን ስኬታማ ለማድረግ ያላቸው ሚና ቀላል እንዳልሆነ ተገልጻል።

### 4.8.2 መምህራን ለማንበብና ለመፃፍ ክሂል ቅንጅታዊ አቀራረብ ያላቸው ግንዛቤ

የቋንቋ ክሂሎችን በቅንጅት ለማስተማር መምህራን የሚኖራቸው ግንዛቤና አመለካከት ለትምህርት ወሳኝነት አለው።ስለዚህ በዚህ ጥናት መምህራን ስለ ማንበብና መፃፍ ክሂል ቅንጅታዊ አቀራረብ ያላቸውን ግንዛቤ መፈተሽ አስፈላጊ በመሆኑ ከመምህራን የቃል መጠይቅ የተገኘው ምላሽ እንደሚከተለው ቀርቧል።የማንበብና የመፃፍ ክሂልን አቀንጅተው ያስተምራሉ? ለሚለው ጥያቄ ሁሉም መምህራን ቅንጅታዊ እንደሚያስተምሩ ገልፀዋል።ለምን? ብሎ ለቀረበላቸው ክሂሎቹ በአብዛኛው ጊዜ የማይነጣጠሉ በመሆናቸው እንደሆነ ገልፀዋል ። አቀናጅተው በማስተማረዎ ደስተኛ ነዎት ለሚለው ሁሉም መምህራን ደስተኛ መሆናቸውን አስረድተዋል።

የማንበብና የመፃፍ ክሂል አቀንጅቶ በማስተማር ምን አይነት ጠቀሜታ ይኖረዋል ብለው ያስባሉ ለሚለው ጥያቄ መ1፣መ2 እና መ3 የማንበብና የመፃፍ ክሂል በበለጠ መልኩ ስለምንገለገልባቸውና ለሌሎቹ ክሂል መዳበር መሰረት ስለሆኑ እነዚህን ከሉሎቹ በቅንጅት በማስተማር የታማሪዎች ተግባቦት ብቃት ማሳደግ ይችላ በማለትያለዉን ጠቀሜታ ገልፀዋል። ትምህርቱን በሚማሩበት ጊዜ ወይም በተለያዩ ስልጠናዎችና ወርክሾፖችስለ ቋንቋ ክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ ምንነትና ጠቀሜታ ተምረዋልለሚለው ጥያቄ ሶስቱም መምህራን በአውንታ መልሰዋል።ነገርግን ሁሉም መምህራን በኮሌጅ ደረጃ በተማሩት እንጂ በስልጠናም ሆነ በወርክሾፖች ላይ ለመክፈል አጋጣሚዎች እንዳልተፈጠረላቸው ተናግረዋል።

የመምህሩ መምሪያ መምህሩ የተማሪዉን የመማሪያ መጸሐፍ እንዴት ሊያስተምር እነደሚችል አቅጣጫ ጥቋሚ መሳሪያ መጽሐፍ ደግሞ ተማሪዎች የተለያዩ መልመጃዎችን እንዲሠሩበት፣ የመማር ማስተማር ሂደቱን እነዲከታተሉበት የሚያስችል የማስተማሪያ መሳሪያ ነው፡፡

የቋንቋ ማስተማሪያ  መጽሐፍት የመማር ማስተማር ሂደትን የሚመሩ የትምህርቱን መነሻና መድረሻ የሚጠቁሙ የተለያዩ ይዘቶችን በምሳሌ አስደግፈው የሚያቀርቡ መልመጃዎችና የተለያዩ ተግባራት በማቅረብ ተማሪዎችን እንዲለማመዱና የመማር ማስተማር ሂደቱን መረጃ የሚሠጡ እነደሆኑ በተዛመጁ ፅሁፍ ቅኝት ላይ ተገልጻል፡፡  የማበብና የመፃፍ ክሂልን በቅንጀት ለማስተማር የመምህሩ መምሪያና የተማሪዉ መጽሐፍ ያላቸው አስተዋፆ ምን እነደሚመስል መፈተሽ አስፈላጊ ነው፡፡

## 4.8.3 ከመምህራን ቃል መጠይቅ የተገኘ ምላሽ

የመምህራን መምሪያ የተማሪዉ መጽሐፍ ተገልጻል፡፡ የማበብና የመፃፍ ክሂልን በቅንጀት ለማስተማር ያለቸው እገዛ ምን እነደሚመስል ለማወቅ ከመምህራን የቃል መጠይቅ የተገኘው ምላሽ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡ለክፍል ደረጃው የቀረበው የተማሪዎች መማሪያ መጸሐፍ ተገልጻል፡፡  የማበብና የመፃፍ ክሂልን አቅንጀቶ ለማቅረብ አመቺ ነው? ተብሎ ለቀረበላቸው ጥያቄ ሶስቱም መምህራን መጽሐፉ ተገልጻል፡፡ የማበብና የመፃፍ ክሂልን በቅንጀት  ለማቅረብ የማይመች  መሆኑን ገልፀዋል፡፡ለምን? ለሚለው ነጥብ መጽሐፍ ለሁሉም ክሂሎች እኩል ትኩረት እንደማይሰጥና መልመጃዎቹ ተማሪዎቹን በተገቢዉ መልኩ ለማለማመድ የሚያስችሉ መሆናቸዉን ጠቁመዋል፡፡

የመምህሩን መምሪያ ይጠቀማሉ? ለሚለው ጥያቄ ሁለቱ መምህራን እንደሚጠቀሙ ገልፀዋል፡፡ ነገር ግን አንዷ መምህርት እነደማትጠቀም ገልፃለች ፡፡ምክንያቱም የመምህሩ መምሪያ በትምህርትቤታቸው ውስጥ ስለሌለ ሁለቱ መምህር ደርሷቸው እሷ ግን ስላደረሳት ነው ሆኖም ለምን በአቅራቢያ ካሉ ትምህርት ቤቶች  በመዋስ ወይም ኮፒ በማድረግ እንደማትጠቀም ለቀረበላት ጥያቄ ምንም አይነት ምላሽ አልሰጠችም ፡፡ የማበብና የመፃፍ ክሂልን ቅንጀታዊ አቀራረብን ለመምራት ምን ያህል ጠቃሚ ነው? ለሚለው ነጥብ መመሪያው ከላይ በተማሪዎች መማሪያ መጽሐፍ  ላይ እንደተገለፀው  ተገልጻል፡፡  የማበብና የመፃፍ ክሂልን ይዘቶችን በስፋት አላካተተም ፡፡ነገር ግን በመጽሐፉ የቀረቡትን የማበብና የመፃፍ ክሂል  ይዘትና ተግባራትን ለመምራት፣ለማቀድና ለመገምገም ምን አይነት ዘዴ ወይም ብለሀት መጠቀም እንዳለብን መነሻ ይሆናል  በማለት ያለዉን ጥቅም አብራርተዋል፡

# ምዕራፍ አምስት

# ማጠቃለያና የመፍትሔ ሀሳብ

## 5.1 ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት አብይ አላማ የማንበብና የመፃፍ ክሂልን አቀናጅቶ በማስተማር ክሂሎችን በማሻሻል ርገድ ያልው ሚና ለማረጋገጥ የተድረገ ጥናት እንድነበር ቀደም ሲል ተገልፃል። የክሂሎቹ ትስስር ና ዝምድና ተመስርቶ በቅንጅት መቅረባቸውን ውጤታማነት ልመፈተሽ በጥናቱ ለመመለስ የተሞከሩ ምሰርታዊ ጥያቄዎች እንደነበሩ ይታወቃል። እነዚህን ጥያቄዎች በአግባቡ መመልስ እንዲቻል በመጅመሪያ ተጠኝዎች እና የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ተመርጠዋል። ለተጠኚዎቹ የእንብቦ የምርዳትና የመፃፍ ችሎታን የሚልካ ቅድመ ትምህርት ፍተና ተሰጥቷችዋል።አጥኚዋ ክሂሎችን አቀናጅቶ ልማስተማር የሚያስችል መመሪያ እቅድ ተዘጋጅቷል።የሙክራ ቡድኑ ተማሪዎች ከመደበኛ ፈርቃችው ውጭ የሚማሩበት መንገድ ተመቻችቷል።ለአንድ ወር / ለአራት ሳምንት እንዲማሩ ተደርጉል። በመጨረሻም የሙከራ ቡድኖቹ አንብቦ የመረዳትና የመፃፍ ችሎታን የሚለካ የጽሑፍ ቅድምና ድህረ ትምህርት ፍተና ተስጥቷል። ውጤቱም በቃለ መጠይቅና በክፍል ውስጥ ምልከታ ከተሰበሰበው መረጃ ጋር እየተገናዝበ ተመዝግቧል።

- ✓ በአጠቃላይ ለጥናቱ የሚያስፍልጉ መረጃዎች በፍተና፣በክፍል ውስጥ ምልከታና ቃለ መጠይቅ ተሰብስቧል።ይፈተና እጤቱ በመቶኛ ተሰልቶ በንፅፅር ተተንትኗል የየዕለት የመማር ሂድት ትግበራውና ከመምህሩ ጋር የነበራቸው ተራክቦ ተጠናክሮ በማደራጃት ተይዟል።የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን። በቅንጅትማስተማር ክሂሎችን ለማሻሻል ያለው ሚና ምን እንደሆነ ለማረጋግጥ ተሞክሯል። ተማሪዎች የቅድመና ድህረ ትምህርት ፍተናዎች በሁለት ባልሙያዎች ታርመዋል። ውጤታቸውም ከታወቅ በሓላ የቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተናዎች አጠቃላይ ውጤት ተሰለቷል። ልዩነቱም በቡድኑ ቅድምና ድህረ ትምህርት አማካይ ውጤት (21.3 )ሆኖ ተመዝግቧል።ሂለቱም ፈተናዎች በተናጥል ታይቷል። በድህረ ትምህርት ፈተና ያስመዝገቡት (66.9 ) ከቅድመ ትምህርት ፈተና ውጤት ( 45.6 ) ጋር ሲነፃፀር የጎላ ልዩነት ያለው መሆኑ ተረጋግጧል።

- ✓ ከክፍል ውስጥ ክንውን ምልከታና ከቃለ መጠይቅ የተገኘው መረጃ እንዳሳየው በትግበራ ውቅት የመውያየት፣ መገምገም፣ የማጠቃለል ፣ ሀሳብ የማመንጨት ና ካነበቡት ተነስተው ሀሳባቸውን በፅሁፍ የመግለፅ ሁኔታዎች ተስተውለዋል። በተጨማሪም ለትምህርቱ እንተተነሳሱና ሀሳብ የማመንጨት ና አስታውሶ የመፃፍ ችሎታቸው እንደዳበረ ለመረዳት ተችሏል። ክሂሎችን በቅንጅት መማራችው በተማሪዎች ዘንድ ተምራጭ መሆኑን የተሰበሰበው መረጃ አርጋግጧል። ይሁን እንጂ እንፃራዊ ለውጥ ቢኖረውም የቆየውንና የተለመደውን የተማሪዎችን የማንበብና የመፃፍ ልምድ ችግር ሙሉ በሙሉ መፍታት እምዳል ተቻለ መረዳት ተችሏል።

- ✓ አንዳንድ ተማሪዎች የቅድመና ድህረ ትምህርት ፍተና ይዝት ተመሳሳይ በመሆኑ ከቅድመ ትምህርት ፈተና ያገኙት ተሞክሮ ስለገባቸው በድህረ ትምህርት ፈተናው መጠነኛ መሻሻል ታይቷል። ይህም ማንበብና መፃፍን ከትስስራቸው አንፃር በቅንጅት ማስተማር ክሂሎችን በማሻሻል ረገድ ጠቀሜታ እንዳለው ፍንጭ ይሰጣል። ማንበብና መፃፍን ክሂሎችን በተዘጋጀው የተማሪው መማሪያ የሙከራ ቡድን ባስመዘገበው (66.9 ) ውጤትና ክሂሎችን በተናጥል ሲማር ከቆየው ካስመዘገበው ( 45.6 )መሰረት ከፍተኛ የሆነ የውጤት ልዩናት አስመዝግበዋል። በመሆኑም ክሂሎችን በቅንጅት ማስተማር ውጤታማ እንደሄነ የዘርፉ ተመራማሪዎች ያቀረቡት ፅንሰ ሀሳብም ትክክል እንደሆነ መረዳት ተችሏል። ከጥናቱ ውጤት በመነሳት ክሂሎችን በቅንጅት የተማሩ ተማሪዎች አንብቦየመረዳትና የመፃፍ ችሎታቸው በከፍተኛ ደረጃ መሻሻል አሳይቷል።ስለዚህ ክሂሎችን በቅንጅት ማስተማር ክሂሎችን በማሻሻል ረገድ ያለው ሚና ከፍትኛ እንደሆነ መደምደም ይቻላል። በአጠቃላይ ከቅድመ ፈተና የድህረ ፈተና ውጤት የተሻለ ውጤት ማስመዝገቡ ለጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄዎች አዎንታዊ መልስ አስገኝቷል ማለት ይቻላል።

## 5.2. የመፍህሔ ሀሳብ

- ✓ የማንበብና የመፃፍ ክሂሎች ከትስስራችው አንፃር በቅንጅት ከቀረቡ ጠቀሜታው የጎላ እንደሆነ ይህ ጥናት አሳይቷል፡፡ ስለሆነም ማንበብና መፃፍ በቅንጅት ማስተማር ትኩረት ተሰጥቶት ተማሪዎች በክፍል ውስጥና ከክፍል ውጭ ልምምድ እንዲያደርጉ ቢበረታታ፡፡

- ✓ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የማንበብና የምፃፍን ክሂሌች በቅንጅት ሲያስተምሩ ተማሪዎቻቸውን በግል፣ በጥንድና በቡድን በመከፋፈል የተለያዩ ተግባራትን እንዲያከናውኑ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ይኸውም ተማሪዎች እንዲያንፀባርቁ በማድረግ፣ ተገቢውን ዝግጅትና ክትትል በማድረግ ፣ የተማሪዎቻችውን ተሳታፊነት በማሳደግ ክሂሎችን የሚያጎለብቱበትን መንገድ ማመቻቸት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ከዚህ አንፃር እየተሰራበት ያለው የመማር ማስተማር መንገድ ቢፈተሸና እንዲታረም ቢደረግ፡፡

- ✓ የማንበብና የመፃፍ ክሂሎች በቅንጅት ከቀረቡ ሁሉም ተማሪዎች ጥሩ ተሳታፊ እንዲሆኑ ፣ ትምህርቱን በትኩረት እንዲከታተሉ ና በተመሳሳይ ጊዜ ከአንድ በላይ ክሂል እንዲለማመዱ ምያደርጋል፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች በልምምድ ትምህርቱን የተሻለ ውጤት ማስመዝገባቸው ጥናቱ አረጋግጣ፡፡ስለዝህ ክሂሎች በቅንጅት ቢሰጥ፡፡

- ✓ የቋንቋ ትምህርት በክፍል ውስጥ ብቻ የሚካሔድ ስላልሆነ ተማሪዎች ከክፍል ውጪ የማበብና የመፃፍ ክሂልን በቅንጅት እንዲያዳብሩና እንዲጠቀሙ የሚያስችሉ የቤት ስራዎችን መምህራን ቢሰጡና ቢከታተሉ፡

# ዋቢ ጽሑፎች

ሞገስ አማረ (1999). "የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን አዋህዶ ማስተማር ክሂሎችን በማጎልበት ረገድ የሚኖረውን ሚና"። ባህርዳር ዩኒቨርሲተ ያልታተመ።

ትዝታ ደሳለኝ(2002). "የቋንቋ ክሂሎችን አቀናጅቶ አማርኛ ቋንቋን የማስተማር አተገባበርና የተማሪዎች አቀባበል ፍተሻ"። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ያልታተመ።

አትክለቲ መኮንን (1998). "የቋንቋ ክሂሎችን አቀናጅቶ አማርኛን የማስተማር ስነ-ዘዴ አተገባበር ፍተሻ" ። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ያልታተመ።

እሸቴ መብራት (2003)."የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን አዋህዶ ማስተማር ክሂሎችን በማጎልበት ረገድ የሚኖረው ሚና ዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ያልታተመ።

ያለውእንዳወቀ (2001).የምርምርመሰረታዊመርሆዎችናአተገባበር። (ሁለተኛዕትም) አዲስአበባ፣ ንግድማተሚያቤት።

Atkin S, J.etal.(1996).Skills development methodology part two Addis Ababa: Addis Ababa Universty press.

Barrs, Myra. (2000).The Reader in the Writer.Reading (United Kingdom Reading Association), July, 54-60.

Block, CathyColling. (1997).Teaching the Language arts.Expanding thinking Student Centered instraction. Bastone: Allyn and Bacon.

Block, Cand Mangieri,J.(1995).Reason to Read Thinking Strategies for life Through Literature, Volumes 1-3 Menlo Park, CA: Addion.

Byrne, D. (1981). Integration Skill in Johnson and Marrow.HongKong: Long man Group Ltd.

Celce-Murcia,M.(eds.)(1991).*Teaching English as a Second or Foreign Language*.(2nd ed.).Boston: Heinl & Heinle publishers.Ltd.

Conley, Mark W. (1997).*Reading and Writing: teaching for the connection*. (2nd ed.)Less har court Brache and company.

Durkin, D. (1997). Teaching themtoread.(5th edition)Boston:Allyn and Block, Cand Mangieri,J.(1995).*Reason to Read Thinking Strategies for life Through Literature,* Volumes 1-3 Menlo Park, CA: Addion.

Gilbert,J.(1982).Clear Speech:Pronunciation and Listening Comprehension in English.TesolQuarterly.Vol 25 No.1(spring,1991) PP.51-75.

Grellet (1991:8) Grellet,F.(1981).*Developing reading skills*.Cambridge:Cambridge unverstiy Press.

Gary, cobine.(1995).Writing as aresponse to reading.(http:// www.vatide.com./pnp/ERIC/ write- read.htm.

Grellet,F.(1981).*Developing reading skills*.Cambridge:Cambridge unverstiy Press.

Harmer,J.(1991).*Teaching the practices ofEnglish Language*.London Long man.

Harp, Bill and Brewry, John.(1996).*Reading and writing Teaching for the connection.*(2nd ed.)S.A: Har court brace and campany

Johnson,P.(1982)."Effects on Reading comprehension of Building Back ground Knowledge." TESOL Quarterly 16:4,503-516.

Lindsay and knight.(2006).*Learning and teaching English:A course for teachers*.Oxford: oxford university press.

Littile wood, W.(1981:83*).Communicative language*

Mc Donough and Shaw (1993).*Materials and Methods in ELT*. Cambridge: Black well publisher Ltd.

May, Frank B.(1990).*Reading as communication*.New york:Macmilan Publishing company.

Nunan D.(1988). *Syllabus Design*. Oxford: Oxford university press.

Oxford, R. (2001:12).Integrated Skills in the ELS/EFL Class room.

Raimes, A. (1983). *Techniques in teaching writing*. Oxford: Oxford University press Inc.

Ruddel,MarthaRapp (1997).Teaching content Reading and Writing. (2nd.ed.).

Rivers, W. (1981:297).*Teaching Foreign Langage Skills*.Chicago: Cicago University Press.

Square(1984):how to teach language In practice learning.

Ur.P.(1996:168).*A course in language Teaching Practice and Theory* .13th Printing Cambridge: Cambridge University.

Widdowson, H. G.(1978).*Teaching Language as Communication*.Oford:oup

Williams,(ed.)(1984).*Reading in the Language Class room .London: Macmillan Publishers Ltd*.

# አባሪዎች

**አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ**

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የድህረ ምረቃ መርሀግብር የሂዩማኒቲስ ፣ ቋንቋዎች ጥናት፣ ጋዜጠኝነትና ኮሚኒኬሽን

ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ ስነ-ፅሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት ለተግባራዊ ስነ- ልሳን የአማርኛ ቋንቋን ለማስተማር ትምህርት ክፍል ማስተማር ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያነት ለቀረበ ጥናት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ፡፡

## አባሪ አንድ በሙከራ ቡድኑ ለተካተቱ የ9ኛ "ለ" ክፍል ተማሪዎች የተዘጋጀ ቅድመ ትምህርት ፈተና፡፡

**መለያ ኮድ --------------- ክፍልና ሴክሽን 9ኛለ**

**አጠቃላይ መመሪያ፡-** የዚህ ፈተና ዋና ዓላማ የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን አቀናጅቶ ማስተማር ክሂሎችን በማጎልበት ረገድ ያለውን ሚና ለማረጋገጥ ሲባል ለማድረግ ሙከራዊ ጥናት መረጃ ማግኘት ነው ፡፡ ቡድኑ ክሂሎቹን በቅንጅት ምንም ሳይማሩ የግንዛቤ ደረጃቸውንና ችሎታቸውን ምን ያህል እንደሆነ ለማወቅ ይህቅድመ ትምህርት ፈተና ተዘጋጅቷል፡፡ ከዚህ አንፃር ይህ ፈተና ሶስት ክፍሎች አሉት፡፡ እያንዳንዱን ክፍል ጥያቄዎች መመሪያውን በጥንቃቄ ካነበቡ በኂላ ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ በፅሁፍ መስጠት ይኖርባቸዋል፡፡ ጥያቄዎችን ለመስራት የተፈቀደው ጊዜ 1፡40 ሰዓት ሲሆን አጠቃላይ 100 ነጥብ ይይዛል፡፡

**ክፍል አንድ ፡-** ቀጥሎ ቅደም ተከተላቸው ተዘበራርቀው የተቀመጡትን ዓረፍተ ነገሮች እንዲያያዙ ሀሳብ በቅደም ተከተል በማስተካከል አንድ ተራኪ ድርሰት የተሟላ አንቀፅ አድርጋችሁ ፃፉ፡፡ ለእያንዳንዱ ዓረፍተ ነገር በተገቢው ቦታ ተስተካክሎ መጻፍ አስር ነጥብ በመስጠት ከመቶ ሀምሳ ድርሻ ይኖረዋል ፡፡

1. በክረምት በእረፍት ትምህርት ቤት ሲዘጋ እንደምጠይቃት አስቀድሜ ለአክስቴ ቃል ገብቼላት ነበር፡፡

2. በዚያው ሰሞን እናቴ አክስቴን ጠይቃ ስትመለስ፣ አክስቴ ብቻዋን እንደምትኖር የነገረችኝትዝ አለኝና ምናልባት የሚሰማኝ ያጣሁት ደህና ባትሆን ይሆናል ብዬ አሳብ ገባኝ፡፡ ምን ማድረግ እንዳለብኝም ማሰላሰል ቀጠልኩ፡፡

3. በልጅነቴ የምወዳትን አክስቴን ለመጠየቅ ወደ ፊቼ ከተማ በሄድኩ ጊዜ ያጋጠመኝ ነገር መቼም አይረሳኝም፡፡

4. ለግማሽ ሰዓት ያህል ከቆየሁ በኃላ፣ ባረጀውና ቁመቱ በጣም ከፍ ባለው የፍልጥ አጥር ላይ ተንጠልጥዬ አክስቴን ለመጣራት ወሰንኩ።

5. የአክስቴን ዐይን ለማየት ብቸኩልም ወደ ቤቷ አጥር ግቢ ከመድረሴ በፊት ጥቅጥቅ ባለው የባህርዛፍ ጫካ ውስጥ ጠቂት መጓዝ ነበረብኝ ።

6. እኔም ከታች አግጥጦ ከሚጠብኝ ጉቶ ላይ አረፍኩ። ከዚያ በኃለማ ሁለት የጎድን አጥንቶቼ ተሰብረው እክስቴ አልጋ ላይ እንደተኛሁ ከመንቃቴ በስተቀር የሆነውን ሁሉ አላስታውስም።

7. ድካሜን ሁሉ እረስቼ ጫካውን በሩጫ በማለፍ እውጪው በር እንደ ደረስኩ በሩን ቶሎ ቶሎ አንኳኳሁ። ነገር ግን፣ ማን ነህ? የሚለኝ አጣሁ።

8. እንደምንም ብዬ በመውጣት አጥሩ ጫፍ እንደደረስኩ የጨበጥኩት የበሰበሰ ፍልጥ ተሰበረ።

9. የሐምሌን ጭጋግና ዝናብ ችዬ በልጅ እግሬ እየገሰገስኩ ከምኖርበት የገጠር መንደር ከአዲስ አበባ ግምሽ ቀን ተጉዤ ስድት ሰዓት ገደማ ፍቼ ከተማ ደረስኩ።

10. እንደገናም በሩን ደጋግሜ ደበደብኩት ምንም መልስ የለም ።

**ክፍል ሁለት፡-ቀጥሎ** የቀረበውን ምንባብ ከመጀመራችሁ በፊት ለመልሳችሁ ምክንያት በመስጠት አብራርታችሁ ፃፉ። (ቅድመ ምንባብ ጥያቄዎች ) ።ከመቶ ሀያ ድርሻ አለው

1. ከግጥምና ዝርው (ስድ-ፅሁፍ) አንባቢን ወይም አድማጭን ይበልጥ የሚስበው የትኛው ነው?ለምን አብራርታችሁ ፃፍ?

2. በግጥምና በዝርው ፅሁፍ መካከል ያለውን ልዩነት አብራርታችሁ ግለፁ።

3. ግጥም ሙዚቃዊ ቃና ወይም ዜማ አለው ሲባል ምን ማለት ነው?አብራርታችሁ ፃፉ።

እንደቤትህ እደር አትይ ጎረቤት
የሚለውን እርሳው አይደለም እውነት
ቢሆንልህ ሞክር አንተ ልትሻል
ተሰጥቶሃልና የነፃነት ኃይል።
ጎረቤትህ በልቶ ጠግቦ ሲደነፋ
አንተ ጦም አትደር እንደሌለው ተስፋ
ደግሞም ዝም አትበል ድንበርህ ሲገፋ።
ጎረቤት ሃገሮች የሰሩትን ሁሉ
አሻሽለህ ስራው እፁብድንቅ ይበሉ።
አንተሁን ምሳሌ ለጎረቤትህ
ቁመህ አትመልከት እሱ ሲቀድምህ።

ታጠቅ ተነስ እንጂ አትፍራ ሞትን

ሀውልትህ ለህዝቡ ይሰጣል ብርሃን፡፡

ሀገሩን ሊያሳድግ ቢሰራ ሰው ሁሉ

ታሪኩ ይፃፋል ይተረካል ገድሉ፡፡

(ኢሰያስ አለሜ መፅሐፈ ምክር ገጽ 54-55) ተሻሽሎ የቀረበ

ቀጥሎ የቀረቡ ጥያቄዎቸ ቀደም ሲል ባነበባችሁት ምንባብ ላይተመስርተው የወጡ ናቸው፡፡ ስለዚህ ጥያቄዎችን ስትመልሱ ፡-

ሀ. ከፅሁፉ በቀጥታ የሰፈረን ሀሳብ መሰረት በማድረግ

ለ. ከቅድመ ልምድና ዕውቀት በመነሳት የሚመለሱ ናቸው፡፡ (ድህረ ንባብ ጥያቄዎች) አስራስምንት ነጥብ አለው፡፡

1. ሀገሩን ሊያሳድግ ቢሰራ ሰው ሁሉ

ታሪኩ ይፃፋል ይተረካል ገድሉ፡፡ ሲል ምን ማለቱ ነው? አብራሩ፡፡-----------------------------------

-------------------------------------------------------------------------

2. የፅሁፉን አብይ ጭብጥ በራሳችሁ አገላለፅ በአጭሩ ፃፉ፡፡

--------------------------------------------------

-------------------------------------------------

3. አንድ እጅግ በጣም የምትወዱትን መምህር አስቡና እንዲኖረው የምትፈልጉትን ተፈላጊ( ጥሩ ባህሪያት) በቃላት ብቻ በመዘርዘር በተፈላጊነት ቅደም ተከተላቸው መሰረት ዘርዝራችሁ ፃፉ፡፡-----------------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------

**ክፍል ሦስት** ፡- ቀጥሎ የተዘረዘሩትን አያያዝና የመሸጋገሪያ ቃላት ካነበባችሁ በኃላ በሚከተሉት አረፍተ ነገሮች ውስጥ ያሉትን ክፍት ቦታዎች ከቀረቡት አማራጮች መካከል አያያዥና የመሸጋገሪያ ቃላት የሆኑትን በመለየት በፅሁፍ አሟሉ፡፡ከመቶ አስራሁለት ድርሻ ይሆረዋል፡፡

- በተደጋጋሚ በመቀጠል
  ዳግመኛ
- በማስከተል ከዚህ ቀጥሎ
  እስከዚ ድረስ
- በሌላ ጊዜ ከዚህ በኃላ
  ታዲያ

➢ ከዚህ

➢ በማያያዝ

ወደፊት

➢ ደግሞ

በዚህ አኳኋን

1. ተጋባዡ ተናጋሪ፣ መፃህፍት የንማንበብ ልምድን በሚመለከት ገለፃ አደረጉ፤ ---------------------- ስለሚያነቧቸው መጻሕፍት በራስ አባባል ማስታወሻ መፃፍ ጠቃሚ እንደሆነ ተናገሩ፡፡

2. የጤና ባለሞያ የኤች አይ ቪ ኤድስን የመተላላፊያ መንገዶች በሚመለከት ዋነኛ የሆኑትን በዝርዝር አቀረቡ ፤----------------በዚሁ ጉዳይ ላይ ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚያስፈልጋቸውን ነጥቦች ለይተው ገለፃ በመስጠት ንግግራቸውን ደመደሙ፡፡

3. ተውኔትን በሚመለከት ግጥሞችን አስፋፍቶ ተውኔቶችን እንዴት ማዘጋጀት እንደሚቻል ተምረናል፡፡--------------አያያዥ ቃላት ወይም ሐረጋትን እንማራለን፡፡

4.እስከአሁን ያለው የንባብ ልምዳችን ብዙ የሚያኮራ ላይሆን ይችላል፤-----------------ግን አስፈላጊነቱን ስለተረዳን ጠንክረን ልናሻሽለው እንችላለን፡፡

5. ሁሉም ኢትዮጵያዊ የየድርሻውን በተሰማራበት ተግባር ለአገሩ እድገት ማበርከት አለበት ፤ ------------------የተሰሩ ስራዎች በቂ ላይሆኑ ይችላሉ፡፡

6. እንደሌሎቹ ክበቦች ሁሉ በትምህርት ቤታችን የተውኔት ክበብ በሚገባ ተደራጅቷል፡፡ --------------------ክበቡ በየሦስት ወራት የተለያዩ ተውኔቶችን ለተማሪዎች ያሳያል፡፡

## አባሪ ሁለት በሙከራ ቡድን ለተካተቱ የ9ኛ ክፍል ተመሪዎች የቀረበ ቅድመ ትምህርት ቃለ መጠይቅ

## ቀን 15/08/ 2015 ዓ.ም

ቦታ ትምህርት ቤት ውስጥ

ለተጠያቂ ተምሪዎች፡-የዚህ መጠይቅ ዋና አላማ ማንበብና መፃፍ ክሂሎችን አቀናጅቶ ማስተማር ክሂሎችን በማስተማር ረገድ ያለውን ሚና ለማረጋገጥ ለሚደረግ ጥናት መረጃ ለማሰባሰብ ነው፡፡

ከቃለመጠይቁ የተገኘውን መረጃ ከታቀደው አላማ ውጭ ለሌላ ተግባር አይውልም። ስለዚህ ቀጥሎ ለማቀርባቸው ጥያቄዎች እውነተኛና ትክክለኛ መልስ እንድትሰጡኝ በትህትና እጠይቃለሁ።

1. 9ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ ስትማር /ስትማሪበቅንጅት እንድታነብና እንድትፅፍ የሚያደርግ መልመጃ አጋጥመውህ/ሽ የውቃልውይ?

2.ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ለመማሪያነት በተዘጋጀው መጽሀፍውስጥ ማንበብና የመፃፍንበቅንጅት እንድትለማማዱ የሚያደርጉ ሁኔታዎች አሉ?

3. የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን በቅንጅት ትምህርቱ ከ9ኛ ክፍል ጀምሮ ቢሰጥ ምን አይነትምቹሁኔታ ሊፈጥር ይችላል ትላለህ/ያለሽ?

4. የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን በቅንጅት ብትማሩ ጥቅም ወይስ ጉዳቱ የሚያመዝን ይመስልሃል/ሻል?

## አባሪ ሶስት የመምህራን ቃለ መጠይቅ

**አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ**

**የሂዩማኒስቲስ ፣የቋንቋዎች ጥናት የጆርናሊዝምና ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ**

የአማርኛ ቋንቋ ስነ ጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

በ2015 ዓ.ም ለሁተኛ ወሰነ ትምህርት በተመረጠው የገደባኖ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የዘጠነኛ ክፍል በአማርኛ ቋንቋ መምህራን የሚሞላ ቃል መጠይቅ

ውድ መምህር/ ርት

የዚህ መጠይቅ ዋና አላማ በገደባኖ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በአሁን ሰዓት ስራ ላይ በዋለው የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ የቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ የአንብቦ መረዳትና የመፃፍ ክሂል ቅንጅታዊ አቀራረብ ምን እንደሚመስል ከመምህራን መረጃ መሰብሰብ ነው ። ጥናቱ ግቡን ይመታ ዘንድ በመጠይቁ የተካተቱትን ጥያቄዎች በጥሞና በማዳመጥ ተገቢ የሆኑ አስተያየትዎን ለመስጠት ይተባበሩኝ ዘንድ በትህትና እጠይቃለሁ ።ውድ ጊዜዎን መስዋት በማድረግ ለለሚያደርጉልኝ ቀና ትብብር በቅድሚያ ማስጋናዬን አቀርባለሁ ።

**ክፍል አንድ አጠቃላይ የመምህራን መረጃ**

ጾታ-------------------------------------

ዕድሜ-------------------------------------

የትምህርት ደረጃ ----------------------------

የተመረቁበትየትምህርት አይነት-------------------------

በዋናነት-----------------------------------

በንዑስ ------------------------------

አሁን ያሉበት የትምህርት ደረጃ

ዲፕሎማ --------------------------

በመጀመሪያ ድግሪ -------------------------------

በሁለተኛ ድግሪ ---------------------------------

የአገልግሎት ዘመን-----------------------------------

በዲፕሎማ ---------------------

በድግሪ---------------------

ሌላ ካለ ይገለፅ----------------------

ክፍል ሁለት፡- የማንበብና የመፃፍ ክሂል ቅንጅታዊ አተገባበር የተመለከቱ ጥያቄዎች

1. የማንበብና የመፃፍ ክሂልን አቀናጅተው ያስተምራሉ ለምን ?

2. የማንበብና የመፃፍ ክሂልን አቀናጅተው ለማስተማር ደስተኛ ነዎት? ለምን ?

3. የማንበብና የመፃፍ ክሂልን በማቀናጀት በሚያስተምሩበት ጊዜ በተማሪዎች ላይ የተመለከቷቸው ድክመቶች አሉ? ድክመቶቹንስ ለማሻሻል ምን አይነት መፍትሄ ይጠቀማሉ ?

4. በመማሪያ መፃህፍ ውስጥ ያሉትን የማንበብና የመፃፍ ክሂል የሚያቀርቧቸው እንዴትነው? ለምን ?

5. የተማሪው መማሪያ መፃሀፍ፣ የመምህሩ መምሪያ እና መርሃ ትምህርቱ አንብቦ የመረዳትና የመፃፍ ክሂሎችን እርስ በእርስ ተያይዘው እንዲቀርቡ በማድረግ የመማር ማስተማር ዘዴን ለመምራት ምን ያህልአጋዥ ናቸው?

6. አንብቦ መረዳትና የመፃፍ ክሂል ተቀናጅተው ቢቀርቡ ተማሪዎች የቋንቋ ችሎታ ላያ ለውጥ ይመጣል ብለው የስባሉ? የእርሶስ የአቀራረብ ስልት ምን ይመስላል ?

7. የመምህሩን መምሪያ ይጠቀማሉ? የማንበብና የመፃፍ ክሂልን ቅንጅታዊ ትምህርት እንዴት ያቀርበዋል?

ጊዜዎትን ሰጥተው ቃለ መጠይቁን በመመለስ ላደረጉልኝ ትብብር ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

## አባሪ አራት የምልከታ ቅጽ

በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜያት አንብቦ መረዳትና የመፃፍ ክሂል ትምህርት ቅንጃታዊ አቀራረብ ምልከታ ማከናወኛቅጽ (Check List)

አጠቃላይ መረጃ

የምልከታው ቁጥር---------------------

ቀን-------------------ወር--------------ዓ/ም-------------

የትምህርት ቤቱ ስም --------------------------------

ትምህርቱ የተጀመረበት ጊዜ-------------------------

ትምህርቱ  የተጠናቀቀበት ጊዜ------------------------------

ሴክሽን ---------------------------------

ክፊለ ጊዜ -----------------------------

የተማሪው ብዛት---------------------------

የዕለቱ ትምህርት ርዕስ ----------------------------------------------

የዕለቱ ትምህርት አላማዎች፡---------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-------------------------------------------------------

መመሪያ አንድ ፡- ቀጥሎ ከቀረቡት መስፈርቶች መካከል አንዱን በመምረጥ በተሰጠው መልስ መስጫ ቦታ ላይ ትክክለኛውን መልስ (X) ምልክት በማድረግ ማሳየት፡፡

የፍረጃ ደረጃዎች ፡-

በጣም ከፍተኛ 5

ከፍተኛ 4

መካከለኛ 3

ዝቅተኛ 2

በጣም ዝቅተኛ 1

| ተ.ቀ | የመከታተያ ነጥብ | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የክፍለ ጊዜው ይዘት አንብቦ የመረዳትና የመፃፍ ክሂልን ለማቀናጀት ያለው እገዛ | | | | | |
| 2 | አንብቦ የመረዳትና የመፃፍ ክሂልን በቅንጅት ለማስተማር የሚቀርበው ይዘት ከተማሪዎች ህይወት ጋራ ያለው ቁርኝት | | | | | |
| 3 | መ/ሩ(ሯ) ተማሪዎች በትምህርት ጊዜ ምንባብ እዲያነቡ የማድረግ | | | | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ሁኔታ | | | | | |
| 4 | አንብቦ መረዳትና የመፃፍ ክሂልን በቅንጅት ለማስተማር የሚረዱ ብልሃቶች ለምሳሌ ፡-ጥያቄ መጠየቅ ፤ መተንበይ፤ መገመት ፤ ማብራራት ፤መተርጎምና ማጠቃልል | | | | | |
| 5 | መ/ሩ(ሯ)አንብቦ መረዳትን ከመፃፍ ክሂል ጋር ትኩረት በመስጠት የማቀናጀት ሁኔታ | | | | | |
| 6 | መ/ሩ(ሯ) ተማሪዎች አንድን ምንባብ ካነበቡ በኃላ በራሳቸው አባባል እንዲፅፉ የማድረግ ሁኔታዎች | | | | | |
| 7 | መ/ሩ(ሯ) ተማሪዎች የሚፅፉቸውን ፅሁፎች ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያነቡላቸው የማድረግ ሁኔታ | | | | | |
| 8 | መ/ሩ(ሯ) ተማሪዎች ሃሳባቸውን በፅሁፍ እንዲገልፁ በቂ ጊዜ የመስጠት ሁኔታ | | | | | |
| 9 | የሚሰጡ የክፍል ስራዎች አምብቦ መረዳትና የመፃፍ ክሂልን ለማቀናጀትና ለማዳበር ያላቸው ብቃት | | | | | |
| 10 | መ/ሩ(ሯ) የሚሰጧቸውን የቤት ስራዎች የአንብቦ መረዳትና የመፃፍ ክሂልን በማቀናጀት የሚሰሩ ናቸው | | | | | |
| 11 | መ/ሩ(ሯ) ከተማሪ መፀሐፍ ውጭ የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳትና የመፃፍ ፍላጎት የሚያነሳሳ ይዘት የማካተት ሁኔታቸው | | | | | |

13. መ/ሩ (ሯ) አንብቦ የመረዳትና የመፃፍ ክሂልን ለማቀናጀት ይሞክራሉ ከሞከሩ በምን በምን ስልት?

14.መ/ሩ (ሯ) በመማሪያ መፅሀፉ ላይ ካለው በተጨማሪ የቋንቋ ክሂሎችን ለማቀናጀትየሚጠቀሙባቸው ዘዴዎች ምንድ ናቸው?

15 አጠቃላይ በመማር ማስተማር ሂደቱ የአንብቦ መረዳትና የመፃፍ ክሂል ቅንጅታዊ አቀራረብ በተመለከተ አጠር ያለ ግላዊ አስተያየት ካለዎት ይስጡ ፡፡

## አባሪ አምስት በሙከራ ቡድኑ ለተካተቱ ተማሪዎች የተዘጋጀድህረ ትምህርት ፈተና

**መለያ ኮድ------------ክፍልና ሴክሽን ---------------**

አጠቃላይመመሪያ የዚህ ፈተና ዋና አላማ የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን አቀናጅቶ ማስተማር ክሂሎችን በማጎልበት ረገድ ያለውን ሚና ለማረጋገጥ ታስቦ ለተደረገው ጥናት መረጃ ማግኘት ነው፡፡የተመረጠው አንድ የ9ኛ ‹‹ለ››ክፍል በተለያየ መንገድ ለአንድ ወር የተማሩት ትምህርት ምን ያህል የባህሪይ ለውጥ እንዳመጣና ልዩነታቸው በምን ደረጃ ላይ እንዳለ ለመገምገም እንዲያመች የድህረ ትምህርት ፈተና ተዘጋጅቷል፡፡ ይህ ፈተና ሦስት ክፍሎች አሉት፡፡ የእያንዳንዱን ክፍል መመሪያ በጥንቃቄ ካነበቡ በኃላ ለሚቀርቡት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ይሰጣሉ፡፡ ጥያቄዎችን ለመስራት የተፈቀደው ጊዜ 1:40 ሲሆን አጠቃላይ 100 ነጥብ ይኖረዋል፡፡

***መመሪያ አንድ፡-*** የተጀመረውን ሀሳብ ለመጨረስ በርካታ መንገዶችን ተጠቅማቹ የሚከተሉትን ጅምር ዓረፍተ ነገሮችን አስፈላጊ ቃላትና ሐረጋትን በመጠቀም በራሳችሁ አባባል ጨርሱ፡፡ ከመቶ ሃምሳ ድርሻ ይኖረዋል፡፡

1. ------------------------- ልብስ ሰውነትን ከብርድ አይከላከልም ፡፡
2. ------------------------- ባህል ለእድነታችን የማይረዳ ከሆነ መወገድ አለበት፡፡
3.--------------------------- ጫማ እግርን ከእንቅፋት ይከላከላል፡፡
4.---------------------------- ትውልድ የስራ ፍቅር ሊያድርበት ይገባል፡፡
5.---------------------------- ዕለት በዕለት ካልተከታተሉት ፈተናውን ማለፍ አስቸጋሪ ሳይሆን አይቀርም ፡፡
6. መስከረም ሲጠባ ----------------------------
7. ሰሞኑን የገዛነው ዶሮ -----------------------------
8. ጉዞው ከተጀመረ ጀምሮ ወደ ኃላ የማይቀረው --------------------
9. አበበና መሀመድ ቤት እንደገዙ -------------------------
10.ጉበዝ ተማሪ ለመሆን --------------------------

***መመሪያ ሁለት፡-*** ቀጥሎ የቀረቡትን ሦስት ጥያቄዎች ምንባቡን ማንበብ ከመጀመራችሁ በፊት ለመልሳችሁ ምክኒያት በመስጠት አብራርታችሁ ፃፉ ፡፡ ( ቅድመ ምንባብ ጥያቄዎች ) ከመቶ አስራምስት ነጥብ ይኖረዋል፡፡

1. ሰዎች ያልጠበቋቸው ችግሮች በሚያጋጥሟቸው ጊዜ ምን አይነት ስሜት ይፈጠሪባቸዋል ብላችሁ ትገምታላችሁ? ለምን ?-----------------------------------------------------------------------

---------------------------------------------------------

2. የምንባቡን ርዕስ ብቻ በማንበብ ስለ ምን የሚገልፅ ይመስላችሁኋል? ምክኒያታችሁን በመግለፅ መልሳችሁን አብራርታችሁ ፃፍ ።-----------------------------------------------------------

---------------------------------------------------------------

3. ስለ ምክር ምንነት የምታውቋቸውን ነገርችበቅደም ተከተል ዘርዝሯቸው ።

## ጠቃሚ ምክር

ከእለታት አንድ ቀን እንድ አዳኝ በወጥመድ አንዲት ዋኔ ይዞ ወደ ቤቱ ሲመለስ "ወዴት ነው የምትወስደኝ? " ብላ ዋኔዋ ጠየቀቸው ። አዳኙም "ምን ትጠይቂኛለሽ? " አርጄ ልበላሽ ነዋ" ብሎ መለሰላት "እንዴት ያለኸው ሞኝ ነህ አሁን እኔን በልተህ ልትጠግብ ነው ወይ ልትወፍር? እስቲ አስተውለህ ተመልከተኝ ሰውነቴ በጣም ያነሰ ፍጥረት ነኝ። ከጉሮሮህ እንኳ አልወርድም። ይልቅዬ እንስማማ እኔ የሚጠቅሙህ ሶስት ምክሮች ልስጥህ። አንተ ደግሞ ማረኝ። በዚህ ከተስማማን አንዱን አሁን፣ ሁለተኛውን ስትለቀኝ ከዛፍ ላይ ሆኜ ሶስተኛውን ደግሞ እዚያ ማዶ ካለው ዳገት አፋፍ ላይ ተቀምጬ እነግርሀለው። አለችው።አዳኙም "የመጀመሪያ ምክርሽ ከጠቀመኝ እለቅሻለው።" አላት እሷም "ባመለጠህ ነገር አትፀፀት" ፤ እንዲሁም አትቆጭ የመጀመሪያው ምክሬ ይሄ ነው።" አለችው። ሰው "የልቡን ሲነግሩት የኮረኮሩትን ያህል ይስቃል" እንደሚባለው፣ ሰውዬውም ከዚህ ምክር ጋር በልቡ ውስጥ የሚጉላላ አንድ ነገር ተቀሰቀሰበትና "እውነት ተናግረሻል ምሬሻለው ሂጂ" ብሎ ለቀቃት።እሷም በረረችና ከዛፍ ላይ አርፋ፣አንተ ቂል አንተ ሞኝ አንተ ተላላ በዛሬው ስህተት እድሜህን ሙሉ ትፀፀታለህ። አውነት ነው ብትበላኝ ትንሽ ነኝ አልጠቅምህም።ነገር ግን ሆዴ ውስጥ ሃያ ወቄት የሚመዝን ዋጋው በጣም ውድ የሆነ አልማዝ አለ። ብታርደኝ ኖሮ እሱን ልታገኝ ነበር።አሁን ግን ከመሄዴ በፊት ሁለተኛውን ምክር ልንገርህ። የማይሆነውን ነገር ይሆናል ብለህ በሞኝነት አትመን። እንግዲህ ደህና ሁን ከነህብቴ ልሂድ ብላው በረረችና ካፋፉ ላይ አረፈች። ሰውዬውም ይህንን ሲሰማ፣ "ወይ እኔ እንዴት ጉድ ሰራችኝ" ብሉ እየተናደደከንፈሩን እየነከሰ፣ እያጨበጨበ፣እየጦፈ፣ተከተላት። ካፋፉ አጠገብ ደረሰና ቁና ቁና እየተነፈሰ "ምህረት ባደረኩልሽ እንዲህ የሚያናድድ ነገር ትነግሪኛለሽ" የውለታዬ ዋጋ ይህ ነው?" ብሎ እየወቀሳት ድንጋይ ወርውሮ ሊገድላት አሰበ። ሆኖም ምንም ለማድረግ እንደማይችል ሲረዳ "የአልማዙ ነገር ይቅር፡

፡ ይልቅስ ሶስተኛውን ምክር ንገሪኝና ወደቤቴ ልሂድ፡፡" አላት፡፡ ሁለቱ ምክሮቼን ሳትሰራባቸው ሌላ ብጨምርልህ ምን ያደርግል? ‹በመጀመሪያ ባለፈ ነገር እንዳትፀፀትና ያመለጠህ ነገር እንዳይቆጭህ ነገርኩህ›ቀጥዬም የማይሆነውን ነገር ይሆናል ብለህ በሞኝነት አትመን አልኩህ፡፡ ነገር ግን ተግባራዊ አላደረካቸውም፡፡ ‹በሆዴ አልማዝ አለ› ስልህ ከለቀቀከኝ በኂላ ዳግመኛ ልትይዘኝ ባለመቻልህ ተፀፀትክ፡፡ ለምንስ ትቆጫለህ? ድግሞም እኔ (ስጋዬ፣ አጥንቴና ላባዬ ጭምር) ብመዘን ሀያ ወቄት ልሆን አልችልም፡፡እንደምን ሀያ ወቄት የሚመዝን አልማዝ በሆዴ ውስጥ የምሸከም ይመስልሀል? ‹የማይሆን ነገር ይሆናል ብለህ በሞኝነት አትመን› ብዬ ነግሬህ ነበርኮ የያዝከውን ሳትሰራበት ሌላ ጭምሩልኝ አትበል ሶስተኛው ምክሬ ይህ ነው፡፡ሶስተኛውን ልጨምርልህ አይገባኝም ነበር፡፡ ግን ካንተ ይቅር እንጂ ከኔ ሊጎድል አይገባም፡፡እንግዲህ ደህና ሰንብት ብላው በረረች

ቀጥሎ የቀረቡት ጥያቄዎች ቀደም ሲል ያነበባችሁትን ምንባብ ተመስርተው የውጡ ናቸው፡፡ ስለዚህ ጥያቄዎችን ስትመልሱ ፡-

ሀ. ከፅሁፉ በቀጥታ የሰፈረን ሀሳብ መሰረት በማድረግ

ለ. ከቀደመ ልምድና እውቀት በመነሳት የሚመለሱ ናቸው፡፡( ድህረ ምንባብ ጥያቄዎች ) ከመቶ ሃያ ድርሻ ይኖረዋል፡፡

1. በዋኔዋ አገላለፅ አዳኙ ምን አይነት ሰው ነው በዝርዝር አቅርቡ ፡፡-------------------------------
----------------------------------------------------------

2. አዳኙ ዋኔዋን ሊለቃት የቻለው በምን ምክንያት ነበር? -------------------------------------------
--------------------------------------------------------------------------

3. አዳኙ እየተመከረ ስንት ስህተት ፈፀመ ለመን ይመስላችኃል? ------------------------------------
-----------------------------------------------------------------------------------------------

4. ዋኔዋ ለአዳኙ በህይወት ዘመኑ ሁሉ የሚፀፅተው ነገር መኖሩን የነገረቸው የት ሆና ነው? -
------------------------------------------------------------------------------

5. የፅሁፉን አብይ መልዕክት በራሳችሁ አገላለፅ በአጭሩ አብራርታችሁ ፃፉ? -------------------
-----------------------------------------------------------------------------------------

***መመሪያ ሦስት*** ፡- የሚከተለውን ምንባብ በሚገባ ካነበባችሁ እና በውስጡ የተካተቱትን ፈሊጣዊ አነጋገሮች ለይታችሁ ካወጣችሁ በኃላ ፍቻችውን በፅሁፍ አስፍሩ፡፡ከመቶ አስራምስት ድርሻ ይኖረዋል፡፡

**አያ ጥበቡ**

አቶ ጥበቡ የሚባሉ አንድ አዛውንት ነበሩ፡፡ ከዕለታት አንድ ቀን ወደ እርሻቸው ደፋ ቀና እያሉ ሲሄዱ አንዲተራ መልከ መልካም ሴት ከመንገድ ዳር ቁጭ ብላ ስታለቅስ ያገኛሉ፡፡ "አንቺን የመሰለ ቆንጆ ይስቃል፣ይጫወታል እንጂ፣እንዴት ሆደ ባሻ ይመስል ዝምብሎ መንገድ መንገድ ላይ ያለቅሳል? ሲሉ ይጠይቋታል፡፡እሷም "አባቴ የማለቅሰው ዝም ብዬ ሳይሆን፣ ‹እግረ ቀጭን እንደሳሳ፣ ልበሙሉ እንደ አንበሳ እያለ፣ ጧት ማታ ራሱን የሚያሞካሽ እኔን ሲሻው ‹አቅመ ቢስ› ሲሻው ‹ቀልበቢስ› እያለ የሚያናንቅና ተስፋ የሚያስቆርጥ ባል አጋጥሞኝ ሆድ ቢብሰኝ ነው" ትላቸዋለች እሳቸውም "ወቼው ጉድ እግሩ ቢቀጥን፣ልቡ ቢደነድን፣ከሰሳና ከአንበሳ የተወለደ መሰለው?" ከሴት ማህፀን አይደለም የወጣው? ወይ አለማወቅ ደፋር ተይው እያደር ልብ ሲገዛ ይተወዋል፡፡እስከዚያው ትንሽ ሆደ ሰፊ መሆን ጥሩ ነው ልጄ" ፡፡ እስዋም እንባዋን ጥርግ ጥርግ አድርጋ ቀስ እያለች ወደቤቷ ታዘግም ጀመር፡፡ (ባየ ይማም፤ አጭርና ቀላል የአማርኛ ሰዋሰው ፣(2002 )

1.-----------------------------------

2. --------------------------------- 3.---------------------------------------

## አባሪ ስድስት ለሙከራ ቡድኑ የቀረበ የድህረ ትምህርት ቃለ መጠይቅ

*ቀን------------------------*

*ቦታ ትምህርት ቤት*

*አጠቃላይ መረጃ ፡- የዚህ መጠይቅ ዋና አላማ የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን አቀናጅቶ ማስተማር ያለውን ሚና ለመፈተሽ የሚረዳ መረጃ መሰብሰብ ነው፡፡ የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች ለአንድ ውር ማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን አቀናጅቶ ትምህርቱን ከተማሩ በኃላ የመጣውን ለውጥ ለማየትና ለማወቅ ሲባል ይህ ቃለ መጠይቅ ተከናውኗል ፡፡ስለዚህ ከዚህ በታች ለማቀርብቸው አራት ጥያቄዎቸ ተክክለኛ መልስ እንድትሰጭኝ/ጠኝ በትህትና እጠይቃለሁ፡፡*

1. ለአንድ ወር የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን በቅንጅት የተማርክበት መንገድ እንዴት ተመለከትከው/ሽው ?

2. የዚህ ወር ትምህርት አቀራረብ ከዚህ በፊት ከተማርከው የትምህርት አቀራረብ ጋር ሲነፃፀር ልዩነቱ ምንድ ነው?የትኛው ይሻላል ?

3.በቅንጅት የሚሰጠው ትምህርት እንዲቀጥል ምን ምን መደርግ አለበት?

4. አሁን በተማርክበት መንገድ በሁሉም የክፍል ደረጃ ትምህርቱ በቅንጅት ቢሰጥ ምን ለውጥ ሊመጣ ይችላል ብላህ/ሽ ትገምታለህ/ሽ?

## አባሪ ሰባት ለሙከራ ቡድኑ አባላት ማስተማሪያነት የተዘጋጀ ዕቅድ

ይህ አላማ በተፈለገው ጊዜና ሁኔታ ግቡን ይመታ ዘንድ የትግበራው ሂደት ጥራቱንና ጊዜውን በጠበቀ አኳኃን እንዲጓዝ ለማድረግ ዕቅድ አስፈላጊ ነው፡፡ በመሆኑም ቀጥለው የቀረቡትን እቅዶች የሙከራ ቡድኑን የየዕለት ተግባራት በተገቢው መንገድና ጊዜ ለማከናወን የሚያስችል ዕለታዊ ዝርዝር ዕቅድ በአጥኝዋ ተዘጋጅቷል፡፡የዕቅዱ ዋና አላማ የማንበብና የመፃፍ ኪሂሎችን አቀናጅቶ ማስተማር ያለውን ሚና ለመፈተሸሰ ታስቦ ለተደረገው ጥናት መረጃ ማስገኘት ነው፡፡

የትምህርት አይነት አማርኛ

-----ሚያዚያ ----2015 ዓ.ም

ክፍል 9ኛ ‹‹ለ››

አንደኛ ሳምንት ----ክፍለ ጊዜ

የክፍለ ጊዜ ርዝመኔ 1፡30

የትምህርቱ ርዕስ፡- ማንበብ፣ መገመት፣ማብራራት፣ማሰብና መፃፍ

የትምህርቱ አላማ፡- ከዚህ ትምህርት በኃላ ተማሪዎች፡-

◦ በአከባቢያቸው ስለ ሚከናወነው ባህላዊ የጋብቻ ስረዓት ሂደት በዝርዝር ይፅፋሉ፡፡

◦ ምንባቡን አንብበው ባህላዊ የጋብቻ ስረዓት ከዘመናዊው የጋብቻ ስረዓት ጋር በማነፃፀር አብራርተው ይፅፋሉ፡፡

◦ካነበቡት ተነስተው የባህላዊ የጋብቻ ስረአት ጠንካራና ደካማ ጎን ዘርዝረው ይፅፋሉ ፡፡

ዝርዝር ተግባራት

1.የታደላቸውን ቅንጫቢ ፅሁፍ ሁሉም ተማሪዎች በግላቸው ያነባሉ፡፡

2.በአከባቢያቸው የሚከናወነውን ስለ ባህላዊ የጋብቻ ስረዓት የሚያውቁትን ጥንድ በመሆን ተወያይተው በግልይፅፋሉ፡፡ በመቀጠል አራት ቡድን ያለው ቡድን መስርተው የፃፉትን መልሰው ያነባሉ፣ እንደገና አሻሽለው ይፅፋሉ፡፡

3. ባህላዊ የጋብቻ ስረዓት ከዘመናዊ የጋብቻ ስረዓት ጋር ጎን ለጎን ቢሰራበት ጥሩ ነው ወይስ አይደለም ብለው የገመቱትን ተወያይተው በተናጥል ይፅፋሉ ፡፡ከጎናቸው ሦስት አባላት ያሉት ቡድን በመመስረት የሰጡትን መልስ በየተራ ያነባሉ ፡፡ከውይይቱ በተገኘው ማሻሻያ በግላቸው ይፅፋሉ ፡፡

መርጃ መሳሪያ

ድንበሩ አለሙ (1987 ዓ.ም )

ከጎርዴኔ ሴራ የተወሰደ ቅንጫቢ ፅሁፍ

ግመገማ"

የግልና የጥንድ ተሳትፏቸውን በመከታተል፣ ከአከባቢያቸው የተረዱትን በመግለፅ ድምዳሜና የመፍትሔ ሀሳብ ላይ መድረሳቸውን በማረጋገጥ ተማሪዎች የማንበብና የመፃፍክሂሎችን አቀናጅተው መጠቀማቸውን መመዘን ይቻላል።

የትምህርት አይነት አማርኛ

----------ሚያዝያ----ቀን ---2015 ዓ.ም

ክፍል 9ኛ ለ

የቡድን አባላት ብዛት 50

ሁለተኛ ሳምንት ሁለተኛ ክፍለ ጊዜ

የክፍለ ገዜ ርዝማኔ 1.30

የትምህርቱ ርዕስ ፡- ማንበብ፣ ማሳጠር ፣በጥልቀት ማሰብና መፃፍ

የትምህርቱ አላማ ፡-ከዚህ ትምህርት በኃላ ተማሪዎች ፡-

∆ካነበቡት የጽሑፍ ማሳጠር መመሪያ መሰረት ቅንጫቢ ጽሑፉን በሦስት እጅ አሳጥረው ይፅፋሉ።

∆ ስለምሳሌያዊ አነጋገር የቀረበላቸውን ምሳሌ ካነበቡ በኃላ ሊያስተላልፉ የፈለጉትን መልዕክት ይፅፋሉ።

ዝርዝር ተግባራት

1. ቅንጫቢ ጽሑፍን በመመሪያው መሰረት ተወያይተው በተናጥል በሦስት እጅ አሳጥረው ይፅፋሉ። የሰጡትን መልስ ለማረጋገጥ ከጎናቸው ካሉት ተማሪዎች ጋር በመሆን በየተራ ያነባሉ። ከውይይቱ ባገኙት ማሻሻያ ሀሳብ መሰረት ጽሑፉን እንደገና አስተካክለው በተናጥል ይፅፋሉ።

2. የቀረበውን ምሳሌያዊ አነጋገር ካነበቡ በኃላ የያዘውን መልዕክት በተናጥል ይፅፋሉ። የሰጡትን መልስ ለማረጋገጥ ከኃላቸው ሦስት አባላት ያሉት ቡድን በመመስረት መልሳቸውን ከተማሪዎች ጋር በመቀያየር አንብበው አስተያየታቸውን በጽሑፍ ይሰጣሉ።

መርጃ መሳሪያ

አለሙ ገብረማርያም (2002)

ግምገማ

ቅንጫቢ ጽሑፉን በሦስት አጅ አሳጥረው ሲፅፉ ካነበቡት ጽሑፍ ላይተመስርተው መሆኑን በመከታተል ፡፡የሰጡትን የምሳሌያዊ አነጋገር መልስ በማየትና በመከታተል እንዲሁም የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን ማሻሻላቸውን በመከታተል መገምገም ነው፡፡

የትምህርት አይነት አማርኛ

----------ሚያዝያ----ቀን ---2015 ዓ.ም

ክፍል 9ኛ ለ

የቡድን አባላት ብዛት 50

ሁለተኛ ሳምንት ሁለተኛ ክፍለ ጊዜ

የክፍለ ገዜ ርዝማኔ 1.30

የትምህርቱ ርዕስ ፡- ማብራራትና መተርጎም፣ ማንበብና ማጠቃለል ፣ ዳራዊ እውቀት በመጠቀም መፃፍ፡፡

የትምህርቱ አላማ ፡- ከዚህ ትምህርት በኃላ ተማሪዎች ፡-

∆ ለቅድመ ንባብ ጥያቄዎች መልሳቸውን በጽሑፍ ይሰጣሉ፡፡

∆ በግጥም ውስጥ ያለውን ቁም ነገር አብራርተው ይፅፋሉ፡፡

∆ በግጥምና በዝርው ጽሑፍ ውስጥ ያለውን ልዩነት ይፅፋሉ፡፡

ዝርዝር ተግባራት

1. ሕይወት በነጠላ የሚለውን የግጥም ቅንጫቢ ጽሑፍ ሁሉም ተማሪዎች በተናጥል ያነባሉ፡፡

2. የቅድመ ንባብ ጥያቄዎችን በተናጥል ከሰሩ በኃላ በጎናቸው ካሉ ተማሪዎች ጋር በመቀያየር አንብበው አስተያየታቸውን በጽሑፍ ያቀርባሉ፡፡

3. የግጥምና የዝርው ጽሑፍ ልዩነት በግላቸው ከፃፉ በኃላ አራት አባላት ያለው ቡድን በመመስረት የሰጡትን መልስ እያነበቡ ከተወያዩ በኃላ አስተያየታቸውን በዝርዝር ይፅፋሉ፡፡

መርጃ መሳሪያ

ይስማዕከ ወርቁ ፣ የወንድ ምጥ(፣1999 ፣9)

የግጥም ቅንጫቢ ጽሑፍ

ግምገማ

የግጥሙን ማህበራዊ ፋይዳ ተረድተውእንዲጠቀሙ በማድረግና በመከታተል ፣ የግጥምና የዝርው ጽሑፍ ልዩነት መረዳታቸውንና ግንዛቤ ማዳበራቸውን መከታተል ፣የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን አቀናጅተው መጠቀማቸውን መገምገም

የትምህርት አይነት አማርኛ

----------ሚያዝያ----ቀን ---2015 ዓ.ም

ክፍል 9ኛ ለ

የቡድን አባላት ብዛት 50

ሁለተኛ ሳምንት  ሁለተኛ ክፍለ ጊዜ

የክፍለ ገዜ ርዝማኔ 1.30

የትምህርቱ ርዕስ፡- ማንበብ ፣መተንበይ ፣በጥልቀት ማሰብ፣መገመትና መፃፍ፡፡

የትምህርቱ አላማ ፡-ከዚህ ትምህርት በኃላ ተማሪዎች ፡-

∆ ካነበቡት ተውኔት ተነስተው በአከባቢያቸው የሚከናወነው የጋብቻ ስረዓት ከእድሜ አንፃር ምን መምሰል እንዳለበት ዘርዝረው ይፅፋሉ፡፡

∆ ስለ ተውኔት ምንነትና የተውኔት አላባውያን በመዘርዘር በስነ-ጽሁፍ ውስጥ ያላቸውን ሚና በጽሁፍ ይገልፃሉ፡፡

∆ የቀረበውን የተውኔት ቅንጫቢ ጽሁፍ አንብበውና ተረድተው ለሚጠየቁት ጥያቄ መልሳቸውን በጽሁፍ ይሰጣሉ፡

ዝርዝር ተግባር

1. የተዘጋጀላቸውን ቅንጫቢ ጽሁፍ ሁሉም ተማሪዎች በተናጥል ይፅፋሉ፡፡

2. የፍቅር እስከመቃብር ልቦለድ ታሪክ ባከባቢያችሁ ላሉ ማህበረሰብ ባህልና ወግ ከመግለፅ አንፃር ምን ያህል ተፅኖ ፈጣሪ እንደሆነ የሚገልፅ ጽሑፍ ከተዘጋጁ በኃላ ለክፍል ጓደኞቻቸው ያነቡላቸዋል፡፡

3. በተውኔት ውስጥ መካተት ያለባቸውን ነገሮች ዘርዝረው ከፃፉ በኃላ አራት ቡድን ያሉት አባላት በመመስረት የተዘረዘሩት ነገሮች ከተውኔት አላባውያን ይመደባሉ ወይስ አይመደቡም የሚለውን አንብበው ይሳያሉ፡፡ በተሰጣቸው አስተያየት ላይ በመወያየት ሀሳባቸውን እንደገና አሻሽለው ይፅፋሉ፡፡

4. በአከባቢያቸው ያለውን የመተጫጨት ስረዓት ከዕድሜ፣ ከዘርና ከሀብት ጋር በተያያዘ ምን እንደሚመስል በቡድን ከተወያዩ በኃላ በተናጥል ይፅፋሉ፡፡ በመቀጠል የፃፉቱን እያነበቡ ይወያያሉ እንደገና በተናጥል ይፅፋሉ ፡፡

መርጃ መሳሪያ

ሀዲስ አለማየሁ (1958)

ቅንጫቢ ጽሑፍ

ግምገማ

ስለተውኔት ምንነትና አላባውያን ሲዘረዝሩና ሲያቀርቡ በመከታተል ።በአከባቢያቸው ያለውን የአስተጫጨት ሁኔታ እንዲገልፁ በማደረግና በመከታተል ። የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን አቀናጅተው መለማመዳቸውን መገምገም ይቻላል።

ትምህርት አንድ

*መመሪያ አንድ፡- ጽሁፉን ከማንበባቸው በፊት ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልሳችሁን በፅሁፍ ስጡ (ቅድመ ንባብ ጥያቄ )*

1. በአከባቢያችሁ የሚከናወነው ባህላዊ የጋብቻ ስረዓት አስፈላጊ ነው ወይስ አይደለም ለምን?-- ----------------------------------------------------

2. ባህላዊ ጋብቻ እና ዘመናዊ ጋብቻ ሊያስብሉ የሚችሉ ነገሮች ምን ምን ናቸው ዘርዝሩ?

**ምንባብ**

የጋብቻ ስነ ስረዓት በሁሉም ቦታ ያለ ቢሆንም ከቦታ ቦታ ይለያያል። የኮኪር ገደባኖ አንዳንድ አከባቢዎች የጋብቻ ስረዓት ስንመለከት የልጅቷና የልጅ ቤተሰቦች በያዙት የጋራ የስርግ ቀጠሮ መሰረት ወደ ወንድ ልጅ ቤት አጃቢ ሰጥተው የሚልኳት የራሷ ቤተሰቦች ነበሩ። መንገድ የምትመራ ቤቱን የምትጠቁምና ጥሎሽ የምታከፋፍል ከድንገ ጡሮችዋ መካከል አንዷት ብስለት ያላት ሴት አብራት እንድትሄድ ይደረጋል ። ከወንድ ወገንም እስከ ተወሰነ መንገድ ተጉዘው ሙሽሪቷን ይጠብቁዋትና ተጠያይቀው በመገናኘት ተያይዘው ሙሽራው ቤት ይሄዳሉ። ሙሽራው ቤት ሲደርሱም ከያዙት ኬሻ አንዱን ከጥላ ስር አንጥፈው ይቀመጣሉ። ከዛ መሪዋ ወደ ሙሽራው እናትና አባት ቤት በመግባት ሙሽራዋን ተረከቡን በማለት በቅድሚያ ትጠይቃለች ። የወንድ ልጅ ቤተሰብም እንግዶችን ተቀብሎና ሙሽሪቷን ቦታ ስጥተው አጃቢዎቹንም አስተናግደው ከልጅቷ ቤተሰብ ከተመረጠችው መሪ ለአማት አንድ ጠገራ ብር ለሙሽራው እህት እንዲሁም ለሙሽራይቱ ተላላኪ የያዙትን ጥሎሽ ከከፋፈሉ በኋላ ወንድ ልጅ ተለምኖ ወደ ሙሽሪቷ እንዲሄድ ይደረግ ነበረ።

*መመሪያ ሁለት ፡- ጽሁፉን ከነበባችሁ በኃላ ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልሳችሁን በጽሁፍ ስጡ ( ድህረ ምንባብ ጥያቄዎች )*

1. ከባህላዊ የጋብቻ ስረትና ከዘመናዊ የጋብቻ ስረዓት ክዋኔ ያለው የትኛው ነው ለምን?

2.በባህላዊ ጋብቻና በዘመናዊ የጋብቻ ስረዓት ውስጥ የጋራ የሚሆነው የስረዓት አይነት ምን ምን ናቸው?

ትምህርት ሁለት

መመሪያ አንድ፡-የቀረበውን ታሪክ ከማንበባቸው በፊት ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልሳችሁን በጽሑፍ ስጡ( ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች)፡፡

1. አንድን ጽሑፍ ወይም ታሪክ አሳጥረን ለመፃፍ ስናስብ መጀመሪያ መደረግ ያለበት ቅድመ ሁኔታ አብራርታችሁ ፃፍ፡፡

2. በርካታ ሰዎች መልዕክታቸውን ሚዛን እንዲፅፋ ለማድረግ ምሳሌያዊ አነጋገሮችን በጻሁፋቸው/ በንግግራቸው መካከል ጣልቃ በማስገባት የሚጠቀሙት ለምን ይመስላችኋል አብራርታችሁ ፃፉ፡፡ --------------------------------------------------------

የሚከተለውን ጽሁፍ በሦስት እጅ አሳጥሩና ፃፉ

ባህል ሲባል በህብረተሰብ ታሪክ ሂደት ውስጥ መላው የሰው ልጅ የፈጠራቸውን ቁሳዊና መንፈሳዊ ቅርሶችንና እንዲሁም እነዚህ ቁሳዊና መንፈሳዊ የባህል ግንኙነቶች የተፈጠሩበን ግልጋሎት ላይ የሚውሉበትንናየሚተላለፉበትን ዘዴዎች ያጠቃልላል ፡፡ ቁሳዊ ባህል የሚባለው የሰው ልጅን ቁሳዊ ክንውንንና ውጤቶችን የሚሸፍን መስክ ሲሆን፣ ይህ የቴክኒክ መገልገያ መሳሪያዎችን ፣የማምረት ልምድና ሌሎችንም ቁሳዊ ሀብቶች በማጠቃለል ይይዛል ፡፡ መንፈሳዊ ባህል የሚባለው ደግሞ ሰዎች ቁሳዊ ምርትን በማምረት ሂደት የሚያመርቱት የመንፈሳዊ ምርት መስክ ሲሆን ይህም እንደ ሳይንስ ትምህርት ሥነ ጥበብ ፣ፍልስፍና ወዘተ----- የመሳሰሉትን ባህላዊ ቅርሶችን ያጠቃልላል፡፡ እነዚህ የቁሳዊና የመንፈሳዊ ባህል መስኮች የተነጣጠሉ ሳይሆን እርስ በርሳቸው የተያያዙ ነቸው፡፡ በመካከላቸው ባለው ግንኙነት ውስጥ መንፈሳዊ ባህል ከቁሳዊ ባህል የሚመነጭና በሱም የሚወሰን ይሁን እንጂ መንፈሳዊ በቁሳዊው ላይ ተመልሶ የራሱን ተፅዕኖ ያሳርፋል፡፡ ይኸው የቁሳዊ ባህል ዕድገት ደግሞ ተመልሶ በተራው የመንፈሳዊ ባህል ዕድገት ያዳብራል፡፡

መመሪያ ሁለት ፡- የቀረብቱን የተለያዩ ምሳሌዊ አነጋገር ካነበባችሁ በኃላ የሚያስተላልፉትን መልዕክት ፃፉ፡፡

| ምሳሌያዊ አነጋገሮች | መልዕክታቸው |
|---|---|
| 1. እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል | ------------------------------------------------------- |
| 2. ሰርቆ ከማሰብ እጅን መሰብሰብ | ------------------------------------------------------- |
| 3. አፍንጫን ሲመቱት አይን ያለቅሳል | ------------------------------------------------------------- |
| 4. አተርፍ ባይ አጉዳይ | |

ትምህርት ሦስት

መመሪያ አንድ፡- የቀረበውን ግጥም ከማንበባችሁ በፊት ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልሳችሁን በጽሑፍ ስጡ፡፤ (ቅድመ ምንብባ ጥያቄዎች )፡፡

1. ከግጥምና ከዝርው ጽሑፍ አንባቢን /አድማጭን ይበልጥ የሚስበው የጥኛው ነው? ለምን? አብራርታችሁ ጻፉ፡

2. በግጥምና በዝርው ጽሑፍ መካከል ያሉ ልዩነቶች ምን ምን እንደሆኑ በዝርዝር ፃፉ፡፡

ሕይወት በነጠላ

አፈር ጥጡን ለቅሞ፣አባዝቶ----------አሳስቶ

በእፍታ ብርቱ፣አዳምጦ -------------አጥርቶ

በእስትንፋስ ደጋኑ ፣ነድፎ -----------አስፋፍቶ

ልቃቂት አልቆ፣በህላዊ እንዝርቱ፣ፈትሎ---------አመልማሎ

ሕይወት ነጠላ ነው፤

አምላክ የሸመነው ፣አምላክ ቀጭን ፈትሎ ፡፡

ዘህውና ማጉ ፣ነው ተመሳሳዩ ፣ኑሮ ጥልፍልፉ፡፡

ሞት ጥለሞት ጌጡ ፣

ለነባሬው ጣዕም ለበኩሉ ምዕራፍ ፡፡

መጋጠሚያ ውሉ ፣ የማህልስፌቱ ፣ ነጠላ ጥንደቱ፣

ልዩነት ውህደቱ፣ ጥበቡ አንድነቱ፣አብሮነት ሀሴቱ ፤

የሚፈራገጠው አልቋጭም ባዩ በዘርፉ ቁጭቱ፣

እምቢ ልኑር ባዩ፣

ነጠላ ቀጭኑ ሕይወት ተፈታዩ፣

------ላንዱ ተዘቅዝቆ፣

-------ለሌላው ሽብርቶ፣

ላንባንዱ ማሰሻ፣ የመርገምት ጨርቁ፣

ላንዳንዱ ነጭ ኩታ፣

ደግ ሆነ ምናዬው -------ላንዱ ደግሞ ማቁ፣

ሕይወት ነጠላ ነው ፤

አምላክ ቀጭን ፈትሎ ፣ አምላክ የሸመነው ፤

ሞገሱና እድሜው ግን ፣ እንደለባሹ ነው ፡፡

ይስማከ ወርቁ፣የወንድምጥ (1999፣9)

*መመሪያ አንድ ፡- ከቀደሞ ልምድና ካነበባችሁት ግጥም ተነስታችሁ በመገመት በመተንበይ ከምንባቡ ለወጡ ጥያቄዎች መልሳችሁን በጽሁፍ ስጡ (ድህረ ምንባብጥያቄዎች )።*

1. *ግጥም በሚነበብበት ጊዜ ዜማውን ጠብቃችሁ አንብቡ የሚባለው ለምን ይመስላችኃል? ዘርዝሩ?* ------------

2. *ሕይወት ነጠላ ነው ሲል ምን ማለቱ ነው? በአጭሩ አብራሩ* ?----------------------------------
------------

3. *አልቋጭም ባዩ ማነው ከግጥሙ መልዕክት በመነሳት መልሳችሁን ፃፉ፡*

## *ትምህርት አራት*

*መመሪያ አንድ ፡- የቀረበላችሁን ቅንጫቢ ጽሑፍ ከማንበባችሁ በፊት ለቀጣዮቹ ጥያቄዎች መልሳችሁን በጽሁፍ ስጡ (ቅደመ ምንባብ ጥያቄዎች )።*

1. *ካነበባችኃቸው የልብ-ወለድ መፀሀፍት ውስጥ የምታስታውሷቸውን ገፀ-ባህሪት በዝርዝር ጥቀሱ*-----------------

2. *በሬድዮና በቴሌቭዥን እንዲሁም በመድረክ ቀርበው ከተከታተላችኃቸው ተውኔት ውስጥ የምታስታውሷቸውን ገፀ-ባህሪያት ዘርዝሩና ገፀ-ባህሪያቱን ለም እንደምታስታውሷቸው በፅሑፍ ግለፁ*።:----------------------------------

## ቅንጫቢ ጽሑፍ

***ቄስ ታምሩ፡-*** *«ብርቱ ጉዳይ አለኝ እፈልግዎታለሁ» ካሉኝ ሰነበቱ አይደል አያ ቦጋለ ?*

***አያ ቦጋለ ፡-*** *«አዎ! ሰንበተ ብሏል ፤እስካሁን ከቆየሁት አይበልጥም፤ እታገሳቸዋለሁ፤ፋታ የማይሰጥ ጉዳይ አጋጥሚቸው ይሆናል» ብዬ ነው።*

***ቄስ ታምሩ፡-*** *አይ የኔ ነገር ! አንዳንዴ እዘነጋለሁ፤ አንዳንዴ ደግሞ እርስዎም እንደሚያውቁት የንስሐ ልጆቼ ከዚያም ከዚህም ይጠሩኛል ።አሁን ዛሬ ትዝ ሲለኝ ጊዜ« አያ ቦጋለን ከብቶች ከሚያግዱበት ቦታ አላጣቸውም »ብዬ ነው ደንግጬ የመጣሁት ፤ ለመሆኑ የፈለጉኝ በደህና ኖሯል ?*

***አያ ቦጋለ፡-*** *ደህናስ ደህና ነኝ ፤ እንዲያው ብቸኝነት ሲከብደኝ ጊዜ «ለምን አንድ ውሃ አጣጬን አንፈልግም » የሚል ሀሳብ ከታየኝ ሰንበት ብሏል።*

***ቄስ ታምሩ፡-*** *የማንን ልጅ አሰቡ ?የትኛዋን ልጃገረድ አዬ?*

***አያ ቦጋለ፡-*** *ኸረ እንዲያም አይደል፤ በዚህ እድሜዬ የማንንም ልጅ ለጋብቻ መጠየቅ አልሻም።*

***ቄስ ታምሩ ፡-*** *ታዲያ በየትኛዋ ፊት ላይ ነው ቀልቦ ያረፈው ?*

***አያ ቦጋለ ፡-*** *ኸረ ሩቅም አይደል የሄድኩት !ከዚሁ ከጎረቤቴ አንዷት ሴት አይቻለሁ።*

**ቄስ ታምሩ፡-** *ማንን ነው የዩት ? እመት ውድነሽን ውይስ ሌላ ሴት ?*

**አያ ቦጋለ** ፡- (እያቅማሙ-----) እንዴት ባንዴ ደረሱብኝ !እንዴት በአንዴ አገኑኝ !

**ቄስ ታምሩ** ፡-ነገሩ ጥሩ ነው፡፡እመት ውድነሽ ባሎቿ በተራ ሞተውባት የለ!---

**አያ ቦጋለ** ፡-አዎ ! እሱማ አውቃለሁ -----ሀሳቤን በውስጤ ደብቄ ከርሜያለሁ፡፡ አሁን አሁን ብቻዬን ከመሆን ሰው ይሻለኛል ፤ ከወዲህም ለቁንጅናዋ ምንም አይወጣላት፡፡ ሞት እንግዲህ ለሁሉም አይቀር ፤ እጣ ፈንታችን አይደል! የአንድዬ ፍቃድም ከሆነ ዘር ማትረፍም ደግ ነው፡፡

**ቄስ ታምሩ፡-** *ነገሩማ ደግ ነው ፤ነገር ግን* እመት ውድነሽ «ከእንግዲህ ትዳር አላስብም ፤ የቀረውን እድሜዬን ብቻዬን እገፋለሁ» ትላለች አሉ፡፡

**አያ ቦጋለ** ፡- እስዎን መፈለጌ ለዚሁ አይደል! በአንድ በኩል የንሰሐ ላጅዎ ናት ፤ በሌላ በኩል ደግሞ የሀይማኖት አባት እንደመሆነዎ በአከባቢያችን ከእርስዎ ቃል ማንም አይወጣም ብዬ ነው፡፡ እና ሀሳቤን ለእርስዎ ከነገርኩ ጭንቀቴ የለቀቀኝ መሰለኝ፡፡ ውለው ሳያድሩ ይጠይቁልኝ ፤ ይጠይቁልኝ ብቻም አይደልም ፤ እሺ ያስኙልኝ፡፡

**ቄስ ታምሩ** ፡- እስቲ እሱ ይጨመርበት! እኔማ እንደዚ ላለ ጉዳይ ቀጠሮም አልሰጥ ፤ ደግሞ እሺ ላሰኛት እሞክራለሁ፤ ከቃሌ የምትወጣ አይመስለኝም፡፡

**አያ ቦጋለ** ፡- ባዶ አፍዎን እንዲያው ዝም ብዬ--------በደረቁ------

**ቄስ ታምሩ፡-** እዳሜ ይስጠን ፤ለወደፊት እንደርስበታለን ፤ደህና ይዋሉ አያ ቦጋለ

**አያ ቦጋለ** ፡- ደህና ይዋሉ ፤ የምትልዎትን ቶሎ ያድርሱኝ፡፡--------

*መመሪያ ሁለት* ፡- ከቀድሞ ልምድና ካነበባችሁት የታሪክ ሂደት ተነስታችሁ በመገመት ፣ በመተንበይ ምንባቡ ውስጥ ለተካተቱ ጥያቄዎች መልስ ስጡ (ድህረ ምንባብ ጥያቄዎች )፡፡

1. በጽሑፈ ተውኔት ውስጥ የቀረቡት ቄስ ታምሩ፣ አያቦጋለና እመት ውድነሽ በስነ-ጽሑፍ ቋንቋ ምን ተብለው ይጠራሉ ምክያታችሁን በመግለፅ አብራርታችሁ ፃፉ፡፡-------------------------------------------------------------

2. እመት ውድነሽ በጣሙ አያቦጋለን ለማግባት ያቅማሙት በምን ምክኒያት እንደሆነ በዝርዝር ፃፉ፡፡

3. በቀረበው የተውኔት ጽሑፍ ውስጥ ከባህል ጋር ሊያያዙ የሚችሉ ነገሮች ምን ምን ተነስተዋል? ለዩና በጽሑፍ ግለፁ

## አባሪ ስምንት፡ የቅድመ እና ድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት ዝርዝር

| ቅድመ ትምህርት ፈተና ውጤት | | | ድህረትምህርት ፈተና ወጤት | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ተቁ | መለያ ኮድ | ውጤት ከ100% | ተቁ | መለያ ኮድ | ውጤት ከ100% |
| 1 | 01-2 | 32 | 1 | 0.1-ለ | 74 |
| 2 | 0.2-2 | 27 | 2 | 0.2-ለ | 62 |
| 3 | 0.3-2 | 32 | 3 | 0.3-ለ | 51 |
| 4 | 0.4-2 | 51 | 4 | 0.4-ለ | 30 |
| 5 | 0.5-2 | 52 | 5 | 0.5-ለ | 67 |
| 6 | 0.6-2 | 51 | 6 | 0.6-ለ | 61 |
| 7 | 0.7-2 | 52 | 7 | 0.7-ለ | 57 |
| 8 | 0.8-2 | 46 | 8 | 0.8-ለ | 35 |
| 9 | 0.9-2 | 35 | 9 | 0.9-ለ | 58 |
| 10 | 10-2 | 30 | 10 | 10-ለ | 70 |
| 11 | 11-2 | 22 | 11 | 11-ለ | 56 |
| 12 | 12-2 | 41 | 12 | 12-ለ | 60 |
| 13 | 13-2 | 53 | 13 | 13-ለ | 100 |
| 14 | 14-2 | 41 | 14 | 14-ለ | 84 |
| 15 | 15-2 | 36 | 15 | 15-ለ | 52 |
| 16 | 16-2 | 41 | 16 | 16-ለ | 48 |
| 17 | 17-2 | 52 | 17 | 17-ለ1 | 71 |
| 18 | 18-2 | 25 | 18 | 18-ለ | 67 |
| 19 | 19-2 | 48 | 19 | 19-ለ | 62 |
| 20 | 20-2 | 27 | 20 | 20-ለ | 57 |
| 21 | 21-2 | 46 | 21 | 21-ለ | 75 |
| 22 | 22-2 | 33 | 22 | 22-ለ | 89 |
| 23 | 23-2 | 48 | 23 | 23-ለ | 87 |
| 24 | 24-2 | 31 | 24 | 24-ለ | 47 |
| 25 | 25-2 | 52 | 25 | 25-ለ | 67 |
| 26 | 26-2 | 58 | 26 | 26-ለ | 83 |
| 27 | 27-2 | 53 | 27 | 27-ለ | 58 |
| 28 | 28-2 | 27 | 28 | 28-ለ | 66 |
| 29 | 29-2 | 58 | 29 | 29-ለ | 71 |
| 30 | 30-2 | 37 | 30 | 30-ለ | 95 |
| 31 | 31-2 | 66 | 31 | 31-ለ | 79 |
| 32 | 32-2 | 53 | 32 | 32-ለ | 76 |
| 33 | 33-2 | 53 | 33 | 33-ለ | 76 |
| 34 | 34-2 | 13 | 34 | 34-ለ | 78 |
| 35 | 35-2 | 67 | 35 | 35-ለ | 66 |
| 36 | 36-2 | 63 | 36 | 36-ለ | 77 |
| 37 | 37-2 | 63 | 37 | 37-ለ | 70 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 38 | 38-2 | 40 | 38 | 38-ለ | 65 |
| 39 | 39-2 | 26 | 39 | 39-ለ | 41 |
| 40 | 40-2 | 50 | 40 | 40-ለ | 63 |
| 41 | 41-2 | 40 | 41 | 41-ለ | 77 |
| 42 | 42-2 | 30 | 42 | 42-ለ | 45 |
| 43 | 43-2 | 45 | 43 | 43-ለ | 61 |
| 44 | 44-2 | 57 | 44 | 44-ለ | 44 |
| 45 | 45-2 | 72 | 45 | 45-ለ | 59 |
| 46 | 46-2 | 56 | 46 | 46-ለ | 85 |
| 47 | 47-2 | 70 | 47 | 47-ለ | 78 |
| 48 | 48-2 | 48 | 48 | 48-ለ | 68 |
| 49 | 49-2 | 66 | 49 | 49-ለ | 97 |
| 50 | 50-2 | 65 | 50 | 50-ለ | 80 |

## አባሪ ዘጠኝ ለቡድኑ አባላት ማስተማሪያነት የተዘጋጀ እቅድ

የመ/ሩ ስም ለምለም ከበደ — ቀን 15/08/2015ዓ.ም

የት/ት አይነት አማርኛ — የክፍል ደረጃና ሴክሽን 9ኛ ለ

የክፍለ ጊዜ እርዝማኔ 40 ደቂቃ — የትምህርት ርዕስ አንብቦ መረዳት

| የትምህርቱ አላማዎች | የትምህርቱ ይዘቶች | ለመማር ማስተማር ክንዋኔ የመምህ ተግባር | በመማር ማስተማር ክንዋኔ የተማሪው ተግባር | የግምገማ ስልት |
|---|---|---|---|---|
| አንድን ፅሁፍ አንብበው ያገኙትን ቁም ነገር ያስረዳሉ ፡ ፡<br>ቃላትን ያዛምዳሉ<br>ለቃላት የሚስማሙ ፍቺዎችን ያብራራሉ፡፡ | አንብበው ያገኙትን ቁመነገር መግለፅ፡፡<br>ቃላትን ማዛመድ፡፡<br>የቃላትን አውዳዊ ፍቺ በቃል መግልፅ፡፡ | ቅድመ ንባብ ሁኔታዎችን ማመቻቸትና ከማንበባቸው በፊት ምን ማድረግ እንዳለባቸው መግለፅ፡፡<br>በንባ ጊዜ ምን ማድረግ እንደሚጠበቅባቸው ማሳወቅ፡ ፡<br>አንብበው ሲጨርሱ በጨብጡ ላይ እንዲወያዩ ማድረግ፡፡<br>ቃላትን እንዲያዛምዱና ለቃላትና ሀረጎች ፍጪ እንዲሰጡ ማድረግ፡፡<br>ለሁሉም ተግባራት ማጠቃለያ መስጠት፡፡ | የመወያያ ጠያቂዎችን መስራት ፡፡<br>በፅሁፍ ውስጥ የተካተቱተን ፊሊጦች መለየት ፤የዘይቤዎችን ምንነትና ፋይዳ ለመግለፅ መሞከር፡፡<br>በጭብጡ ላይ መወያየት፡፡<br>ቃላትን ማዛመድና ለቃላት ፍቺ መስጠት፡፡ | በቡድን እነዲወያዩ ማድረግ፡<br>ቅድመና ድህረ ጥያቄ መጠየቅ፡፡<br>መልመጃዎችን ማሰራት፡ |

## አባሪ አስር፡ተማሪዎች ትምህርት ሲማሩ የሚያሳይ መረጃ በፎቶ

